# አውራምባ ታይምስ

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

2ኛ ዓመት ቁጥር 97 | ጥር 01 ቀን 2002 | ዋጋ 5.00 ብር




## የኢህአዴጉ ከፍተኛ አደራጅ ስለ ብርቱካን

7



ፎቶ አውራምባ ታይምስ (ሲሳይ ጉዛይ)

# የኤርትራን ነገር

## «ትውልድ የቆረጠውን ትውልድ ይቀጥለዋል»

ቴዲ አፍሮ


ሰ

ለፉት ጥቂት ወራት በአውሮፓና በአሜሪካ የሙዚቃ ዝግጅቱን ለአድናቂዎቹ ሲያቀርብ ቆይቶ ወደ አገሩ የተመለሰው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ በዓመቱ ሁለተኛውንና «ሙዚቃ ህይወቴ» የተሰኘውን ታላቅ ኮንሰርት በትናንትናው እለት በግዮን ሆቴል አቀረበ::

ይህ ኮንሰርት እጅግ የተሳካና በሰላም የተጠናቀቀ ሲሆን ብዙ ሁኔታዎቹ ከእስታዲየሙ ኮንሰርቱ ጋር ያመሳስለዋል:: ለምሳሌ ያህል ህዝበ ትኬተ ለመግዛት የተሰለፈበት ርዝመት፣ መድረኩና ከመድረኩ ጀርባ የተተከሉ ነጫጭ የማረፊያ ድንኳኖች ከስታዲየሙ የሙዚቃ ድግስ ጋር በመጠኑ አመሳስሎታል::

በዕለቱ ወደ ግዮን ሆቴል ስናመራ እጅግ በርካታ የቴዲ አድናቂዎች ትኬቱን ለመግዛት ሲተረማመሱ ይታይ ነበር:: ይሁንና የሁሉንም ፍላጎት ለማሟላት (ትኬት ያላገኙ እስኪያገኙ ድረስ) ቴዲ እስከ 3:20 ሰዓት ድረስ ወደ መድረክ ብቅ አላለም:: እርግጥ ድምፃዊው እዛው ግቢ ውስጥ እንደነበርና ከምሽቱ 12:00 ሰዓት አካባቢ መድረክ ላይ መጥቶ መድረኩንና ሳውንድ ሲስተሙን ጉብኝቶና አረጋግጦ እንደገባ አዘጋጆቹ ገልጸዋል:: ቴዲ ወደ መድረክ መጥቶ መዘፈን እስኪጀምር ድረስ ዲጄ ዊሽ እና ዲጄ መሳይ ከመድረክ በሚለቋቸው የውጭና የአገር ውስጥ ሙዚቃዎች ህዝቡ እየተዝናና ቆይቷል:: በተለይም


ወደ ገፅ 9 ዞሯል



## «የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ የመስጠት ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም»

አቶ ስዬ አብርሃ

10



## አገራዊው ፈተናና ፖለቲካዊው ጥያቄ

4


በውስጥ ገፆች

የዋና አዘጋጆችን መብት የገፈፈው የኢቲቪው ውይይት

አስር ሚሊዮኖች በርሃብ
በሰላምና በትምህርት እጦት እስከመቼ?

በ«ህዳሴው ዋዜማ» ሲዲ ላይ ያልጠገብናቸውን ሰዎች በ«ጨለማው ጉዞ» ዶክሜንተሪ አገኘናቸው

መድረክና መኢአድን ሲያወዛግብ የነበረው የምርጫ ምልክት ለመኢአድ ተሰጠ

## ኤዲቶሪያል

# ብልሹ አስተዳደር ማሕበራዊ ቀውስን እንዲያቀጣጥል መፈቀድ የለበትም!

ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለክርስቶስ ኢየሱስ የልደት በዓል አደረሳችሁ እንላለን፡፡ የልደት በዓሉ በተለያዩ ኃይማኖታዊና ባሕላዊ መንገዶች የተከበረ ሲሆን የተቸገሩ ወገኖችን በማስታወስና በመመገብ ዕለቱን ለዘከሩ ምዕመናን ያለንን አድናቆት እንገልፃለን፡፡ የዚህ አይነቱ አሳቢነት በአገራችን ባሉ የተለያዩ እምነት ተቋማት ሁሉ የሚተገበር መሆኑ ደግሞ በእጅጉ የሚያስደስትና ልንንከባከበው የሚገባን ልዩ እሴታችን ነው፡፡ ከታወቀበት ይህን ልዩ እሴት ወደ ግዙፍ አገራዊ ፋይዳ መቀየር እንደሚቻል ለመጠቆም ወይም ለማስታወስ እንወዳለን፡፡

ሁላችንም እንደምናስታውሰው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት አዋጅ በወጣበት ወቅት ከባለ ድርሻ አካላቱና ከተለያዩ ወገኖች ከፍተኛ ተቃውሞ ቀርቦበት ነበር፡፡ ይህ የሆነው በተለይ በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች እንደነበር ከክርክሮቹ ጭብጥ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው አንድ ድርጅት ከአስር በመቶ በላይ የገንዘብ ምንጩ ከውጭ የሚገኝ ከሆነ እንደኢትዮጵያዊ ድርጅት አይቆጠርም የሚለው ነው፡፡ ህጉን ያወጡ ሰዎች ይህ መመዘኛ ሲዘጋጅ የራሱን ታሳቢ ጥናቶች ያካተተ መሆኑን ቢሰብኩም፤ አንዳንድ አገር ወዳድ ዜጎች ከተጠቀሰው መጠን በላይ አሩት ከውጭ በማምጣታችን ብቻ እንደኢትዮጵያዊ ያለመቆጠራችን ኢ-ስነአመክንዮአዊ ከመሆኑም በላይ አሉታዊ ስነ ልቦና አለው ብለው ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛው ነጥብ ከዚህ የተለየ ነበር፡፡

እነዚህ ድህነትን ለመቀነስ፣ አደጋን ለመከላከል፣ ጥበብን፣ ባህልንና ትምህርትን ለመስፋፋት እንዲሁም የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ለማበረታታት በሚል የሚቋቋሙ ድርጅቶች የገንዘብ ምንጫቸውን ከአገር ውስጥ ለማሰባሰብ የሚያስችል ልምድና መዋቅር ኖሮ አያወቅም የሚል ሲሆን ይህም የአሴት ሳይሆን የመዋቅር መዘርጋትና ችግሮችን በራስ መንገድ ለመፍታት የሚደረገውን መንፈሳዊ ዝግጁነት የማስረጽ ክንዋኔ ታሳቢ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ በመግቢያችን ላይ የተመለከትነው በአገራችን ባህል ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የመተጋገዝና ለሌሎች አሳቢነት በተሞላው መንገድ የሚደረግ የማካፈል እሴት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል እንላለን፡፡

80 ሚሊዮን አካባቢ ሕዝብ እጅግ ብዙ ነው፡፡ ሰፊ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ያስፈልጋሉ፡፡ ይህን አሃዝና እያሻቀበ የመሄዱን እውነታ ያገናዘቡ መፍትሔዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ትምህርት፣ ጤና፣ ንጽህና፣ ማህበራዊ ደህነነትና

የመሳሰሉት ይህን ታሳቢ ያደረጉ መሆን አለባቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት የሚያሳስበንን ያህል ይህ እንደአሉታዊ ሁነት የምንቆጥረው የሰው ኃይል ወደላቀ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ደረጃ ለመድረስ እንደግብአት ማገልገል እንደሚችል ጥናቶች ይጠቁማሉ:: ሰፊ የሰው ኃይል፣ ያልተጠቀምንበት ጥሬ ሃብትና ምርቶቻችንን በብዛት ሊጠቀም የሚችል የሕዝብ ብዛት/መጠን/ አለን:: ሰፊ የገበያ እድል አለን ማለት ነው:: ይሁንና የተጣቡን የሚመስሉ ችግሮች አሉ::

አሁንም ከ50 እስከ 60 በመቶ የሚሆነው ሕዝባችን ከድህነት ወለል በታች እንደሚገኝ ጥናቶች ያመለክታሉ:: ችግሩ ደግሞ የድህነት ብቻ አይደም:: ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ከአደጋ የነፁ አይደሉም:: የተዛባ የብሔር ወገንተኝነት፣ የተዛባ የፖለቲካ ወገንተኝነት፣ ነፃ አስተሳሰብን የምንረዳበት የተዛባ ስሌት አለ:: እነዚህን ሁሉ ችግሮች ተሸክመን በስኬት ጎዳና ላይ እየተጓዝን ነው ከማለት ይልቅ የችግሮቻችን ምንጮች ልንመረምርና በመፍትሔያቸው ላይ ልንረባረብ ይገባናል:: ለእነዚህ ችግሮች በዋና መንስኤነት የሚጠቀሰው የፓለቲካው ብልሹነት ሲሆን የሚንፀባረቅበት መንገድም አሳሳቢ ነው::

የአገራችን ፖለቲካ የኃይል የበላይነት ያለው ከታች ያለውን ሁልጊዜ የሚደቁስበትና ዴሞክራሲን በመስበክ ሽፋን ፍላጎትን በመጫን የሚታወቅ ሲሆን ልዩነት የሚገለጽባቸው መንገዶችም «አንዱ አይመለስ ሌላው አይታገስ» የሚሉት አይነት ነው:: ልዩ እሴት ነው ካልነው የሕዝባችን የባህል የእምነትና የአስተሳሰብ ስነ ልቦና መሰረት ተነስቶ ሁኔታዎችን ከማስተካከል ይልቅ ሁልጊዜ ተመሳሳይ ስህተት፣ ተመሳሳይ ሽንፈትን የመደጋገም ተሞክሮ አለ:: ይህም ስልጡን ማሕበረሰብ ለመገንባትና ዴሞከራሲያዊ መንግስት ሳናይ እንድንቀር እያደረገ ነው::

የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መረገጥ፣ የመንግስታዊ ተጠያቂነት መርህ መላላት፣ ብልሹ አስተዳደርና የመሳሰሉት ለአስከፊ ድህነት ለኋላቀርነት፣ ለማሕበራዊ ቀውስ መንስኤ ሲሆኑ አንዳቸው ከሌላኛው ጋር ያላቸው ትስስርም የጠበቀ ነው:: ድህነት ካለ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የላላ ይሆናል:: በኋላቀር አገር ውስጥ መንግስታዊ ተጠያቂነትን ለማስፈን ያስቸግራል፤ ለገዢዎችም ተጠያቂነት የሌለበትን ምህዳር ያሰፋላቸዋል:: ብልሹ አስተዳዳር እያለ ማሕበራዊ መረጋጋት አይታሰብም::ብልሹ አስተዳደር ማሕበራዊ ቀውስን እንዲያቀጣጥል መፈቀድ የለበትም! ስለዚህ አንዳቸው ከሌላኛው ያላቸውን መስተጋብር ለመበጠስ የኢትዮጵያዊነት ልዩ እሴቶችን ፍቱን መድሃኒቶች አድርጎ መጠቀም ይገባል:: እውን እንዲሆኑ ግን ከሁሉም የባለድርሻ አካላት በተለይም ከፓለቲከኞቻችን ብዙ እንጠብቃለን::

ከፖለቲከኞቻችን ብዙ እንጠብቃለን ስንል የማይወጡትንና ሊያደርጉት የማይችሉትን ያድርጉ እያልን አይደለም:: የኃላፊነት ወሰናቸው በሚፈቅድላቸው መጠንና ግዴታ ይስሩ ለዚህም ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ጥቅም እንታገላለን የሚሉ ከሆነ ቀጥሎ ያሉትን ሁነቶች በመመርመር ከሕዝቡ ልዩ እሴቶች ጋር አቀናጅተው እንዲጠቀሙባቸው መልዕክታችንን እናስተላልፋለን::

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንጻራዊ ሁኔታ አሁን ካሉበት የበለጡ ተግባራት የሚጠበቁ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ ኢህአዴግ እንደገዢ ፓርቲነቱ በጫንቃው ላይ የሚወድቁ የፖለቲካ፣ የማሕበራዊና የኢኮኖሚ ተጠየቆች አሉበት:: በአሁኑ ወቅት የፖለቲካው ትኩሳት የሚያጠነጥነው በግንቦቱ ምርጫ ዙሪያ ነው:: የግንቦቱ ምርጫ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄድ የሂደቱ ነፃ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ የመሆን መጠንም በአገራችን ውስጥ ስር ሰድደው ለቆዩና እርስ በርሳቸው እየተደጋገፉ ዜጎችን ለመከራ ሲዳርጉ ሊኖሩ ችግሮች መቆም ወይም መቀጠል አቅጣጫ ጠቋሚ ይሆናል:: ይሁንና ግን በብዙዎች ዘንድ (በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ጭምር) የዚህ ምርጫ ውጤት እንደተበላ እቁብ እየተቆጠረ ያለበት አሳሳቢ ሁኔታ ይንፀባረቃል::

200 ሺህ የምርጫ አስፈፃሚዎች ተመርጠዋል:: ከ1997ቱ የበለጠ የምርጫ ጣያዎች (40 ሺህ ያህል) ተዘጋጅተዋል:: በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የምርጫ ጣያዎች በሰው ኃይልና በቁሳቁስ እየተደራጁ ነው:: ከፍተኛ ወጪ ተመድቦ በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ የሕዝብ ምርጫ ታዛቢዎች ስልጠና እየተሰጠ ነው:: በምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ ላይም የግንዛቤ ማስጨበጫ እየተሰጠ ነው:: ይሁንና እነዚህ ሁነቶች ብቻቸውን ጥርጣሬውን ሊያስወግዱ አልቻሉም::ለምን? የሚለው መመለስ ይኖርበታል::

ይህ የሆነው አማላይ የምርጫ ሂደት ክንውን ዘገባዎችን ብቻ እያቀረቡ «ደረሰ፣ ደረሰ» ቢሉት በአንድ እጅ ከማጨብጨብ የተለየ ስለማይሆን ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅን፣ ተባባሪና እምነት የሚያሳድር ቢሆንም አጠራጣሪ ነገሮች ሲያጋጥሙት ተቃውሞውን በገለልተኝነት (በዝምታ) የሚገልጽበት ልዩ እሴት ያለው ሕዝብ ነው::ምርጫው ነጻ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆንና መሆኑንም ለማሳየት መፍትሄው ምንድነው?

መጀመርያ ጥርጣሬዎቹ ከሰማይ የወረዱ ያለመሆናቸውን መቀበል ግድ ይላል:: ለጥርጣሬዎቹ መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን ማለትም በምርጫ ቦርድና በምርጫ አስፈፃሚዎች አመራረጥ ላይ ግልጽና ፍትሃዊ አቋም መያዝና ይህንኑም ለሕዝቡ ማሳወቅ በተለይ የምርጫ አስፈፃሚዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው ከሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ሲውጣጡ ወይም ተቀይነት ሲኖራቸው ብቻ መሆኑን መግፋት አይቻልም:: ተወዳዳሪዎች የምረጡኝ ቅስቀሳቸውን የሚያካሂዱት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታው ከሚኖረው ወሳኝነት አንፃር በመሆኑ ተገቢ ባልሆነ የፖለቲካ ወገንተኝነት ተጽእኖ እንዳይደረግባቸው ጥበቃ እንዲያገኙ ሊሰረግ ይገባል:: በተጨማሪም በክልሎች የሚከፈቱ የተቃዋሚ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ቀደም ሲል በገለጽነው ተገቢ ያልሆነ የፖለቲካ ወገንተኝነት ሲዘጉና በአስተባባሪዎቹ ላይ እንግልት ሲፈፀም ለሕግ የበላይነት ያለው እሳቤ ትምክህት የማይጥልበት እንደሚያደርገው መገንዘብ ያስፈልጋል:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚደረግ ምርጫ የበላይነት በምን እንደመጣ ስለሚታወቅ ተስፋውን ያደበዝዘዋል የሚል ስጋት አለን::

ከፖለቲካው ስንወጣ ሚሊዮኖችን ከርሃብና ድህነት ማላቀቅ ያልቻለው የግብርና ልማት ፖሊሲ፣ የመሬትና የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ፣የገንዘብና የመሳሰሉትን

ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እናገኛለን፡፡ እነዚህ በአመታት ሂደት ውስጥ ሊቀረፉ ያልቻሉ ጉዳዮች ዜጎች የሚፈልጓቸውን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በሩቁ እንዲመለከቷቸው አስገድደዋቸዋል፡፡ የመኖሪያ ቤት እጥረትን ለመቅረፍ እንደመፍትሄ የተወሰደው የኮንዶሚኒየም ፖሊስ ከ50-60 በመቶ ሕዝብ ከድህነት ወለል በታች ለሚኖርባት አገራችን የታሰበ ነው ቢባል ትዝብት ከማጫር የዘለለ ትርጉም አይኖረውም፡፡ አማካይ ገቢ ያላቸው እንኳ አልቻሉትምና፡፡ በአጠቃላይ ግን ገዢው ፓርቲ ቀጣዩን ምርጫ እንደተጨማሪ አጋጣሚ በመቁጠር ፖሊሲውንና ስትራቴጂዎቹን ሊፈትሽ ይገባል እንላለን፡፡

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር**

# Verbatim

**«ከአል ቃዒዳ ጋር ጦርነት ላይ ነን፤... እናም እነሱን ለማሸነፍ የሚጠይቀውን ሁሉ እናደርጋለን፡፡»**

ባራክ ሁሴን ኦባማ
የአሜሪካ ፕሬዚዳንት

ሰሞኑን የተከሰተውን የፀጥታ ስጋት አስመልክቶ ሐሙስ ዕለት ባደረጉት ሕዝባዊ ንግግር፡፡

**«እኛ ምርጫ ስለመሳተፍ አናወራም፡፡ መሄድ እስከምንችለው ድረስ እንሄዳለን እንጂ አንሳተፍም ብለን «ቦይኮት» አናደርግም፡፡»**

ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ
የመድረክ አመራር አባል

የባለፈው የክልልና የማሟያ ምርጫ ሁኔታ ከተደገመ ምርጫውን ለመሳተፍ ዓላማ አላችሁ ማለት ነው ወይ? ተብለው ከመሰናዘሪያ ጋዜጣ ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ከሰጡት የተወሰደ፡፡

**«ሥራችን በዚህ አገር ሚዲያ የሚገባውን ቦታና ክብር አላገኘም፤ እኛም ባህሪያችን ከመናገር ይልቅ መስራት በመሆኑ ስለጉዳዩ ብዙ አልተናገርንም፡፡»**

ወ/ሮ አዜብ መስፍን
የጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ባለቤት

እርሳቸው የሚመሩት የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ብሔራዊ የሴቶች ጥምረት በአገር ውስጥ ጋዜጦች ተገቢውን ሽፋን አለማግኘቱን አስመልክቶ የተናገሩት።

# ዜናዎች

## የመድረክ የምርጫ ምልክት ለመኢአድ ተሰጠ

## መድረክ ውሳኔውን "ኢ-ፍትሃዊ" ሲል አጣጣለው

መድረክና መኢአድ ለ2002ቱ አገራዊ ምርጫ ለመወዳደር ለምርጫ ቦርድ አቅርበውት የነበረውና በባለቤትነት ሲያወዛግባቸው የነበረው የምርጫ ምልክት ለመኢአድ መሰጠቱን ፓርቲው ለዝግጅት ክፍላችን በላከው ደብዳቤ አስታወቀ።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ለፓርቲው የዞን አመራር አባላትና በውጭ ሀገር ለሚገኙ የመኢአድ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ታህሳስ 28 ቀን 2002 በፃፈው ደብዳቤ ለግንቦቱ ብሔራዊ ምርጫ የሚወዳደርበት ከምርጫ ቦርድ የተፈቀደለት ምልክት "አንድ እጅ አራት ጣቶቹ ታጥፈው አውራ ጣት ቀጥ ብሎ እንደቆመ የሚያሳይ" መሆኑን ገልጿል። ምልክቱ ለመኢአድ መሰጠቱን አስመልክቶ ቅሬታቸውን የገለጹት የመድረኩ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ገብሩ አስራት «መወዳደርያ ምልክቱን በቅድሚያ ያስገባነው እኛ መሆናችን እየታወቀ የተወሰነው ውሳኔ ኢ-ፍትሃዊ ነው።»ካሉ በኋላ ውሳኔውን ቢቃወሙም አስቸኳይ ስብሰባ በማድረግ አማራጭ ምልክት እንደሚያቀርቡ ከዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

## «መሪው ታስሮ ወደ ምርጫ ግባ የተባለው "አንድነት" ፓርቲ ብቻ ነው»

አቶ የሺዋስ አሰፋ (የመርህ ይከበር  አስተባባሪ)

በናፍቆት ዮሴፍ

የፓርቲውን የመተዳደሪያ ደንብ ጥሰዋል በሚል ከ"አንድነት" ፓርቲ የታገዱትና "መርህ ይከበር" በሚል የሚንቀሳቀሱት ወገኖች ሶስት አላማዎችን አንግበን

በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የአንድነት አባላትን እያሳወቅን ነው ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ።

ሰሞኑን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በመዘዋወር አባላትን ለማነጋገር የፈለጉበትን ምክንያት መርህ ይከበር የሚለው ቡድን አስተባባሪ የሆኑት አቶ የሺዋስ አሰፋ ሲያስረዱ «ሁልጊዜ በየክልሉ ያሉ የአንድነት አባላት ብዙ ነገር የሚሰሙት ከስራ አስፈፃሚው እንጂ "መርህ ይከበር" ከሚሉት አይደለም፤ ስለሆነም ሊያነጋግሩን በመፈለጋቸው በየክልሉ እየተንቀሳቀስን ያለውን እውነታ አባላት እንዲያውቁት እያደረግን ነው» ብለዋል።

የሺዋስ አሰፋ፣ ስለሺ ፈይሣና ተስፋዬ ሞረዳ የተባሉት አባላት ሚዛን ፈተሪ፣ ጅማ፣ ጉሬ፣ መቱ፣ ማሻ፣ ቴፒ፣ ቦንጋና አጋሮ የሚገኙ የአንድነት አባላትን እንዳነጋገሩና በተለይም ከማሻና ከሚዛን በስተቀር በሌሎች አካባቢዎች አንድነት ቢሮ እንደሌለው ለመረዳት ችለናል ብለዋል።

በጉዳዩ ላይ ከአንድነት አባላት ጋር ለመምከር አቶ ይልቃል ጌትነትና ሰዒድ ኢብራሂም ደግሞ ደብረ ታቦር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ባህርዳርና ጉንደር እየተንቀሳቀሱ ሲሆን ገና ወደ አዲስ አበባ አለመመለሳቸውንም አቶ የሺዋስ ገልፀዋል። ወደ ደብረ ብርሃንና ሸዋ ሮቢት የተንቀሳቀሰ ሌላ ሶስተኛ ቡድን አለ ያሉት አቶ የሺዋስ «አሁንም የአንድነት አባሎች ነን። ከፓርቲው ለመባረራችን የተሰጠን ወረቀት የለም። ለጥፋታችን የተጠቀሰብን አንቀጽም የለም።» ካሉ በኋላ «እኛ በችግሩ ላይ ለመወያየትና ችግሩን ለመፍታት እስከመጨረሻው ዝግጁ ብንሆንም ሥራ አስፈጻሚው ይህን ፈጽሞ አልተቀበለውም።» ብለዋል ።

«ኅዳር 20 ቀን 2002 ዓ.ም በኢምፔሪያል ሆቴል የተጠራውን ህገ-ወጥ ጠቅላላ ጉባኤ በመቃወም ባለ ስድስት ነጥብ የአቋም መግለጫ ያወጡትን በሼካ ዞን ማሻ ከተማ የአንድነት ሰብሳቢ አቶ ብርሃኑ ኃይሉን ፓርቲው የቢሮ ኪራይና የጥበቃ ሰራተኛ ደሞዝ እንዳቋረጠባቸው ደርሰንበታል።» ያሉት አቶ የሺዋስ ሌላው ቀርቶ ጅማን በሚያህል ከተማ በኢህአዴግ ተጽዕኖ የፓርቲው ቢሮ ሲዘጋ ስራ አስፈፃሚው እንዳላወቀ ጠቁመዋል።

የአንድነት ፓርቲ ትክክለኛ መዋቅር በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች የተከፈለ ነው ያሉት አቶ የሺዋስ «ኦዲትና ቁጥጥር (ህግ ተርጓሚ) ብሔራዊ ምክር ቤት (ሕግ አውጭ) እና ስራ አስፈፃሚ የሚባሉት አሁን በፓርቲው ውስጥ አሉ ለማለት አልደፍርም። አሁን ወደ ስልጣን የመጡት አቶ ስዬ አብርሃ፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ አቶ አንዱአለም አራጌና ሌሎችም ፈጽሞ የአንድነት አባላት አይደሉም ወደ ስልጣን ሲመጡም የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ተሽሮ ነው፣ ይህን ደግሞ ሁሉም አባላት ማወቅ አለባቸው።» ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ የሺዋስ ገለፃ ከሆነ የመጨረሻ ግባቸው የፓርቲው ባለቤት የሆኑ ሰዎችን ጠርተው በፓርቲያቸው ህልውና ላይ እንዲወስኑ ማድረግ እንደሆነና ይህም በቅርቡ እልባት እንደሚያገኝ እምነታቸው እንደሆነ ገልፀው «ለዚህ አላማ ገንዘባችንን

ብቻ ሳይሆን ነፍሳችንንም አንሰስትም» ብለዋል። በተለይም «አንድነት ፓርቲ ወደ ምርጫ የሚገባው የመሪውን ጉዳይ በቅድመ ሁኔታ አስቀምጦ ነው ወይስ እንዲሁ?» በሚለው ጉዳይ ላይ ከአባላት ጋር እንመክራለን ሲሉ ገልፀዋል።

# «የኤርትራን ነገር ትውልድ የቆረጠውን ትውልድ ይቀጥለዋል»

አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ)

በናፍቆት ዮሴፍ

ላለፉት ጥቂት ወራት በአውሮፓና በአሜሪካ የሙዚቃ ዝግጅቱን ለአድናቂዎቹ ሲያቀርብ ቆይቶ ወደ አገሩ የተመለሰው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ በዓመቱ ሁለተኛውንና «ሙዚቃ ህይወቴ» የተሰኘውን ታላቅ ኮንሰርት በትናንትናው እለት በግዮን ሆቴል አቀረበ።

ይህ ኮንሰርት እጅግ የተሳካና በሰላም የተጠናቀቀ ሲሆን ብዙ ሁኔታዎቹ ከእስታዲየሙ ኮንሰርቱ ጋር ያመሳስለዋል። ለምሳሌ ያህል ህዝበ ትኬተ ለመግዛት የተሰለፈበት ርዝመት፣ መድረኩና ከመድረኩ ጀርባ የተተከሉ ነጫጭ የማረፊያ ድንኳኖች ከስታዲየሙ የሙዚቃ ድግስ ጋር በመጠኑ አመሳስሎታል።

በዕለቱ ወደ ግዮን ሆቴል ስናመራ እጅግ በርካታ የቴዲ አድናቂዎች ትኬቱን ለመግዛት ሲተረማመሱ ይታይ ነበር። ይሁንና የሁሉንም ፍላጐት ለማሟላት (ትኬት ያላገኙ እስኪያገኙ ድረስ) ቴዲ እስከ 3:20 ሰዓት ድረስ ወደ መድረክ ብቅ አላለም። እርግጥ ድምፃዊው እዛው ግቢ ውስጥ እንደነበርና ከምሽቱ 12:00 ሰዓት አካባቢ መድረክ ላይ መጥቶ መድረኩንና ሳውንድ ሲስተሙን ጐብኝቶና አረጋግጦ እንደገባ አዘጋጆቹ ገልጸዋል። ቴዲ ወደ መድረክ መጥቶ መዘፈን እስኪጀምር ድረስ ዲጄ ዊሽ እና ዲጄ መሳይ ከመድረክ በሚለቋቸው የውጭና የአገር ውስጥ ሙዚቃዎች ህዝቡ እየተዝናና ቆይቷል። በተለይም 1:30 ሰዓት ላይ ቴዲ ያልመጣው አሁንም ትኬት በመሸጥ ላይ ስለሆነ እንደሆነና በትዕግስት እንዲጠብቁ ህዝቡን በትህትና ጠየቀ። ይሁን እንጂ ህዝቡ መጮሁን ቀጥሏል። ለስለስ ያለ ሙዚቃ ከመድረክ ሲለቀቅ ሕዝቡ ይጮሃል። ሞቅ ያሉ ሙዚቃዎች በዲጄዎቹ ሲለቀቁ ታዳሚው ልቡ ይማልልና ወደ ጭፈራው ይመለሳል። በዚህ ሁኔታ እስከ 3:20 እየጮኸም እየጨፈረም ለመቆየት ተገዷል።

**የፀጥታ ሁኔታ**

ህዝቡን በማስተባበርና በስርዓት እንዲገባ በማድረግ በአዲስ አበባ ፖሊስና የፌደራል ፖሊሶች እገዛ እንዳለ ሆኖ በተጨማሪ «ET POL SECURITY» ከተባለ ድርጅት በመጡ የፀጥታ አስከባሪዎች ጥበቃውና ቁጥጥሩ የጠበቀ ሲሆን ከጋርዶቹ ጋር

ቶሎ ቶሎ በመገናኘትና የተመደቡበትን ቦታ በመቀያየር እስከመጨረሻው በንቃት ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ታይቷል ::

3:20 ሰዓት ላይ ኦሞ ከለር ጂንስ፣ ሙሉ አረንጓዴ ሆኖ ደረቱ ላይ ትንሽ መጠን ያለው ቀይና ቢጫ ያለበት ቲሸርት ፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ስኒከር ጫማና ጥቁር ጃኬት ደርቦ «አዲስ አበባ.. አስመራ» እያለ ወደ መድረክ ሲመጣ የሕዝቡን ሁኔታ ለመግለጽ ያስቸግር ነበር:: «ግባ በለው ቴዲዬን ግባ በለው፣ አበባየሆይ» እና ፉጨቱ ከህዝቡ ተደመጡ:: ቴዲም ጉንበስ ብሎ ህዝቡን በአክብሮት እጅ ነሣ:: ሰላምታ ካቀረበ በኋላ «እወዳችኋሁ እናንተስ ትወዱኛላችሁ?» ሲል ጠየቀ:: ይሄኔ ፉጨቱና ጩኸቱ የበለጠ አስተጋባ:: «አሁን ዝግጁ ናችሁ?» አለ እንደገና ህዝቡም ለጥያቄው በፉጨትና በጩኸት ምላሽ ሰጠ:: ልክ ስታዲየም እንዳደረገው «አሲዮ ቤሌማ» በሚለው ጀምሮ «አይኔ ሁልጊዜ» ሲል «ቴዲ ሁልጊዜ» ሲል ታዳሚው በተራው መለሰ::

እነዚህን ዘፈኖች ከዘፈነ በኋላ ህዝቡን ለሁለት ደቂቃ አስፈቅዶ ከነባንዱ ወደ መድረክ ጀርባ ሲሄድ ህዝቡ ተበሳጨ:: «አሁንስ አበዛው፣ ይሄን ያህል ጠብቀን እንደገና እንዴት ይገባል፣እቃ አደረገን እንዴ? ምነው የባህል ምሽት በሄድን ኖሮ»የሚሉትና የመሳሰሉት ከህዝቡ መደመጥ ጀመሩ::በዚህ ሳያበቃም ጠርሙስ፣ የሀይላንድ እቃና ሊፕስቲክ ወደ መድረኩ የተወረወረ ሲሆን ቴዲ ወደ መድረክ ከመመጣቱ በፊት ማኔጀሩ አዲስ ገሰሰ ወደ መድረክ የተወረወሩ ነገሮችን አነሳስቶ ከጨረሰ በኋላ ቴዲ ወደ መድረክ መጥቷል::

ወደ መድረክ እንደተመለሰም «አልገደድም ይበቃኛል ከእንግዲህ ልዝፈን ይበቃኛ ል ለሚጨፍር ወዳጅ የምን መለማመጥ መዝፈን እንጂ» ሲል የአድናቂዎቹን ኩርፊያ ገፈፈ:: ይህን እየዘፈነም «እዚህ ክርስቲያን አለ?» ሲል ጠየቀ:: «አዎ!» የሚል ምላሽ ተሰጠው :: «ትወዱኛላችሁ?» አሁንም «አዎ!» ተባለ:: መወደዱን በመሀላ ለማረጋገጥ የፈለገ ይመስል«እግዚአብሔርን በሉ» አለና እግዚያብሄርን የሚል ምላሽ አገኘ:: «ሙስሊሞች አላችሁ?» «አዎ!» «ትወዱኛላችሁ?» «አዎ!» «እስኪ ወላሂ በሉ» በማለት ሙስሊሙ ህብረተሰብ እንዴት እንደሚወደው አረጋገጠ:: በኋላም «እኔም እግዚአብሄርን እወዳችኋለሁ» ሲል ፍቅሩን በመሀላ ካሰረ በኋላ «የአላህ ያረቢ» ሲል ጮሆ «አንዋር መስጊድና ራጉኤል ጉረቤታሞች ናቸው:: ዋናው ፍቅር ነው:: ፍቅርም ያሸንፋል::» በማለት «ስለማይሻረው ፍቅራችን ሽመንደፈርን እዘፍነዋለሁ» አለና መዝፈኑን ቀጠለ:: ዘፍኖ ሲጨርስ እዚህ ውስጥ ገ/ሚካኤል አለ? ገ/እግዚአብሄርስ? ቶማስስ፣ መሀመድ የሚባልስ አለ? ካለ በኋላ ቴዲስ ሲል ህዝቡ ጩኸቱን በማሰማት መለሰ:: «ሁላችሁንም እወዳችኋሁ ይህ ትወልድ በፍቅር ያምናል» አለ:: ቀጥሎም «የምስራች እንነግራችኋለን በእርግጠኝነት እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ከዚህ ትውልድ ጋር ይባርካታል:: ባቢሎን ስትወድቅ ጽዮን ትነግሣለች» በማለት ሲናገር አርቲስት ሣይሆን የእምነት ሰባኪ ይመስል ነበር:: ከዛም «ምንኤላዊው ዘመን» ብሎ በመጀመር በአበባየሆይ ዘፈኑ የአድናቂዎቹን ልብ ተቆጣጠረ:: መድረኩንም ናኘበት:: ቴዲ አበባየሆይ ሲል ህዝቡ ቴዲ አለወይ አለለት ጭፈራ ጩኸት ፉጨት ... ቴዲ አሁንም እረፍት ፈለገና የባንዱንአ

ባላት ይዞ ወደ መድረክ ጀርባ ተሰወረ:: እልህ አስጨራሽ ትዕግስት፣ ግፊያና ትርምስ፣ ብርድ እና ሌሎች ፈታኝ ሁኔታዎች ነበሩ:: በኮንሰርቱ ላይ ከድርስ ነፍሰጡር በእድሜ እስከገፋ አዛውንቶች እንዲሁም በርካታ የውጭ ዜጎች የታደሙ ሲሆን ህፃናት ልጆቻቸውን ይዘው የገቡ ወላጆች በልጆቻቸው እንቅልፍ ምክንያት አቋርጠው የወጡም ነበሩ:: ግማሾቹ ደግሞ በዝግጅቱ ማብቂያ ላይ ልጆቻቸውን ከእነ እንቅልፋቸው ተሸክመው ሲወጡ ተስተውለዋል::

ከሁለተኛ የእረፍት ጊዜ በኋላ ጠቅላላ ፊቱ ከጭንቅላቱ በሚወርደው ላብ ተዘፍቆ ሲዘፍን አናቱ ላይ ውሃ የተደፋ ይመስል ነበር:: በተለይ ቦብ ማርሌ የተሰኘውንና በሬጌ ስልት የተቃኘውን ዘፈኑን ሲዘፍን (ፊውቸሪንግ) ከሚገባለት አጃቢው ጋር መድረኩን ስልት ባለው ሩጫ ተቆጣጥረውት የነበረ ሲሆን ቴዲ ዘፈኑ እንዳለቀ «በዚህ ሩጫዬ» ኃይሌን ሳልቀድመው እንደማልቀር እገምታለሁ ሲል ጣል ባደረገው ቀልድ ሕዝቡ በሳቅ እንዲያውካካ አድርጓል:: ከዚያም «ልሻገር ወይ ደራ» በሚለው ዘፈኑ ሕዝቡን ምንጃርኛ አስጨፍሯል:: ከዚህ በኋላ ልክ 5:30 ሰዓት ላይ ለሶስተኛ ጊዜ እረፍት የወጣ ሲሆን ለስድስት አስር ጉዳይ ወደ መድረክ ተመልሷል::

ከሶስተኛው እረፍት በኋላ ቴዲ ወደ መድረክ ሲመለስ መጀመሪያ ላይ ደርቦት የነበረውንና በመሀል አውልቆት የነበረውን ጃኬት መልሶ የደረበ ሲሆን «ላንባዲና» የተሰኘ ውን ዘፈኑን በመዝፈን ሶስተኛውን ክፍል ጀምሯል:: ከዚያም አላምን አለና የተሰኘውን ዘፈኑን ከተጫወተ በኋላ ከባንዱ አባላት ጋር የሆነ ነገር በሹክሹክታ አውርቶ ፊቱን ወደ ሕዝቡ በመመለስ «አሁን የምዘፍነው ከባንዱ ፈቃድ ውጭ እኔ ደስ ያለኝን ነው» አለ:: ህዝቡም በጉጉት መጠበቅ ጀመረ:: «ዘፈኑ የጥላሁንና ለጥላሁን የተዘፈነ ቢሆንም ለእኔ የተዘፈነ ይመስለኛል ኧረ እንዲያውም የእኔ ነው መሰለኝ»በማለት አርቲስት ጥላሁን በመጨረሻ የሰራውንና ሣይዘፍነው ያለፈውን «በስውር ጥበብህ ያከበርከኝ»ን ሲጀምር ህዝቡ የተለመደውን የአድናቆት ሉሉታውን አቀለጠው:: አስከትሎም የጥላሁንን «የትዝታዬ እናት» በጥሩ ሁኔታ ዘፍኖ የአድናቂዎቹን ልብ በሀሴት ሞላው:: በዚህን ጊዜ ስፓንግል (አልማዝ) የተባለችው አጃቢው ከመደበኛ ቦታዋ ወደ ቴዲ በመሄድ ከጀርባው አቅፋው አንገቷን በአንገቱ አሳልፋ ወደ ፊቱ ስትመጣ «አያችኋት ስታሳፍረኝ» አለና «ጉድ ያረገኝ አይኔ ነው» የተሰኘውን ዘፈኑን ቀጠለ በመቀጠልም «ሰው በልኬ» የተሰኘ ውን ዘፈኑን ሲዘፍን «ኧረ ሞራል እንዴት ነው ብታሰር ይሻላል እንዴ?» በማለት የአድናቂዎቹን የልብ ትርታ ለማድመጥ ሞከረ አዳመጠውም:: ህዝቡም የሰይጣን ጆሮ አይስማ በሚል አንድምታ ባለው ጨኸት «እንዳይለምድህ» በሚመስል ሉሉታ ጫወታውን እንዲቀጥል አስደረገው:: ከዚያም «ወደ ቀድሞ ዘፈናችን እስኪ እንመለስ» ካለ በኋላ አቡጊዳን ዘፍኖ «እኔ የጨነቀኝ ከአምስትና ከስድስት አመት በኋላ ምን እንደማደርገው ነው» የምትል ቀልድ ጣል በማድረግ አድናቂዎቹን በቀልዱ በማዝናናት «ልቤ መሸነፉን እንዳይነግራት ሰጋ» የሚለውን ቀጠለ እንዲሁም «ሰለሜ»ን አስከተለ::

በ«ሙዚቃ ህይወቴ» ኮንሰርቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ በቅንነትና በፍቅር ስለመኖር የሰበከ ሲሆን በተለይ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ አፅንኦት ሰጥቶ ነበር:: ይህንንም

«ትውልድ የቆረጠውን ትውልድ ይቀጥለዋል፡፡ እግዚአብሔር ሲፈቅድ አብረን እንኖራለን፣ ለማንም ብድር አንመልስም ሁሉንም በፍቅር እንወዳለን እንጂ» ካለ በኋላ «ዳህላክ ላይ ልስራ ቤቴን» የሚለውን ዘፈኑን ዘፍኗል፡፡ ገና ኮንሰርት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚያቀርብ ሲነገር አብዛኛው ሰው «ጃ ያስተሰርያል»ን ይዘፍነው ይሆን ወይስ? በሚለው ላይ ጉጉት ያሳደረ ቢሆንም በዕለቱ ግን ሕዝቡም አልጠየቀም፡፡ እርሱም አልዘፈነውም፡፡ አስተያየት ሰጪዎች ግን ውጭ አገር እንዳደረገው ቆራርጦ ከሚዘፍነውና ተጨንቆ ከሚያስጨንቀን መቅረቱ ተሻለን ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ በመጨረሻም በስታዲየም ኮንሰርቱ እንዳደረገው ሁሉ የአቡጊዳ ባንድ አባላትን በስም እየጠራ የት ተወልደው እንዳደጉ ካስተዋወቀ በኋላ ባንዱ በፍቅር የተዋቀረ መሆኑን ተናግሮ «ሁሌ ስለፍቅር እንዘፍናለን ምክንያቱም ፍቅር ድንበር የለውም አሁን ወደመሰነባበቻችን «አገሬን አልረሳም» ወደሚለው ዘፈን እንሂድ» በማለት ይህን ዘፈን ዘፍኖ ልክ ለሰባት አስር ጉዳይ ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

# በአዲስ አበባ የትራንስፖርት ችግር እጅግ ተባብሷል

## «አሽከርካሪዎች የትራንስፖርት ተገልጋዩን እያጉላሉት ነው»

**የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ መ/ቤት**

***በኤልያስ ገብሩ***

በትራንስፖርት ባለስልጣን የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ መ/ቤት በከተማ የህዝብ ትራንስፖርት ዘርፍ ብዙ ችግሮች እንዳሉ ለዝግጅት ክፍላችን ገለጸ፡፡

የቅርንጫፍ መ/ቤቱ የከተማ የሕዝብ ትራንስፖርት የኮንትራት ስምሪት አስተዳዳር አስተባባሪ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ታክሲዎች መስመር ማቆራረጥ፣ ከተመን በላይ ማስከፈል፣ መብቱን የሚጠይቅ ተገልጋይን መዝለፍና ማዋረድ፣ የጀመሩትን መንገድ ማቋረጥና ተገልጋዩን ህብረተሰብ እንዲወርድ ማስገደድ ከችግሮቹ ዋነኞቹ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ አስተባባሪው አክለውም ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል ሀይገር ባሶች ከመንገድ ስምሪት ቀጠናቸው ውጪ በመጫንና መንግስት በየወሩ የነዳጅ ምርቶች ማስተካከያ ሲያደረግ ከሚያወጣው የትራንስፖርት ታሪፍ በላይ እንደሚያስከፍሉ አስረድተዋል፡፡

ለዚህም በመ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎችና ከሕብረተሰቡ የሚመጡ ሪፖርቶችና ጥቆማዎች መሠረት ጉዳዩ አቤቱታ አቅራቢና ተበዳይ ባለበት ተጣርቶ እርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝ አስተባባሪው ተናግረዋል፡፡

በመ/ቤቱ በኩል ስላሉ ችግሮች አስተባባሪው ሲገልፁም የታክሲዎች የቀጠና ስምሪት አለመጀመሩ የራሱ የሆነ ትልቅ ችግር እንዳለው ጠቁመው የአዲስ አበባ ከተማ ከጊዜ ወደጊዜ ወደ ጐን መስፋት በእያንዳንዱ ቦታ ላይ ተገኝቶ ትክክለኛ የትራንስፖርት

ፍሰቱን ለመቆጣጠር የአቅም ማነስ ችግር እንዳለባቸው፤ የመንገዶች መጨናነቅም እንደልብ ተዘዋውሮ የማስተባበርና የመቆጣጠር ስራዎችን ለመስራት ትልቅ እንቅፋት እንደሆነባቸውና በአግባቡ አገልግሎት ሳይሰጥ ጊዜ እንደሚባክን አስረድተዋል፡፡

ተገልጋዩ ሕብረተሰብም በትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡ ዙሪያ ከፊሉ መብቱን ተጠቅሞ እያስከበረ እንደሚገኝና ከፊሉ ደግሞ መብቱን በተገቢው መንገድ እንደማያስከብር የተገለጸ ሲሆን ሕብረተሰቡ በዘርፉ ችግር ሲያጋጥመው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት እና ጥቆማ ማቅረብ ይኖርበታል ተብሏል፡፡

ዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የመ/ቤቱ የዋና ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ወጋየሁ አሰፋ የታክሲዎች የቀጠና ስምሪትን በተመለከተ ስራው ገና እየተሰራ እንደሚገኝና አሁንም ለመገናኛ ብዙሃን ምንም የሚገለጽ ነገር አለመኖሩን ተናግረዋል፡፡ ሆኖም የስራ ትግበራው ሲጀመር በዘርፉ ያሉ  አብዛኛዎቹ ችግሮች እንደሚቀርፉ እምነት እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡

# «ባለፈው ዓመት 26 ሺህ እናቶች ከእርግዝና ጋር በተያያዘ ሞተዋል»

የጤና ጥበቃ ሚ/ር

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከጥር 1-30/2002 ዓ.ም ድረስ "የጤናማ እናትነት ወር" በሚል የሚያቀርበውን ልዩ ዝግጅት በተመለከተ በትናንትናው ዕለት በጤና ጥበቃ ሚ/ር አዳራሽ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ፡፡

በዕለቱ ዶ/ር ከስተብርሃን አድማሱ የጤና ጥበቃ ሚ/ር የጤና ማበልፀግና በሽታ መከላከል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጄኔራል እና የሚ/ር መስሪያ ቤቱ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አህመድ ያሲን ስለዝግጅቱ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ይህ ለአንድ ወር ያህል የሚቀርበው ዝግጅት በአገር አቀፍ ደረጃ በወሊድ ጊዜ የሚያጋጥመውን የእናቶች ሞት ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች  ውስጥ ትልቅ ንቅናቄን መፍጠር መሆኑ የተገለፀ ሲሆን እናቶች ወደ ጤና ተቋማት በመምጣት ልጅ መውለድ እንዲችሉ በቂ የግንዛቤ ስራ እንደሚሰራም ተገልጿል፡፡

ምንም እንኳን በወሊድ ጊዜ የእናቶች ሞት ለአገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ቢመጣም ችግሩን ግን እስከአሁን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ አለመቻሉንና እ.ኤ.አ በ2000 ከ100 ሺህ ወሊድ መካከል  871 እናቶች ይሞቱ የነበረ ሲሆን በ2005 ግን የሞቱ ቁጥር 673 መድረሱን ኃላፊዎቹ ተናግረዋል፡፡ ሆኖም ባለፈው ዓመት ከእርግዝና ጋር ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆኑ ችግሮች ሳቢያ 26 ሺህ እናቶች መሞታቸውን መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡

እንዲሁም በአገራችን ከ6 ከመቶ በታች የሆነ ወሊድ ጥሩ በሆነ የጤና አሰጣጥ አገልግሎትና በቂ ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች ሲፈፀም 94 ከመቶው ግን በቤት ውስጥና በቂ ዕውቅና በሌላቸው የልምድ አዋላጆች እንደሚደረግ ተብራርቷል፡፡

የእናቶች ሞትን ከሚያስከትሉት ነገሮች ዋነኞቹ በወሊድ ወቅት ደም መፍሰስ፣ በእርግዝና ጊዜ ያለ የደም ግፊት፣ የተራዘመ ምጥ፣ ህገ ወጥ ውርጃና ንጽህናቸውን ያልጠበቁ የማዋለድ አገልግሎቶች መሆናቸውን የጤና ኦፊሰር የሆኑት አቶ ሶሬሳ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

## መጣጥፎች

# አገራዊው ፈተናና ፖለቲካዊው ጥያቄ

*ኢትዮጵያ ያለችበት ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ በአይነ ቁራኛ በሚከታተሏት አገሮች ስር እንድትሆን ጫና የሚያሳድርባት ሲሆን እነዚህ አገራት የቀጥታ ጥቃት ባይሰነዝሩባት እንኳ የትርምስ ማእከል አያደርጓትም አይባልም የሚለው ጸሃፊ ያችን ሲሳይ ገሳው አገራዊውን ፈተና የስልት ችግር ከሚንጸባረቅበት ተንኳሽ ፖለቲካችን ጋር በመቃኘት መፍትሔ ነው የሚለውን ለማመላከት ይሞክራል፡፡*

ልማት፣ ፍትህ፣ ዴሞክራሲና እኩልነት ለኢትዮጵያ ህዝቦች የማይታለፉ መብቶች ስለመሆናቸው ሲወራና ሲጻፍ ብዙ ጊዜ ሆኖታል፡፡ ይሁን እንጂ ዛሬ ኢትዮጵያ በምትገኝበት ሁኔታ ውስጥ እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በአንድ ላይ የሚያስገብር ትልቅ ጥያቄ አለ፡፡ ይህም የመኖር ወይም ያለመኖር ጥያቄ ነው፡፡ የሁላችንም ማነጣጠሪያ መሆን ያለበት ትልቁ ጥያቄም ይህ ነው፡፡ የትግላችን አስፈላጊነትና ፋይዳም በዚሁ በትልቁ አደራ ውስጥ መስተዋል ይኖርበታል፡፡

የትርምስና የውጪ ጥቃት መነሻ/መዛመቻ ሊሆን የሚችል ጥለኝነትን ማምከን ለኢትዮጵያ አንዱ በጣም ተፈላጊ ጥንካሬ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ የውስጥና የውጪ ጥልፍልፎሽ ያለበት የኢትዮ-ኤርትራ ጠበኝነት ልዩ ቦታ አለው፡፡ ዛሬ ከሶማሊያ አልፎ የመን ተሻግሯል የሚባልለት አተራማሽነት እንኳን ለኢትዮጵያ ለእነ አሜሪካም መፍትሄ ያጣ ችግር ሆኗል፡፡ የአሜሪካ ጦር አዝምቶ ቀጪነት በኢራቅና በአፍጋኒስታን ልምድ ክስርስሩ ወጥቶ የማይሞከር ሆኗል፡፡ የሶማሊያን መንግስት በጦር ደግፎ የባህር ዘራፊነትን እንኳ የመቅጨት ተግባር የሚደፍረው ያጣውም ለዚሁ ነው፡፡ የሻዕቢያን መንግስትም በወታደራዊ ኃይል ይቅርና በማዕቀብ ለማረም በፈራ ተባ የተቆየው የአሜሪካ እስራኤልንና የጸሮቻቸውን የትንቅንቅ እሳት በሰፋ ቀጣና ማጋጋም እንዳይሆን የሚያሳስብ በመሆኑ ነበር፡፡ አሁንም የተጣለው ማዕቀብ ያጥፋ ያልማ መገመት አይቻልም፡፡

እስራኤል-ከፍልስጥኤምና ከጎረቤቶቿ ጋር ያላት ጠብ በሰላም መፈታት ለምስራቅ አፍሪካ መረጋጋት የሚበጅ ቢሆንም በኦባማ ስልጣን ላይ መውጣት ይቃናል ተብሎ ተስፋ እንደተጣለበት አልሆነም። ለአፉ ድርድር እያለ የሰፈራ ይዞታ የሚያሰፋው የቀኝ አክራሪ መንግስት ፍልስጥኤማውያንን ለድርድር የምትሆን ቅንጣት ትርፍ ነፍጓቸው (በዚህም መፍትሄ ከልክሎ) ይገኛል።

ጠንከር ያለ የጌታ ጫና ያርፍበት ይሆናል ተብሎ እንዳይጠበቅም የኢራን ኃያል እየሆንኩ ነው ማለትና የኒኩሌር ባለቤት የመሆን ግስጋሴ አሜሪካና እስራኤልን ከመጻረር ባለፈ ለምዕራብ ስልጣኔም አደጋ እንዳይሆን ማስፈራቱ ጥላ ሆኗል። እናም ከፍልስጥኤም መፍትሄ ጋር ይረግባል ተብሎ ተስፋ የተደረገበት ጸረ አሜሪካንነትና ጸረ እስራኤልነት ከኢራን መቅበጥበጥ ጋር አብሮ እያደገ ነው። ይህም በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ላለው አሸባሪነት መስፋትና መቀጠል የሚመች ነው።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ጥለኝነት በሰላም መፈታት ቢችል በተቃዋሚ መወጋጋትን ያስቀራል። በሶማሊያ ውስጥ ያለውን ከጸረ ኢትዮጵያነት ጋር የተያያዘ አተራማሽነትን ያዳክማል። በዚህም ለሶማሊያ መረጋጋት የተሻለ ዕድል ከመፈጠሩ ሌላ፣ የአፍሪካን ቀንድ ያጣበበው የጥለኝነት ድባብ ይቀንሳል። ኢትዮጵያና ኤርትራ በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚኖራቸው የስትራቴጂያዊ አጋርነት፣ ተፈላጊነት፣ ተሰሚነትና ሚና ይጨምራል። ይህንን ባለብዙ ጥቅም ጥንካሬ ኢትዮጵያ እንደዋዛ ልታልፈው አይገባትም። ከዚህ ጋር አብሮ ኢትዮጵያ ከጉልበት ይልቅ የዲፕሎማሲ የድርድርና የሕግ መንገድን፣ በአገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባትንና በጋራ ጥቅም ተያይዛ ማደግን ጽኑ ፖሊሲዋ ማድረጓ በሁሉም አቅጣጫ ደህንነቷን ለማስጠበቅ የሚያስችል ሌላ ጥንካሬ ነው።

በአገር ውስጥም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች/ቡድኖች ከጠላትነት ግንኙነት ወጥተው በአገራዊ ተልእኮና ኃላፊነት ላይ መዛመዳቸው፣ የመቀዋወምና የስልጣን ትግላቸውም በትልቁ አገራዊ የጋራ ግብ ውስጥ ያጠነጠነ መሆኑ፣ የአገሪቱ ፌዴራላዊ ክልላዊ የመንግስት አውታራት ካንድ ውስን ቡድን /ቡድኖች ተቆጣጣሪነትና ከእከክልኝ ልከክልህ አሰራር ተላቀው ለሕግና ለስራ ሃላፊነት መታመንን መጎናጸፋቸው ከየትኛውም ፓርቲ የስልጣን አፍቅሮት ጋር የማይወዳደር ጥንካሬ ነው።

## አገልግል ሙሉ ጥያቄዎች

1) «ታሪካዊው»ን ድርድር እንውሰድ። ኢዴፓና አዲሱ ቅንጅት እውነተኛ ተቃዋሚዎች አይደሉም ከእነሱ ጋር በተቃዋሚ ስም አብሬ አልቀመጥም በሚለው የመድረክ አቋም መድረክን ለማጥመድ ኢህአዴግ ድርድሩን አልተጠቀመበትም? በኋላ ላይ ለምን የተወሰኑ ቡድኖች ተለይተው ተጠሩ? ለምን 92 ፓርቲዎች አልተጠሩም? የሚል ጥያቄ ሲመጣ በቅድሚያ በፓርላማ ወንበር ካላቸው ጋር ብንደራደር ይሻላል፣ ከ92 ፓርቲ ጋር በአንዴ መደራደር አስቸጋሪ ስለሆነ ነው የተባለው ሁሉ ማመካኛ አይደለም?በመሰረቱ ፈርጅ አያያዙ ከታወቀ ከ92 ከበለጡ ቡድኖችም ጋር ተሰብስቦ ስምምነት ላይ ሊደረስ

ይችላል። አራቱ ፓርቲዎች ሁለት ወር ፈጅብን ያሉትን ሰነድ መሰረት አድርገው 65 ፓርቲዎች በጥቂት ቀናት ውስጥ ስምምነቱን ሲያቀላጥፉትም አይተናል። አምስት ቡድኖችን በድርድሩ ለማስቀደም ከተባለው ሁሉ ለእውነቱ የምትቀርበው ዋናዋ ምክንያት መድረክን ከእነ ኢዴፓ ጋር ማያያዝ ነበረች። የመድረክ የሁለት በኩል ድርድር መጠየቅ መላኮሻ ሆነ። በጋራ ጉዳይ ሌላ የድርድር መንገድ የለም ሲባልም መድረክ እንደተፈለገው በወጥመድ ሙሉ ለሙሉ ገብቶ ከስነምግባር ድርድሩ ራሱን አገለለ።
የመድረክ የብቻ ድርድር እሻለሁ ማለት ለቀሪዎቹ ከድፍረት ቁጥር ነበርና መድረክ በሌለበት የሚካሄደው ድርድር ፊዛዛ እንዳይሆን ማድረግ የአራቱም ፍላጎት ሆኖ ተገጣጠመ። ለበጣ በተቀነሰበት ሁኔታ ድርድሩ ተዋበ። በምርጫ ስነምግባር ላይ ከመስማማትም ሌላ መድረክ ሊደራደርባቸው ይፈልጋቸው ከነበሩ ጥያቄዎች ጋር የተያያዙ ውስን ጉዳዮችም (እስረኛ ማስፈታትን ጨምሮ) ተድበስብሰው ታሪካዊ የስምምነት ሰነድ ወስጥ ተካተቱ። በመጨረሻም፣ አቶ መለስ ዜናዊ ተገኝተው የየድርጅቶቹን መሪዎች በታላቅ አክብሮት እየጠሩ በተናገሩበትና በተጨባበጡበት፣ ሌሎቹም በአቻ ወግ መልካም ቃላትን በተናገሩበት ታሪካዊ የፊርማ ስነስርዓት ያበሻንም የፈረንጅንም ትኩረት እንዲማርክ ሆኖ ተጠናቀቀ።

ከዚያ ወዲህ ፕሮፓጋንዳው ጥሩምባ በጥሩምባ ሆነ። ታሪካዊው የፊርማ ስነ ስርአት (መጨባበጥና ንግግሩ) በመንግስት ሚዲያው እንደጸሎት ተደጋገመ። ድርድሩ ያስገኘው መቀራረብ (በተለይ በኢህአደግና መኢአድ መሐል) የ97 ዓ.ም አይነት ሁከት እንዳይኖር የሚያስችል ስምምነት ከዋናዎቹ ተቃዋሚዎች ጋር የመደረጉ ማሳያ ሆኖ ተሞካሸ።
የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ቡድንና የአንድነት አመራር በያዙት ትግል ውስጥ ለወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ መቆም ለድጋፍ ትርፍ እንደተሰራበት ሁሉ እነመኢአድ ኢዴፓም እሷንና ሎሎች የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት እንደሚታገሉ ገለጹልን። (ወ/ት ብርቱካን ከመነገጃነት የሚተርፍ ውጤት ይደርሳት እንደሆን ወደፊት እናያለን።)
የውጪ ሚዲያዎች ምስክርነት እየተጠቀሰ ዋናዎቹ ተቃዋሚዎች እነ መኢአድ መሆናቸውን «እንድናውቅ» ፣ በዚህም የመድረክን የተቃዋሚነት ክብደት ለማቃለል ተጣረ። ታሪካዊውን ሰነድ የ65 ፓርቲ ተቋም ማስደረግንና ሕግ ሆኖ እንዲወጣ ወደ ምክር ቤተ ማስተላለፍን ሞቅ ሞቅ እያደረጉ መድረክን ሰላማዊ ደርድርን በመሸሽ፣ የምርጫ ስነምግባርን በመቃወም፣ በጸረ ዴሞክራሲና በአደገኛ ሴረኛነት የመቅረጹ ዘመቻ (መድረክም እያገዘ) ደራ። የማዲያ ዳሰሳ የተሰኘው የቲቪ ፕሮግራም ኅዳር 5 እና 6 ባቀረበው ዝግጅት «ኢህአዴግን በኃይል ማስወገድ ቢቻል እንኳ ኢህአዴግ ችግር አይፈጥርም ማለት አይደለም» የምትልን አባባል ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በነጋድራስ ጋዜጣ ላይ ያሉት ብሎ ነጥሎ በማወጣትና ዛሬ የኃይል መንገድ ተቀባይነት የለውም፣ ስልጣን በህዝብ ምርጫ ብቻ ነው ... የሚል የቅብብል አስተያየት በማስከተል የኃይል መንገድ መድረኮች ፈልገዋል ሳይል የፈለጉ ማስመሰልን እንደሚችልበት አሳይቷል።

የድርድሩን ወጤት ማራገቡም ሆነ መድረክን ማንኳሰሱ የመንግስታዊው ሚዲያ እንቅስቃሴ ከመሆን አልፎ የዋናዎቹን ተደራዳሪዎችንም አባሪነት ያገኘ ነበር:: የስነምግባር ድርድርና መድረክን በማውገዝ ሆይሆይታ የመንግስት መገናኛን አጨናንቆ (መድረክም እንደሚወገዘው አለማድረጉን በመከላከል እንዲጠመድ አድርጎ) ከስነምግባር የበለጡ ሌሎች ጉዳዮችን የማረሳሳቱ ነገር ለጊዜው ሰምሯል:: ሆይሆይታው የፈጠረው ሙቀት ግን ከላይ አልፎ ወደ ውስጥ አልገባም:: ውስጣ ውስጡ ገና ቀዝቃዛ ነው፤ ሕዝቡን አልነዘረም:: የስነምግባር ደንብ ላይ ያለፉትም ዋና ቡድኖች በስነምግባር ለመገዛት የሚጠቅም ባህርይና ቅንነት ምን ያህል እንዳላቸው ከወዲህ ለመገምገም ተችሏል::

ተከባብረን ተደማምጠን ለመደራደር ቻልን መባል ይበል የሚያሰኝ ጅምር ቢሆንም፣ በምርጫ ስነምግባር ላይ ስምምነት መደረሱ ህገ ወጥነትና ሸፍጥ ያለቀለት የሚያስመስል ጥሩንባ መፍጠሩ ገና ምን ተጨበጠና የሚያሰኝ ነው:: በፊተኛው ምርጫ ግርግርና ጉዳት የደረሰው «አሳሪ» የሆነ የስነምግባር ደንብና የጋራ መግባባት ባለመኖሩ ምክንያት ነበር? መስማማት ሌላ፣ በተግባር አክብሮ መገኘት ሌላ:: አንድ ኮሽታ ሳይሰማ የአሁኑ ምርጫ ቢከናውን እንኳ ኮሽታ አለመኖሩን ብቻ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ስኬት ማረጋገጫ ማድረግ አይቻልም::

ባለፈው የአሜሪካ ምርጫ የዴሞክራቶቹን እጩ ባራክ ኦባማን ከሶሻሊዘም፣ ከእስልምና አክራሪነትና ከጥቁር ዘረኝነት ጋር ለማያያዝ ተሞክሮ ነበር:: ኦባማ ስልጣን ከያዙ በኋላ ያኔ ያልሆነ ስም ሲሰጡት የነበሩት ሰዎች ኦባማ ያጠቁናል ብለው አልፈሩም:: አሁንም በስልጣን ላይ እያለ፣ ውዱን የግል ኢንሹራንስ መጠቀም የማይችለውን የሕብረተሰብ ክፍል የሚሸፍን መንግስታዊ የህክምና ዋስትና ይኑር የሚል (የግል ኢንሹራንሶችን የትርፍ ጥቅም የሚነካ) የማምጣቱ የተነሳበት ተቃውሞ ፍርሃት የሌለበት (ከሂትለርና ከስታሊን ጋር እስከ ማመሰል የተስፈነጠረ) ነበር:: በእኛ አገር ውስጥ የዚህ አይነት የከረረ ቅዋሜ ውስጥ ዛሬ እገባለሁ የሚል ቢኖር በመንግስት እጠቃለሁ በሚል ፍርሃት ሲቃዥ ማደሩ የማይቀር ነው:: ሌላውም ሰው ይሰጋለታል:: ለምን? ከገዢው ፓርቲ ጋር ለተጣመደ ፓርቲ ጽህፈት ቤት ወይም አዳራሽ ለማከራየት መፍራትና እምቢ ማለት የሚያጋጥመው ለምን? ገዥውን ፓርቲ ብቃረን በሆነ መንገድ ችግር ሊደርስብኝ ይችላል የሚል ፍርሃትን ምን አመጣው? የተቃዋሚ የሀሰት ወሬ አሳስቶ? መንግስታዊ የፀጥታ ኃይሉ ለየትኛውም ቡድን ታማኝ አለመሆኑን ገና ሰው ስላላወቀ? በአንድነት አስቸኳይ ጉባኤ ላይ ፀጥታ ለማስከበር እንዲገኝ የተጠየቀው ፖሊስ ተገኝቶ (በጉባኤ የሚሳተፍና የማይሳተፍ የሚል የድርጅት ውዝግብ ውስጥ ሳይገባ) ድብድብና ጥፋት እንዳይደርስ እስከመጨረሻው መቆየት ነበረበት:: ይህን ኃላፊነት ለምን አልተወጣም?

አራቱ ተደራዳሪ ድርጅቶች ከስነምግባር ደንብ ሌላ የሕዝቡን ውሳኔ በመጻረር በመንግስት ስልጣን ላይ ለመቆየትም ሆነ ከሕገ መንግስታዊው ስርዓት ውጪ ስልጣን ላይ የመውጣት እንቅስቃሴ እንደሚቃወሙ፤ የምርጫ ቦርድ፣ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግና

የዳኝነት ሥርአቱ ከፓርቲዎች ነጻና ገለልተኛ ሆነው ማገልገል እንዳለባቸው፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይልና ተጠባባቂ ጦርም ሆነ የአካባቢ ታጣቂዎች ወራሪን ለመመከተና ዳር ድንበርን ለማስከበር ሲባል የተደራጁና ሰራዊቱ ከወገናዊነት ነጻ እንዲሆን የተደነገገ መሆኑን እንደሚገነዘቡ የሚገልጽ መግባቢያ አስቀምጠዋል፡፡

መሆን/መደረግ ስላለበት፣ በህግ ስለተደነገገውና በጋራ ስለሚቃወሙት ነገር መስማማት የማይናቅ ቢሆንም፣ ዋናው ጉዳይ መሆን ያለበትንና የተደነገገውን እንዳይሆን የሚያደርጉ ችግሮች መኖር አለመኖራቸውን መለየት፣ ካሉም ችግርነታቸውን ለማስወገድ የሚከናወኑ ተግባራትን ማስቀመጥና ሂደቱን መጀመር ነው፡፡

ሕጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ከፖለቲካ ሌላ ኃይል የላቸውም፡፡ ህግን ቢዳፈሩና በጉልበት ስልጣን እንይዛለን ለማለት ቢሞክሩ የሕግና የጸጥታው አካል ይቆነጥጣቸዋል፡፡ በገዢነት ላይ የሚገኘው ፓርቲስ ህግን ልተላለፍ ቢልም በሕግ መከልከል ይቻላል? የመንግስት አምድ (state) የሆነ ያህል ነው፡፡

አፄ ኃይለስላሴ ለማይከስስና ከሰማይ ለተሰጠ ፍጹማዊ ገዢነት መሳሪያ የሆነውን አውታር መንግስት ገነቡ፡፡ የደርጉ መንግስቱ ኃ/ማርያም የራሱን ተመላኪነትና ተቆጣጣሪነት በኢሠፓ መረቡ አማካይነት በሕብረተሰቡ ላይ አዋቀረ፡፡ ኢህአዴግ መጥቶም በግል/በፓርቲ አምሳል የመቅረጽ ታሪክን አላስቆመም፡፡ ገና ወደ ስልጣን እንደመጣ የቅልበሳ አደጋ በማይኖርበት አኳኋን የነበረውን የአገዛዝ (የደህንነትና የጦር አውታር) አፍርሶ የራሱን ታጋዮች አከርካሪ ያደረገ ግንባታ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያካሄደው ለውጥ ከፓርቲ ነፃ የሆነ መንግስታዊ የአገዛዝ አውታርን ተጨባጭ እንዳያደርግ ሰንክሎ ይዞታል፡፡ የአገሪቱ ደህንነትና መከላከያ ዛሬም ከህወሃት/ኢህአዴግ ጋር የተሳሰረ አመጣጡን አልጨረሰም፡፡ ይህ ሊካድ አይችልም፡፡ ኢህአዴግ በአንጃ መከፋፈል ደርሶበት በነበረ ጊዜ፣ ሰራዊቱ አንጃ ለይቶ ውጊያ እንዳይመጣ ከፍተኛ ስጋት የነበረው የሪፖርተር ጋዜጣም ሰራዊቱን ከክፍፍል ለማራቅ ያለማሰለስ ሲታገል የነበረው በዚህ ሀቅ ምክንያት ነበር፡፡ የደደቢት እግር ኳስ ክበብን በመከላከያ ተደጋፊ እንዲሆን ያስቻለውም ቦታው ካለፈው የህወሃት / ኢህአዴግ የተጋድሎ ታሪክ ጋር ያለው የጀርባ ቁርኝት ነው፡፡

ገዥው ፓርቲ እቅድና ፖሊሲውን በንቃት የሚያስፈጽም የሰው ኃይል ለማብዛት ያደረገውም ትግል የመንግስታዊ መስሪያ ቤቶችን አውታራት በአባላትና በካድሬዎቹ እንዲጥለቀለቅ እያደረገው ይገኛል፡፡ የመንግስታዊ አካላት ለኢህአዴግ ማጋደልም በግልጽ የሚታይ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከኢህአዴግ የተሸካከረ ጉዞውና እንቅስቃሴው መሰናክል ቢበዛበት፣ የተለሳለሰ ፓርቲ መሰናክል ቢቀልለት አያስደንቅም፡፡

የመንግስት ጋዜጦች የራዲዮና የቴሌቪዥን ስርጭቶች ባመዛኙ የገዢዎቹን ፍላጎት በማገልገል የተዋጡ ናቸው፡፡ ልማታዊ ጋዜጠኛነት ስሙ እንጂ ተግባሩ የለም፡፡ ልማታዊ ጋዜጠኛነት «ይህ ተገነባ ያ ለማ» የሚል አዳናቂ ፕሮግራሞችን ማጉረፍ ማለት አይደለም፡፡ የመልካም ስራ መደነቅ ሳይረሳ ልማትን፣ መልካም አስተዳደርን፣ ፍትህንና የሰብአዊ መብት አያያዝን የሚያጎሳቁሉ የባህል፣ የአሰራርና የተግባር

ብልሽቶችን በየትኛውም የመንግስትና የግል ተቋም ውስጥ እያሳደዱ ሁለገብ ልማትን መታደግ ነው:: ይህ በመንግስት መገናኛ ብዙኃን ውስጥ ተጨባጭ ሊሆን የሚችለው የመንግስትን አቋምና ፖሊሲ ከማክበርና እንቅስቃሴውን ከማሳወቅ ባሻገር ጋዜጠኛው የገዢው ፓርቲ አዘጥዛጭ መሆን ሳይጠበቅበት ሕብረተሰቡን እንዲያገለግል ነፃነቱ ሲኖረው ነው::

የኢህአዴግ መንግስት ግን ከግል መገናኛ ብዙኃን የሚፈልገውን ነባራዊነትና ሚዛናዊነት በመንግስታዊ የመገናኛ አውታሮች ላይ ተፈጻሚ አያደረገውም:: ለገዥው ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ የመጥቀምና የመጉዳት ሚዛን በመንግስት መገናኛ ላይ የሚተላለፉና የማይተላለፉ / ስፊ ሽፋን የሚሰጣቸውና የማይሰጣቸው ሀቆችን፣ መረጃዎችንና ክንዋኔዎችን እየወሰነ ነው:: ለገዢው ፓርቲና አጋሮች ይጠቅማል የተባለ ይናኛል:: አይበጅም ወይም ተቃዋሚን ይጠቅማል የሚባል ይለባበሳል ወይም ይታፈናል:: ገዢው ፓርቲ የወደደው ይሞካሻል፤ የጠመደው ደግሞ ይጥላላል:: በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሕዝብ አስተያየት እየተባሉ የሚቀርቡ አስተያየቶች እንኳ ከሞላ ጎደል የገዢው ፓርቲ ፍላጎትን የሚያጫፍሩ ናቸው:: የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና አጋሮች እንቅስቃሴና ድርጅታዊ በዓል የዜናና የዘገባ ሽፋን ሲትረፈረፍለት የተቃዋሚዎች ግን በአብዛኛው ከቅምሻ ታህል ያለፈ ቦታ አይሰጣቸዋውም:: ከተሰጠም ለማሳጣት የሚመች ሲሆን ነው:: ዘጠና ምናምን ፓርቲ ባለበት ሁኔታ ስለፓርቲዎች ሁሉ እንዘግብ ከተባለ ለሌላ የልማትና የፖሊስ ሰራ ጊዜም አይኖር ሲባል የተሰማው ማንንም የማያሳምን ሰበብ ነው:: መንግስታዊው መገናኛ ዛሬ እመርታዊ ስፋት አግኝቶ ሳለ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን በተናጠልም ሆነ በቡድን እየቀረቡ (በቃለ መጠይቅ/በውይይት) ማን ምን እንደሆነ ሕዝብ ሊያውቅ የሚችልበት አንድም ፕሮግራም እስከ ዛሬ የለም:: የተሞከሩም ረዥም እድሜ አላገኙም:: ጋዜጠኞቹ ገዢውን በመካብና የማይታመን ተቃዋሚን በማሳጣት መስመር ውስጥ የመጓዝ ችግር ያለባቸው መሆኑ የዚያ አይነትን ፕሮግራም ከጅምሩ የሚያከሽፍ ነው::

ታዲያ ሌላ ሌላውን የመንግስት ዘርፍ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ዘመም እንዲሆን አድርጎ ሳለ የምርጫ አስፈፃሚ አካላቱን ይተዋል ብለን እንድናምን የሚያደርገን ምንድን ነው? እስከዛሬ በኢትዮጵያ በተካሄዱት ምርጫዎች ኢህአዴግና አጋሮቹ ከሞላ ጎደል አሸናፊ እየሆኑ ያሉት በፓለቲካ ተቀባይነት የሚስተካከላቸው ተቃዋሚ ታጥቶ ከእንከን በጸዳ የምርጫ ሂደት ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ «ያለጥርጥር» ብሎ መመለስ እንኳን ሌላው ኢህአዴጎችስ ይችላሉ?

የምርጫ አስፈጻሚዎችና ታዛቢዎች የገዢ ፓርቲ አባል ወይም ደጋፊ ላለመሆናቸው መታወቂያ አለመያዛቸው መተማመኛ አይሆንም:: መታወቂያ የሌለውን ደጋፊ ለመለየት ቢበዛ በተግባራዊ ህይወቱ ውስጥ ያለውን ሚዛናዊነትና ለኃላፊነት የመታመን ሁኔታ መገምገም ነው የሚቻለው:: የለየለት ደጋፊ ባይኮንም የገዢው ፓርቲ መንሰራፋት፣ በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚቹ መካከል ያለው መከባበርና ተቃዋሚዎችና ደጋፊዎቻቸው ላይ ከዚህ ቀደም የደረሰውና ደረሰብን የሚሉት ጥቃትና እንግልትም

ሊያስደገድግ የሚችል ነው:: በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚዎች መካከል የቆየው በጠላትነት መጠማመድ ቢፈርስ ግን የወገኖች ክረት ይረግባል:: በፍርሃት የድምጽ ማጭበርበር አባሪ የመሆንን ዕድል ይቀንሳል:: ያለአድሎ አደራን የሚወጡ የምርጫ አስፈጻሚዋችን ለማግኘትና ለመምረጥ ብሎም ብልሽት ያነሰበት ምርጫ ለማካሄድ (ፓርቲዎች ለመሸፈጥ እየሞከሩም ቢሆን) ያመቻል::

ያም ሆነ ይህ ግን አሁን ባለንበት ደረጃ፣ ገዢው ፓርቲ ነጻ፣ዴሞክራሲያዊ ምርጫንና ውጤቱን ለማክበር የራሱ ፍላጎትና በተቃውሞ እንዳልወድቅ የሚል ስጋት ካላስገደደው በቀር በኢትዮጵያ መንግስት ውስጥ ያለው አተካከል ቢፋጅ በማንኪያ ቢበርድ በእጅ ጥቅሻ ለመግዛት የሚያስችል ነው:: ስለዚህ የተጀመረው ድርድርና መግባባት ለሕዝብ የሚተርፍ ቁምነገር የሚኖረው፣ ገዢው ፓርቲ የሕዝብ ውሳኔን በመጻረር በመንግስት ስልጣን ላይ ላለመቆየትና ህገወጥ የስልጣን አመጣጥንም ላለመቀበል ሲስማማ ከልቡ ህዝቡን ከመቆጣጠር ፈንታ በህዝብ ቁጥጥር ውስጥ ለማደር መልካም ፈቃደኛ ከሆነና ከመንግስት አውታሩ ውስጥ ያለውን የኢህአዴግ አዘንባይነትም ወደፊት ለማቃናት ዝግጁ ከሆነ ነው:: የኢህአዴግ ፍላጎት እንደዚያ ይሆን? ወደፊት ይታያል፤ «ሽል ከሆነም ይወጣል እህል ከሆነም ይጠፋል» እንዲሉ::

2) እነኢዴፓና መኢአድን ተስፋቸውንና የወደፊት ጥረታቸው ከዚህ አይነት መሻሻል (ለውጥ) ጋር የተገናኘ ነው? ከኢህአዴግ ጋር የመቀራረብ እርምጃ ያሳዩት የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ እና እድገትን ጥቅም ከመድረክ ይበልጥ አርቀው ተመልክተው ነው? መድረክ ለብቻዬ ካልተደራደርኩ ማለቱና የኢህአዴግ ጎራ (ብሎክ) አድርጎ መፈረጁ ተንኳሽ ቢሆንም የትንኮሳ መምጣት ወደ መናቆር መግባትን ትክክል ያደርጋል? ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የሚበጀው ከመድረክ ጋር የመጠፋፋት ግጥሚያ መያዝ ወይስ ገና ግንኙነት ውስጥ ለመግባት መጣር? የተያዘው ንቁሪያ እውን የድጋፍ ትርፍ እያስገኘ ወይስ ትዝብት ወሱጥ እየጣለ? ትልቅ ፓርቲ እኔ ነኝ በመባባል ፖለቲካ ትንሽነት ይወገዳል? ችግሮች እየተቃለሉ ነው፣ ከአሁን በኋላ ያለችግር ለመስራት ይቻላል እየተባለ በድል ስሜት ሲነገር ተሰምቷል:: የምናወራው ለራስ ድርጅት ታህል ስለተገኘች ጉርሻዊ ምቹነት ነው ወይስ ስለአጠቃላዩ? ከራስ ውጪ ባለ በማንኛወም (ባለጋራም የሆነም ያልሆነ) ሕጋዊ ደርጅት ላይ የሚካሄድን አፈና ሳይቃወሙና ሳይታገሉ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ መታገልና እየታገልኩ ነው ማለት ይቻላል? ዛሬ ለራስ ድርጅት የተገኘ ያፈና ቅለት እድል ለሌላውም እንዲተርፍ እስካልታገሉ ድረስስ ዛሬ እነመድረክ (በቅርቡም ኢፍዴኃግ የሚባል ድርጅት) ደረሰብን ያሉት እንግልት ነግ በራስ ላይ አለመድረሱን ማስቀረት ይቻላል?

ከጥንታዊው ዴሞክራሲ ወዲህ በዓለም ውስጥ ህያው ሆኖ ያለ ዴሞክራሲ የከበርቴው ዴሞክራሲ ነው:: የከበርቴውን ሙዚየም እከተላለሁ ብሎ የተነሳው «ሶሻሊስት ዲሞክራሲ» ከሽፎ እራሱ ከሙዚየሙ ገብቷል:: ዛሬ ከከበርቴ ዴሞክራሲ ውጪ የሆነው ሌላ የዴሞክራሲ ስርአት የለም:: በከበርቴ ዴሞክራሲ ክልል ውስጥ ፓርቲዎች ዝርዝር የአላማና የትኩረት ልዩነቶች እንዳላቸው ሁሉ ከፓርላማ ወንበር ጋር

በተያያዘ የፓርቲዎች ስልጣን አቀማመርና በመሳሰሉት ላይ ልዩነት አላቸው:: ከእነዚሁ ልዩነቶች ጋር ግንኙነት ባለው መልክ የዴሞክራሲውም አደረጃጀት ውሱን ልዩነቶች ይታዩበታል:: አንዳንዶቹ በከበርቴው ጥቅም ላይ ይበልጡን ሲጣበቡ፣ ከእነዚህ ፈንጠር ብለው በከበርቴውና በድሃው መካከል ያለውን ርቀት ማጥበብ የሚሹና ከፓርቲዎች ጨዋታ ባሻገር ሰፊ አሳታፊነት ያለውን የዴሞክራሲ አወቃቀር የሚመርጡ አሉ::

በሊብራል ዴሞክራሲ ውስጥ የምናገኛቸው «ወግ አጥባቂ»፣ «ሶሻል ዴሞክራሲያዊ»፣ «ሶሻሊስት» ወዘተ የሚባሉ ፓርቲዎች ሁሉ የዚህ አይነት (በንድ የዴሞክራሲ ቤት ውስጥ ያሉ) ልዩነቶች መገለጫ ናቸው:: ምእራብ አውሮፓ ውስጥ ወግ አጥባቂው ከሶሻል ዲሞክራሲ ፓርቲ ጋር መንግስት ሲመራና የሶሻሊስት ፓርቲ በሊበራል ዴሞክራሲ ውስጥ ተወዳድሮና አሸንፎ መንግስት ላይ ሲወጣ ማየት አስገራሚ የማይሆነውም ለዚህ ነው:: አቶ ልደቱ አያሌው ታዲያ መድረክን የማይቻል ግጥምጥም አድርገው «የትም የማያደርስ ፈረስ» ያሉት፣ ይህንን የፖለቲካ ሀሁ ገና አያውቁ ሆነው ወይስ የመድረክን ድጋፍና ጥምረት የጎዱ መስሏቸው?

«ሊብራል» «ሶሻሊስት» «ሶሻል ዴሞክራት» ነን ያሉ ቡድኖች መጣመር ይቅርና በሂደት በሚፈጠር የአስተሳሰብ ሽግሽግ ወደ አንድ ፓርቲ የመጠቃለል እድልም ይኖራቸዋል:: «መሬት ይሸጥ»/ «አይሸጥ» የሚሉ አስተሳሰቦች ባንድ ፓርቲ ውስጥ ሳይቀር ሊገኙ፣ እየተከራከሩና የጋራ መገናኛ እየፈለጉ ሊሰሩ ይችላሉ:: በአገራችን አሉ የሚባሉት በዘጠና የሚቆጠሩ ፓርቲዎችም ቢሆን የብሔረሰብ ቆዳን ያለፈ ፈርጅ ሲገቡ ከእጅ ጣት ቁጥር በማይበልጥ ቡድን ውስጥ እንደሚጠቃለሉ ይገመታል:: ልደቱ መድረክ ውስጥ አለ የሚሉት «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የ«አረና»ዎችንና የስዬን የፖለቲካ ጀርባ ከማስታወስና (በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ላይ የሰነዘሩትን ትችት እንዳልነበረ አድርጎ) የኢህአዴግ ብጤ ለማስመሰል ይጠቅም እንደሆነ እንጂ አብሮ የማያስኬድ ተፃራሪነትን አያመለክትም:: መጠማመዱን ሊጥሉት ቢፈቅዱ፣ በአንድ መለስተኛ የጋራ ፕሮግራም ላይ መስራት እንኳን መድረክ ውስጥ ላሉት ኢህአዴግ፣ ኢዴፓና መኢአድ ተጨምረውም የማይቻል አይደለም::

*መድረክስ? የመደራጀትና የመሰብሰብ መብቶችን፣ የህግ መከበርንና የመሳሰሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ይዞ ለመደራደር መሞከሩ አበጀህ ያሰኛል:: ግን ለማንኛውም ጥምዝምዝና ውጣ ውረድ ራሱን አዘጋጅቶ ነበር? ወይስ በድንገተኛ ሁኔታዎች ተላግቷል? ለመደራደር የጠየቅነው ከኢህአዴግ ጋር ነው፣ ከእኛ ጋር ለመደራደር አልፈቀደም፣ ዋናው ጉዳይ ስነምግባር አይደለም፣ ስነምግባርን በተመለከተ ችግር የለብንም፣ አጋር አገሮች ለእኛም ለኢህአዴግም የሰጡት አንድ አይነት ሰነድ ሆኖ ሳለ እነሱ አስተማሪ እኛ ተማሪ እንድንሆን ተፈለገ፣ ምርጫ ቦርድ ሰነዱን የራሱ አድርጎ ስብሰባውን የሚመራ ከሆነ እንሳተፋለን፣ የምርጫ ደንብ ማርቀቅ ያለበት ምርጫ ቦርድ ነው፣ አራቱ ፓርቲዎች ደንብ ማርቀቃቸው ህገወጥ ነው ወዘተ ሲባል የነበረው ሁሉ እውን የሚያዋጣ መከራከሪያ ነበር?* የፓርቲዎቹን ህግ የማርቀቅ ክንዋኔ ህገወጥ ነው ከማለት ይልቅ እንዲያውም በተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ትኩረት ሊያገኙ ይገባቸዋል

የሚባሉ ጉዳዮችን ፓርቲዎች ተጋግዘው የሕግ ረቂቅ ሃሳብ በማመንጨትና በማቅረብ ክብደት ለመፍጠር ጥሩ ጅምር ነው ብሎ ማሞገስ የተገባ አልነበረም?

የመድረክ ከምርጫ ስነምግባር ድርድር የማፈንገጥ ትክክልነት የሚለካውስ ኢህአዴግ ሌላ የድርድር ምርጫ ለማድረግ በመንፈጉ ወይም ሌሎች ፓርቲዎች በመጨመራቸው ወይም የማይጥም ድርድርን ረግጦ መውጣት መብት በመሆኑ ነው? ወይስ የሚወሰደው እርምጃ ሊያስገኝ የሚችለውን ጉዳትና ጥቅም በማመዛዘን? የፖለቲካ ትግል እንደ ፖለቲካዊ የክብደት ሚዛን፣ እንደ ፖለቲካ አየሩ ገርነትና ክፋት ፈግፈግ ራመድ /ጎብደድ ለጠጥ የሚባልበት እንጂ ደረትን ገልብጦ አንጼ ከሆነ ይሁን የሚባልበት አይደለም።

ባራክ ኦባማ በምርጫ ዘመቻው ጊዜ እንደ ኢራቁ ጦርነት የአፍጋኒስታንን ተቃውሞ ቢሆን ኖሮ ራሱን በራሱ ተሸናፊ ከማድረግም አልፎ በአሜሪካዊነቱ ላይ ጥያቄ ያስነሳ ነበር። በወታደራዊ መንገድ አልቃይዳንና ታሊባንን አጠናቅቃለሁ ብሎ አመነም አላመነም ከአሜሪካ ደህንነትና ከመስከረም 11/2001ዱ የኒውዮርክ መንታ ህንፃዎች ጥቃት ጋር ቀጥታ ተያያዥነት የነበረውን የአፍጋኒስታንን ጦርነት መደገፍና የምርጫ ዘመቻው አካል ማድረግ ግዱ ነበር።

ስልጣን ላይ ከወጣ ወዲያ ከኢራቅ ጦር ኃይል አዛውሮ ሞከረ፤ ተስፋ የሚሰጥ ወጤት አልተገኘም። ጭራሽ ተጨማሪ አርባ ሺህ ወታደር ካልተላከ የሚል ጥያቄ መጣበት። አሜሪካ የምትገኝበት ብዙ ሰውን ስራ ያሳጣ የቀውስ ኢኮኖሚ፣ የባጀት ጉድለቷና የአንድ ዘማች ወጪ በዓመት አንድ ሚሊዮን ዶላር የሚፈጅ መሆኑ የእሺታ መልስን አያግዝም። እምቢ ማለትም ለፖለቲካው የሚያዋጣ አይደለም። በጥያቄው ላይ ማሰብና መምከሩ ጊዜ በተወሰደ ቁጥር የአሜሪካንን ደህንነት ለአደጋ አጋለጠ በሚል ነቀፌታ አካልበው የሚፈልጉትን ለማስደረግ ሪፐብሊካኖች ራስ ምታት ሆነው ነበር። ኦባማ ግን ሳይበገር 30 ሺ ሰራዊት ለመላክ እሺ ከማለት ጋር ታሊባንን በማዳከምና የአፍጋኒስታንን መንግስት ጣጣ ቻይ እንዲሆን በማብቃት ላይ በተገደበ መውጫውን ሊያበጅ በቃ። የዚህ አይነቱ በጉንተላዎች ሳይንተከተኩና ሳይዝረከረኩ ከቅድመ-ስልጣን እስከ ስልጣን ድረስ ጊዜና ቦታ እየጠበቁ የመራመድ ብልህነት ለእኛ የፖለቲካ ሰዎች ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ይመስለኛል።

ኢህአዴግ ሌላ የድርድር መንገድ አልሰጥም ብሎት መድረክ ሲወጣ፣ ላነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ለማስገኘት / ኢህአዴግን ለመጫን ምን አማራጭ አለኝ ብሎ? የሕዝብ ድጋፍን በተለያየ ሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ አነቃንቆ ኢህአዴግን ወደ እሺታ ለማምጣት የሚያስችል የድርጅትና የፖለቲካ አቅም ዛሬ አለው? በሰፊ ድጋፍ አስጨንቆ ለመደራደርና ውጤት ለማምጣት የሚሻ ኃይልስ የኢትዮጵያ አጋርነት ቡድን ከሚባሉ ኤምባሲዎች ጋር ተፍተልትሎ በኋላ ተገቢ ነገር አላደረጉም ብሎ ከመማረር ይልቅ የድርድር ጥያቄዎቹን ቀደም ብሎ ይፋ በማድረግ የፓርቲዎችንና የሕዝብን ድጋፍ በዙሪያው ለማሰባሰብ መስራት አልነበረበትም? ኢህአዴግ በተናጠል አልደራደርም ብሎኛ ል ብሎ የስነምግባሩን የድርድር መድረክ ይናቅ እንጂ ለእነመኢአድና ኢህአዴግ «ፍቅር»

አጋዥ ከመሆንና እንደተለመደው እንዲህ ሆንኩ እያሉ ከማማረርና ብቻውን ከመጮህ (ኃይሉ ሻውል እንዳሉት ከ«ለቅሶ ፖለቲካ») በቀር ምን አመጣ? ተነጥሎ በነቀፌታ ለመዋከብ እራሱን አላመቻቸም? ከዚህ ይልቅ በስነምግባሩ ድርድር ውስጥ ጊዜና ሁኔታን እያዩ ተጠንቅቆ መራመድ የተሻለ አትራፊ አያደርግም ነበር? በስነ-ምግባር ድርድሩ ውስጥ ሆኖ በሌሎች ሰነዶችም ሆነ ጉዳዮች ላይ እንደራደር ማለት የእነ መኢአድና ኢዴፓን አጋዥነት ለማግኘትም ዕድል የሚሰጥ ነበር፡፡ ሶስቱ ቡድኖች የኢህአዴግ ጭፍሮች (ከዚህ ቀደም መኢአድ በዚህ ሲታማ አልሰማንም) ሆነውም ከሆነ፣ ድርድሩ ዞሮ ዞሮ ከኢህአዴግ ጋር መሆኑን የእነሱ መጨመር የሚለውጠው አልነበረም፡፡ በድርድሩ ውስጥ የሚጨዋቱት ሚና ድርድርን የማወላከፍ የሚሆን ከሆነም በስተኋላ ለሕዝብ እዩልኝ ስሙልኝ ብሎ ማጋለጥ ይቻል ነበር፡፡ በማጋለጥም ጊዜ ቢሆን በዙሪያው ሰፊ ድጋፍ የመፍጠር አላማውን የማይዘነጋ ድርጅት ገፍታሪ እንዳይሆን ይጠነቀቃልና በሎክ ተፈጠረ ለማለት አይፈጥንም፡፡ ተንኮልና ውንጀላ ቢወረወርበት እንኳ በወርዋሪው ደረጃ ወርዶ ተመሳሳይ ምላሽ ከመስጠት ፈንታ የአገርን እውነት ከጎኑ ያደረገ ጨዋታ ትችት ላይ ያተኩራል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ኩነኔ እንዳይሆንበት ሳይሆን የድጋፍ ፍላጎቱ ከድርጅቶች አመራር አካላት አልፎ በአባሎችና በደጋፊዎች ዘንድ መደመጥና መከበርን እስከማግኘት የሚርቅ ስለሚሆን ነው፡፡

ለገዢው ፓርቲ አድናቆትና ምስጋናን እያሸከሙም ቢሆን የስነምግባሩን የድርድር አጋጣሚ ከኢህአዴግ ጋር መለሳለሻያና መሰናክል ጋብ ያለበት ሁኔታ ውስጥ መግቢያ አድርጎ ለመጠቀም ማቀድ፣ እንዳቀዱትም ያገኙዋትን የተሻለች ሁኔታ ብታንስም በንቁሪያ ሳያስነጥቁ ድርጅትን ለማስፋፊያና ከሕዝብ ጋር ለመያያዢያ መጠቀም የአርቆ አስተዋይ ሙያ ነው፡፡ የምርጫ ጊዜ ገጽታን ለማሳመር ተብሎ የተገኘ ለስላሳ ሁኔታ እንኳ ቢሆን አንዴ እጅ የገባን ነገር (ተንከባክቦ ለማቆየት የሚጥር እስካለ ድረስ) መልሶ ወስዶ የቀድሞውን ጎርባጣ ሁኔታ ማስፈን ቀላል አይሆንም፡፡ መልካሙን እያቆዩና እያሰፉ ከመሄድ የሚጠቀሙት ደግሞ ሁሉም ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ህዝብ ነው፡፡

## «ከአንጀት ካለቀሱ ... አይገድም»

ሐሳቤን ላጠቃል፡፡ በሜዳው ውስጥ ኢህአዴግ ገዘፎ እያለም ቢሆን ለእነኢዴፓና ለመኢአድ ብቻ ሳይሆን ለእነመድረክም ከኢህአዴግ ጋር መቀራረባቸው ቢጠቅም እንጂ ጉዳት የለውም፡፡ ይህን የምለው መቀራረቡ ያንድ ፓርቲ ተቆጣጣሪነትን ተዛነፍ ለማስተካከልና ነጻ ፍትኃዊ ምርጫን ምሰሶው ወደአደረገ ዲሞክራሲ ለመዝለቅ መንደርደሪያ የመሆን ጥቅሙን በማስተዋል ነው፡፡ መቀራረብ ሲባል በባዶ እጅ ሳይሆን የተጠቀሰው ውጤት ላይ የሚያደርስ ሂደት ውስጥ መግባት ማለት ነው፡፡ የእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ችግራችን ሰነድ ከመፈራረም የዘለለ የማሻሻያ ለውጥን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ለውጥ መምጣት ጠላትና ወዳጅ ተባብሎ በጎራ ከመጠዛጠዝ ይልቅ ተቀራርቦ በመረዳዳት መስራት የተሻለ ይበጃል፡፡ ከዚያ አኳያ ሰፋ ያለ የመግባባት መንግስት ለማደራጀት ቢታሰብም እሰየው ነው፡፡

ይህ ጉዳይ ኬንያና ዚምባቡዌ ውስጥ ከደረሰው ሁኔታ ጋር የተያያዘ ውዥንብር ስላለ አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት ተገቢ ይሆናል:: የኬኒያና የዚምባቡዌ አይነት ቀውስ ከመጣ ህገመንግስትም አይመክተውም:: የዚያ አይነት ቀውስና የቀውስ መንግስት በአገራችን አያምጣብን:: በምርጫ የተሸነፈ ፓርቲ አሸናፊውን ስልጣን ካላጋራኸኝ ዘራፍ ሞቼ እገኛለሁ ቢል ህገወጥ መሆኑ የሚያነጋግር አይደለም:: በህገመንግስቱ አንቀጽ 56 እና 60(2) መሰረት የጥምር መንግስት አመጣጥ በጥምር አብላጫ ድምጽ ማግኘትን መሰረት ያደረገ ነው:: አብላጫ ድምጽ ያገኘ ቡድን / ቡድኖች የተበለጠውን ያሳተፈ መንግስት ለማቋቋም ቢፈልግ/ቢፈልጉ ግን መብት ነው:: ከዚያ አኳያ ኢህአዴግ ሁሉ በእጁ እንደመሆኑ ከቻላችሁ በምርጫ አሸንፉኝና ስልጣን ላይ ውጡ ከማለት ይልቅ በምርጫ አሸንፎም ከራሱ ውጪ የሆኑ ወገኖችን ያከለ መንግስት ለመመስረት ቢያስብ ለበለጠ ተቀባይነት የስራ መቃናት ይጠቅመዋል:: መድረክም ካሸነፍኩ ሰፋ ያለ መንግስት ለማቋቋም ሐሳብ አለኝ ካለ ማድረግ ያለበት በእቅዱ ዙሪያ ድጋፍ ማሰባሰብ ነው::

አሸንፎ ተቃዋሚውን ለማካተት የሚደፍር ቢገኝ የኢትዮጵያን ብሔራዊ መግባባትና ዴሞክራሲን እመርታዊ እርምጃ ውስጥ የማስገባት ታሪክ ይሰራል:: ለዚህ ታሪክ አለሁ የሚል ቢጠፋ እንኳ እየተመካከሩ እየተወያዩ ለመስራት መሞከር ይመረጣል:: የፓርቲዎች ምክር ቤትም ከምርጫ ወቅት ጋር ብቻ ሳይጣበቅ ስልጣን ላይ የተቀመጡም ያልተቀመጡም በእኩልነት ስለአገራቸው ለመወያየት የሚችሉበት (በሩ የሰፋ) መድረክ ሆኖ ሊደራጅ ይገባል::

እዚህ ሂደት ውስጥ ለመግባት ሳይፈቅዱ ወይም ጋሬጣ ሆኖ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስባለሁ ማለት የአዞው አይነት አዛኝነት ይሆናል:: ከትንንሽ ቡድን ወደትላልቅ ቡድን፣ ከንቁሪያ ወደ መነጋገር፣ ከ«ብቻዬን» ወደ «ተጋግዘን» መምጣት ለሰለጠነ ሕብረተሰብ ግንባታ ኃይል ነውና::

# በ«ህዳሴው ዋዜማ» ሲዲ ላይ ያልጠግብናቸውን ሰዎች በ«ጨለማው ጉዞ» ዶክሜንተሪ አገኘ ናቸው

አቤ ቶኪቻው

abeto2007@yaoo.com

ወዳጄ እንዴት ሰነበቱልኝ!?

ሰሞኑን የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ በየክፍለ ከተሞቻችን እና በየ ንዑስ ክፍለ ከተሞቻችን ጥቃቅን እና አነስተኛ ንግድ ላይ የተሰማሩ ግን ጥቃቅን እና አነስተኛ ያልሆኑ ግለሰቦች ባዘጋጁት ባዛር ተጥለቅልቀን ነበር:: በባዛሩ እንጨታ እንጨት ነጋዴውም፣ ልብስ ነጋዴውም፣ እርቦ ነጋዴውም፣ ጥልፉ ጥልፍ ነጋዴውም... ሁሉም ለየራሱ የሚፈቅደውን ሙዚቃ በመልቀቅ ከሙዚቃው ብዛት ባዛሩ ወደ ዛር የተቀየረባቸው ቦታዎች ነበሩ:: አንዳንዶች እንዳሉት ከሆነ የሙዚቃዎቹ አለቅጥ መለቀቅ ጥቃቅን እና አነስተኛ ነጋዴ ወዳጆቻችን ሆን ብለው ያደረጉት ሲሆን ይኸውም ከሸማቾች አላስፈላጊ የዋጋ ክርክር ለመዳን ይረዳል በሚል ስልት መሆኑን ሲያወጉ ተሰምተዋል:: ክርክር ስል ትዝ ያለኝን?! በአዲስ መስመር እቀጥላለሁኝ::

ባለፈው ሰሞን በቴሌቪዥናችን ሲተላለፍ በነበረው እና ስለፕሬሶች ግብረ ገብ ሲሰብክ የቆየው የቴሌቪዝን ፕሮግራም «አስተማሪ ነው?» ወይስ «አይደለም» በሚል በከተማችን «አሉ» የተባሉ ጋዜጠኞችን ምሁራንን እና የመንግስት ባለስልጣናትን ባሳተፈ መልኩ ክርክር ሲደረግበት ነበር:: ታድያ አብዛኞቹ የሙግቱ ተሳታፊ የነበሩ ጋዜጠኞች ሲሰሩ ለነበረው ርኩሰት ንስሃ ከመግባታቸውም በተጨማሪ ሌሎችን «ርኩሳን መናፍስተ ፕሬሶችን» ሲያወግዙ እንዲሁም ከርክስናቸው ይነፁ ዘንድ ሲፀልዩ ሲያሸበሽቡ እና ሲዘምሩ ሰንብተዋል:: እሰይ እንዲህ ነውንጂ ቅድስና! (ትምህርተ ስላቅ አላደረኩኝም) ፕሮግራሙን በአፅንዖት እንደተከታተልነው ለክርክሩ ከታደሙት ሁሉ የአንዱ የግል ፕሬስ «ባሉካ» ብቻውን በታማኝነት እና በትጋት ተወቃሽ የስራ ባልደረቦቹ ወቀሳው ከተገቢው በላይ እንደሆነባቸው ሲናገር እንዲሁም የግሉ ፕሬስ የሰራው መልካም ነገር በፕሮግራሙ አለመካተቱ ነውር መሆኑን ሲገልፅ ሌሎች አብረውት ያሉት አቻዎቹ ግን «ይህ ሰው መዓት ሊያመጣብን ነው!» እያሉ ሲሸማቀቁ አንድ ወዳጄ ተመልክቶ «እነዚህ ሰዎች ከጀርባቸው የተደቀነባቸው ነገር አለ ይሆን?» ሲል ጠየቀን:: ይህ አይነቱን ንግግር «እንዳልሰሙ ሆነው ካላለፉት ሌላ ጦስ ያመጣል» በሚል «ባልሰማ ሙድ» አለፍነው:: ስለ ኢቲቪ ፕሮግራሞች ካነሳን አይቀር በሌላ አዲስ መስመር ሌላ ጨዋታ እናስከትል::

«ኢትዮጵያን የማተራመስ አላማ አንግበው የተነሱ የሽብር ሃይሎች ህዝባዊ ተቋማትን ሲያፈርሱ ህዝባዊ ባለስልጣናትን ሲገሉ እና ህዝባዊ መንግስቱን ሲንዱ... ሲሉ ተደርሶባቸው በቁጥጥር ስር ከመዋላቸውም በላይ በገሚሶቹ ሞት በገሚሶቹ እድሜ ልክ ተፈርዶባቸዋል:: ደስ ብሎናል ደስ ይበላችሁ...» የሚለውን ፕሮግራም ተከታትለውታል? እኔ በበኩሌ ፕሮግራሙን ከመከታተሌም በላይ በድጋሚ እንዲተላለፍ ባደረኩት ውትወታ ሌሎችም ያመለጣቸው ሀገር ወዳድ ግለሰቦች እንዲከታተሉት አስተዋፅዖ አድርጌያለሁኝ:: እኔ የምለው ጄነራልን ማመን ግን ቀብሮ ነውና! እኛ አደራ ሰጥተን «ሃገር እያገለገሉ ነው ህገመንግስቱን ብቻ ሳይሆን ሰፈር እና ቀዬውን ይጠብቃሉ» ብለን የተመካንባቸው ጀነራሎች በእንዲህ አይነቱ አኩይ ተግባር ተሰማርተው ሲገኙ በእውኑ ያሳዝናል:: «የህዳሴው ዋዜማ» ሲዲ ላይ አይተን ያልጠግብናቸው ዋና ዋና ሰዎች «የጨለማው ጉዞ» ትረካ ላይ ስናገኛቸው ማዘን ሲያንሰን ነው:: እውነቱን ለመናገር ከዛሬ በኋላ አንድ የማምነው ባለስልጣን የለም:: እንዴ ጎበዝ «ለዝች ሀገር ከጄነራል

ዶክተሮቿ በላይ እኮ ታጋይ ጄነራሎቿ ትልቅ ውለታ ውለዋል!» እያልን የተናገርንበት ጊዜ እኮ ሩቅ አይደለም:: አንዳንዶችማ ታሪክ ራስዋን ደገመች የደርጉ ጀነራሎች «ማዕረጋቸው በመቀስ ቂጣቸው በሳንጃ እንደተወጋው... የዛሬዎቹም ጀነራሎች...» እያሉ ሊያፌዙብን ሞክረዋል:: የሆነ ሆኖ ሰድቦ ለሰዳቢ የሰጡንን እኒህ ዕውቅ የመንግስት ሰዎች ሌሎቹንም እንድንጠራጠር ስላደረጉን ከተፈረደባቸው ፍርድ ውጪ «እንዳንተማመን አደረጋችሁን እግዜር የስራቹን ይስጣችሁ!» ብለን ልንረግማቸው እንወዳለን::

እኔ የምለው የሀገራችን ደህንነት ሰራተኞችን ግን አላደነቃችሁኋቸውም? እንዴ... አሸባሪዎቹ በላዳ መኪና ሲሳፈሩ እርስ በርስ ሲጨባበጡ ሁሉ እኮ በካሜራቸው ቀርፀዋቸዋል! በእውነት «እኛስ ኮራን በናንተ!!» ብሎ መዝፈን ይሔኔ ነው:: አኮሩን እኮ! አንድ አሸባሪ ቡድን በላዳ ሲሳፈር እና ከጓደኛው ጋር ሲጨባበጥ መቅረፅ መቼም በእውነቱ ታላቅ የስለላ ጥበብን የሚጠይቅ ይመስለኛል:: በተለይ ዱባይ ድረስ ተከታትላ የሄደችው የደህንነት ሰው ትጋቷ የሚደነቅ ነው:: ምንም እንኳ አንደ አዲስ አበባዋ ላዳ መኪና ቁልጭ ያለ ምስል ባታሳየንም የሆኑ ሰው የሚመስሉ ሰዎችን ስላሳየችን ምስጋና ይገባታል! ብዬ ለአንድ ወዳጄ ብነግረው «ሞኝ አትሁን የደህነንነቷ ሰው ቁልጭ ብሎ የሚታይ የሰው ምስል ማሳየት ተስኗት አይምሰልህ» አለኝ እህስ ብለው፤ ሰዎቹን ሰው ይመስላሉ እንጂ ሰው አይደሉም ርኩሶች... የሚል መልዕክት ማስተላለፍ ፈልጋ ነው::» አለኝ:: እውነትም እርኩሶች ሲያንሳቸው ነው:: ብዬ አምርሬ ስናገር የሰማኝ ሌላው ወዳጃችን «ተዉ አትፍረዱ...» አለን «እንዴት?» አልነው «እነዚህ ሰዎች እናንተ እንዳላችሁት ርኩሶች ሳይሆኑ ርጉዞች ሊሆኑ ይችላሉ::» ሲለን «ምን ይቃዣል?» በሚል አተያይ እያየነው የምን እርጉዝ የሚል ጥያቄ አስከተልን «የብሶት!» ሲለን በሀሳቤ «የዘመናት ብሶት የወለደው ጀግናው ሰራዊት....» የሚለው ድምፅ እየመጣብኝ በአንደበቴ ግን «ምን ብሶት ቢያረግዙ ሰላማዊ ትግል የት ሄዶ ነው አሸባሪነትን የሚመርጡት???» ብዬ በርካታ ጥያቄ ምልክቶችን ደረደርኩለት::

ከዚህ ከአሸባሪዎች ቡድን ጋር በተያያዘ ሞት ይሁን እድሜ ልክ የተፈረደባቸው አንድ መልከ መልካም ሰው ምነው እንኳ «በእውነት ይሔ የጨለማ ጉዞ ነው!» እያሉ ሲናገሩ የነበሩት እርሳቸው፣ ለካስ ያልገቡበት የፖለቲካ ድርጅት የለም እና ወላ አንድነት የለ ወላ ቅንጅት የለ አንድም ለዚች ሃገር የሚበጅ የለም «እውነት እውነት እላችኋለሁ መዳን በኢህአዴግ እንጅ ሌላ በማንም የለም::» አይነት ይዘት ያለው መልዕክት በቴሌቪዥናችን ሲያሳዩን እኒህ ሰው ድሮውኑ በተቃዋሚነት ከሚለፉ ከኛ ጋር ተቀላቅለው ልማቱን ቢያቀላጥፉ አይሻላቸውም ነበር? ብዬ አንድ ወዳጄን ብጠይቀው «ግዴለም አሁንም ባሉበት ቦታ ሆነው በርካታ ፖለቲካዊና ልማታዊ ስራ መስራት ስለሚችሉ አትጨነቅ::» አለኝ:: እውነትም በአንድ ወቅት የአውራምባ ታይምስ ዋና አዘጋጅ የነበረውና በአሁኑ ወቅት በተደረገው የስልጣን ሽግሽግ ማኔጂንግ ዳይሬክተርነት ደረጃ ላይ የደረሰው ወዳጄ ዳዊት ከበደ ሲፅፍ በነበረው ዝክረ ቃሊቲ ላይ በርካታ ልማታዊ ታራሚዎች መንግስታቸውን እና ህዝባቸውን በትጋት እያገለገሉ እንደነበር አስታውሼ እኒህ ሰው

ልማታዊ ታራሚ እንደሚወጣው ገባኝ:: የሞት ፍርዱ ተፈጻሚም ሲሆን ደግሞ ልማታዊ ሟች ይሆናሉ ብሎ የቧለተ ወይም ሲቧልት ያሰበ አልያም ሰው ሲቧልት እየተመለከተ በቸልታ ያለፈ ሰው አዲሱ ህግ በቸልታ አያልፈውም!

ወዳጄ ስለገና ጨዋታ ጀምሬ ጭልጥ ያለ ፖለቲካ ውስጥ ገባሁኝ አይደለም እንዴ? በነገራችን ላይ ወዳጄ አብዱር ቃድር እንደነገረኝ ከሆነ ፖለቲካ ማለት በሀገራችን ገጠራማ አካባቢዎች ትርጉም «ወሬ» ማለት ነው:: አንድ ሰው ወሬ የሚያበዛ ከሆነ እና ቁብ ነገር ከሌለው የሀገራችን ባላገር «ፖለቲከኛ» ይለዋል:: እንዲሁም አፈ ጮሌ የሆኑ ሰዎችንም ወሬ ይችላል ብሎ ሲያሞካሽ «እከሌ ፖለቲካ ይችላልና::» ይለዋል:: ታድያስ የሀገራችን ፖቲከኞች ከዚህ ትርጉም ጋር ትስማማላችሁ? ስለ አብዱር ቃድር ካነሳን አይቀር አብዱር ቃድር እኔ በምኖርበት አካባቢ የሚገኝ «የአዕምሮ ህመምተኛ» ሲሆን የሀገራችንን ፖለቲካ እና ፖለቲከኞች አብዝቶ የሚጠየፍ እና ሁሉም ፖለቲከኞች በጨለማ ጉዞ ላይ ያሉ ናቸው ብሎ የሚያስብ ሲሆን «ከንግግር» ችሎታ በስተቀር ሌላ እውቀት የሌላቸው በሚለው በባላገሩ ትርጉምም አብዝቶ ይስማማል::

አሁን ፊታችንን በቀጥታ ከፖለቲካ ጨዋታ ወደ ገና ጨዋታ ይዞራል:: «በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ.... አሲና ገን አሲና ገናዬ...» በሚለው ሙዚቃ ብንታጀብ ያምርብናል:: ከላይ ስለገና ስናነሳ ከተማችን ስላስተናገደችው በርካታ ባዛሮች አንስተን ነበር:: ታድያ እርሱን አንስተን የመጣ ቢመጣ የማናልፈው አንድ ቁብ ነገር አለ:: ትራፊክ ፖሊሶቻችን እና ደንብ አስከባሪዎቻችን «በእግረኛ መንገድ የማይጠቀም ወዮለት!» እያሉ ቀን ተሌት በምክር እና በተግሳፅ ሲተጉ እኒህ ባዛር አዘጋጆች የእግረኛውን ብቻ ሳይሆን የመኪናውንም መንገድ ላይ ድንኳን ጥለው ማለፊያ ማግደሚያ አሳጥተውን ከርመዋል:: እንደውም እናጋንን ከተባለ የአንዳንዶቹ ድንኳኖችማ የተተከሉት ዜብራ ላይ ነበር! ማለት ይቻላል::

የሆኖ ሆኖ ዘንድሮ ገና እንዴት ነበር? አንዳንዶች ገበያውን ያዩት በቴሌቪዥን የገበያ ዘገባ ላይ ነው እንጂ ወደ ገበያ እንዳልወጡ ሲናገሩ ነበር:: እኒህ ሰዎች ምክንያታቸውን ሲያብራሩ ዘንድሮ ሁሉም ነገር ጥሩ ዋጋ ያለው በቴሌቪዥን የዋጋ ዘገባ ላይ እንጂ በዋናው ገበያ አይደለምና ስለምን ወደገበያ እንወጣለን? ብለዋል:: እርሶስ ወዳጄ ገናዎን እንዴት አሳለፉት? አይዞት ቆፍጠን ማለት ነው እንጂ ለችግርማ ፊት መስጠት አያስፈልግም:: ምን በወጣዎ ጭምት ብለው ቤትዎ ይቀመጣሉ ለማን ይድላው ብለው? ገበያዎ ወጥተው ያማርዎትን በግ «ይሔ ስንት ነው?» ብለው ገዝተው እንኳ ባያርዱት ሽንጡን ጨበጥ አድርገው ፍርንባውን በእጅዎ ዳብሰው ሁኔታውንም ከቻሉ በካሜራ ካልቻሉ በልቦናዎ ቀርፀው ለትውልድ የሚወራ ታሪክ መያዝ ይበጃል:: ለትውልድ የሚወራ ታሪክ ስል ምን ትዝ አለኝ? በመጨረሻም ላይ ይወራል:: ከዛ በፊት ዘንድሮም አመትባሉ ለሞላለት ገና ሆኖለት በፍስሃ ጊዜውን ሲያሳልፍ ለሌለው ደግሞ አመትባሉ ገና («ና»ን አላልተው በማንበብ ቢተጉልኝ) ወደፊት የሚመጣ የተስፋ ዳቦ ሆኖበት እየተጠባበቀ ይገኛል:: እኛም ለአመታት ብለነዋልና ዘንድሮም እንደግመዋለን:: «ልዩነታችን ውበታችን!» ብለን እንፎክራለን!

በመጨረሻም:-

በከተማችን በአሁኑ ሰዓት በብዛት እየተቸበቸቡ ካሉ መፀሃፍት ውስጥ በፍቅሩ ኪዳኑ የተፃፈው «የፒያሳ ልጅ» አንዱ ነው:: ደራሲው በመጸሀፉ ግርጌ «ዘብሄረ - ፒያሳ - አዲስ አበባ - ሸዋ - ኢትዮጵያ - አፍሪካ - ዓለም» እንዳለውም ከጉለሌ የሚነሳው ጨዋታ በርካታውን የአለም ክፍል አዳርሶ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ሳይሆን ፈረንሳይ ፓሪስ ይደመደማል:: የመፀሀፉ ፀሀፊ ጋሽ ፍቅሩ ኪዳኑ ዓለምን በሙሉ ሲዞር ታድያ ነገሮችን በሙሉ በካሜራ ቀርፆ የማስቀመጥ ልምድ ስላለው ያጫወተንን ጨዋታዎች በፎቶግራፍ አስደግፎ «ወዳችሁ ሳይሆን በግዳችሁ ይህንን ታሪክ እመኑ» ይለናል:: እኛም «አሜን» ከማለት ውጪ ምን ምርጫ አለን? አሜን እንላለን:: ይሔ ከላይ የተጠቀሰው እንደመግቢያ ይቆጠርልኝና ከወዳጄ ጋር ስንጨዋወት ከዚህ መፀሀፍ ውስጥ በጣም ያስገረመንን እንደሚከተለው እናውጋ:-

ጋሽ ፍቅሩ በመፀሀፉ ውስጥ የበርካታ ሰዎች እውነተኛ ስሞችን ጠቅሷል:: ከጉለሌ ልጆች ጀምሮ እስከ ዲያስፖራው ድረስ አንድም የቀረ ሰው የለም:: እንዲህም ሆኖ ደራሲው «ለዘነጋኋችሁ ሰዎች በሽምግልና ስለሆነ ይቅርታ ይደረግልኝ» ሲል ጠይቋል:: ታድያ መፀሀፉን ያነበበ አንድ ወዳጄ እንዲህ አለ «እኛ የወለድናቸውን ልጆች ስም በቅጡ መያዝ በቸገረን ወቅት ጋሽ ፍቅሩ በመፀሀፉ ውስጥ ከአዲስ አበባው የህዝብ ቆጠራ ጋር የሚስተካከል ዝርዝር አካቶ የተረሱ ካሉ ይቅርታ ማለቱ በእኛ ላይ ለመሳለቅ ነው» ብሎኛል:: ይህ ወዳጄ በቆጠራው አነሰ የተባለውን የህዝብ ቁጥር ለማስተካከል በመውለድ እየተጋ ያለ ግለሰብ ነው:: የሆነ ሆኖ ጋሽ ፍቅሩ የብይ ጨዋታን ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ካስገቡት ክፍሉ እና መላኩ ዮሴፍ አንስቶ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጨዋታ ተሳታፊ እስከሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ድረስ ስም የማስታወስ ችሎታህን ሳናደንቅ አናልፍም:: የመጨረሻው መጨረሻ የሚሆነው «በፒያሳ ልጅ» መፅሀፍ ውስጥ ስለ ፕሮፌሰር መስፍን ወለደማሪያም የተፃፋን በማውጋት ይሆናል::

ፕሮፌሰር መስፍን እና ፍቅሩ ኪዳኔ እግር ኳስ ጨዋታ አብረው ይጫወቱ ነበር:: ያኔ ፕሮፌሰር በተከላካይ ቦታ ይጫወቱ ነበር:: አሁንም የመከላከል ተግባራቸውን ቀጥለዋል ይላቸዋል:: የፒያሳ ልጅ:: ምንም እንኳ አርቢተሩ ቀይ እያሳየ ቃሊቲ ቢከተውም...» የሚልም ተፅፏል::

ጋሽ ፍቅሩ መፀሃፉን ወደነዋል እናመሰግናለን!

ወዳጄ እዚህ ላይ የዛሬ ቶካችን ቢያበቃስ?
አማን ያሰንብተን!

# የዋና አዘጋጆችን መብት የገፈፈው

# የኢቴቪው ውይይት

**በዳዊት ከበደ**

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት፣ እጅግ አናሳ ቁጥር ባላቸው የአገራችን የፕሬስ ውጤቶች ላይ ዘመቻ ማቅረቡን አላቋረጠም፡፡ «የፕሬስ ውልደትና እድገት» በሚል ርእስ በርካታዎቹ ፕሬሶች በአንድ ቅርጫት ውስጥ በመክተት የ«ጥፋት መልእክተኞች» ሲል ይግባኝ የሌለው ፍርድ የሰጠው ኢቴቪ፤ ባሳለፍነው ሳምንት የመጨረሻ ቀናት ደግሞ ይህንኑ ፕሮግራም እንዲያወድሱለት አንዳንድ አሳታሚዎችን ጋብዞ ነበር፡፡ ፕሮግራሙ «አበጀህ በሉኝ፤ የሰጧችሁ ፍርድ ፍትሃዊ ፍርድ መሆኑን መስክሩልኝ» አይነት ይዘትም ነበረው፡፡ የተጠሩትም ከአንዳንዶቹ በስተቀር አላስፈሩትም፡፡ በተለይ የጋዜጠኞችን መብት ለማስከበር ቆመናል የሚሉ ይሉኝታ ቢስ ማህበራትም በላኳቸው ተወካዮች አማካኝነት «ፍርዱ ፍትሐዊ ፍርድ ነው ፤በዚሁ ቀጥል» የሚል ሙገሳ አዘል አድናቆት ችረውታል፡፡ ለመሆኑ ይህን ያህል የአየር ሰዓት ሰጥቶ መወነጃጀል ፋይዳው ምንድነው?

በእኔ እምነት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንደ አንድ የሚዲያ ተቋም የመሰለውን ሐሳብ የመሰንዘር መብቱን አከብርለታለሁ፡፡ ከአመታት በፊት በጋዜጠኞች ላይ ሞት የጠየቁ ባለስልጣን እንዳሉት «ከጥላቻ እና ቂምበቀል በጸዳ መልኩ ሁሉም ራሱን እንዲመለከት፤ጤናማ የሚዲያ ድባብ ለመፍጠር» ቢሆን ኖሮ ችግር አልነበረውም፡፡ ነገር ግን ከፕሮግራሙ ይዘት አንጻር ሦስት መሰረታዊ ስህተቶችን መመልከት ይቻላል፡፡

## 1. የግል ጋዜጣ የሚያነቡ ዜጎችን እንደ ዓመጽ ናፋቂ አድርጎ የመመልከት ችግር

የመንግስት አቋም ይሁን አይሁን ግልጽ ባይሆንልኝም አንድ ፕሮግራሙን በአድናቆት የተመለከቱ «ልማታዊ» አሳታሚ የሰነዘሩት አስተያየት እጅግ አስገርሞኛል፡፡ ከማስገረምም አልፎ ይህችን ጽሁፍ እንዳዘጋጅ መነሻ የሆነኝ «ስለ ሁለት ዲጂት እድገት ልማታዊ ዘገባ ስንሰራ ጋዜጣው አልሸጥ አለን፤ እዚህ አገር ጋዜጣ እንዲሸጥ ቤተመንግስት መታመስ አለበት፡፡» የሚለው አስተያየታቸው ነው፡፡ በእርግጥ እኚህ አሳታሚ እዚህ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ በተጨባጭ የታዘቧቸው መረጃዎች ካሉ ይህ አስተያየት «ተጣመው በቀሉ» የተባሉ ፕሬሶችን ለመውቀስ ማስረጃ ሆኖ መቅረብ የለበትም ባይ ነኝ፡፡ ምክንያቱም ወቀሳው ከፕሬሶቹ ይልቅ በአንባቢው ላይ ያነጣጠረ ስለሆነ፡፡ እዚህ ላይ ግን የእኔ አስተያየት «ቤተመንግስት እንዲታመስ» የሚፈልግ አንባቢ/ዜጋ ቁጥር በርካታ መሆኑ፤ የኢኮኖሚ «ዕድገቱ» በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ በጥርጣሬ የሚታይ ስለመሆኑ በቴሌቭዥን ቀርበው ምስክርነት የሰጡ የአገዛዙ

ታማኞች፤ እውነታው እንደሱ ነው ብለው የሚያምኑ ከሆነ መፍትሄው ፕሬሱን ማውገዝ ነው? ወይንስ ፕሬሱን ለቀቅ አድርጎ «ልማት ወዳድ» እና «አፍቃሬ ቤተመንግስት» የሆነ ዜጋ እንዲፈጠር የህዝቡን ፍላጎት መመለስ? በእኔ እምነት ቀዳሚው የቤት ስራ መሆን ያለበት ይህ ይመስለኛል:: በ«ዶክመንተሪው» ላይ የግሉ ፕሬስ «ለገንዘብ ሲል ሐሰተኛ ሽብር ይነዛል» እየተባለ ነበር:: በኢቲቪ ስቱዲዮ በተካሄደ ውይይት አሁን ያሉ ጋዜጦች የኮፒ መጠናቸው በምርጫ 97 ወቅት ይታተሙ ከነበሩ ጋዜጦች ጋር ሲነጻጸር እጅግ አነስተኛ መሆኑም ተገልጿል:: ለዚህ ደግሞ ምክንያት ሆኖ የቀረበው አሁን ያሉ ጋዜጦች የያዙት አቋም ለዘብተኛ በመሆኑ ነው ተብሏል:: እንግዲህ ልብ በሉ በአሁኑ ወቅት ጋዜጣ የመግዛት አቅም ያለው አብዛኛው አንባቢ ለዘብተኛ ጋዜጦች አይፈልግም ተብሎ በኢቴቪ እየተነገረን ነው:: በውይይቱ ወቅት በስክሪን ይታይ የነበረው «ነጻነት» ጋዜጣ በምሳሌነት ከቀረቡት መካከል ይገኝበታል:: በምርጫ 97 ወቅት የኮፒ መጠኑ መቶ ሺህ ኮፒ የነበረው ይኸው ጋዜጣ የፕሮግራሙ አዘጋጆች እንደሚሉት «ሐሰተኛ ዘገባ የሚያቀርብ ፕሬስ ነበር» ተብሎ ቢታመን እንኳን በመንግስት እንዲቆም እስከተደረገበት የመጨረሻው ዕትም ድረስ በየሳምንቱ መቶ ሺህ አንባቢ ያለማቋረጥ ይገዛው ነበር:: ጋዜጣው ውሸት ከሆነ ይጽፍ የነበረው ህዝቡ የኢህአዴግን ፕሮፖጋንዳ አልፈልግም «ውሸት»ም ቢሆን ስለኢህአዴግ መጥፎነት እስከነገረኝ ድረስ ማንበቤን አላቆምም የሚል አቋም ለምን መረጠ? ይህንኑ ጥያቄ ነው መመለስ ያለብን:: መፍትሄው ፕሬሶቹን ለማውገዝና ለመዝጋት መቸኮል ወይስ ህብረተሰቡ እነሱን ማንበብ የመረጠበትን ምክንያት መርምሮ ለህዝቡ የሚመች አስተዳደር ማስፈን? በእኔ እምነት እንዲህ አይነቱን ጋዜጣ የሚያነቡ አንባቢያንን የኢህአዴግ ደጋፊ እንዲሆኑ ለማድረግ መፍትሄው በጋዜጣውና እና በአዘጋጆቹ ላይ «ህጋዊና ፖለቲካዊ እርምጃ» መውሰድ አይደለም:: ምክንያቱም ይህ አይነቱ እርምጃ ብቻውን አሳታሚውንና አዘጋጆቹን ይጎዳ እንደሆነ እንጂ እርምጃው ህዝቡ ከኢህአዴግ ጎን እንዲሰለፍ አያስችለውም::

## 2. እያሸማቀቁ «መማማር» እንዴት?

በመግቢያዬ ላይ እንደጠቀስኩት የፕሮግራሙ አላማ «መማማር ነው» ተብለናል:: ልብ አድርጉ «የግሉን ፕሬስ ማስተማር» አይደለም:: መማማር በመከባበር ላይ የተመሰረተ የልምድ ልውውጥ ነው:: ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ወገኖች አንዱ ከሌላው ልምድ የሚቀስምበት እንደማለት ነው:: የግሉ ፕሬስ የኢቴቪን ደካማና ጠንካራ ጎን እየነቀሰ ማስተማር ኢቴቪም በተመሳሳይ ሁኔታ የግሉን ፕሬስ ጠንካራና ደካማ ጎን እያነሳ በሰለጠነ መንገድ ልምድ መለዋወጥ ነው ለእኔ የ«መማማር» ትርጉም:: ነገር ግን «ተጣመው የበቀሉ» የሚል ርዕስ በተሰጠው «ዶክሜንተሪ» ላይ ተዋናይ የነበሩ «ረዳት ፕሮፌሰሮች» ሐሳባቸውን የሰጡት መማማርን አስበው ነው? እንዳልሆነ በእርግጠኝነት

መመስከር ይቻላል:: ምክንያቱም በዩኒቨርስቲ ያሉ ተማሪዎቻቸውን «ተጣማችሁ የበቀላችሁ» እያሉ እንደማያስተምሯቸው መገመት ይቻላል:: የስድብ ናዳ ሲያወርዱ የነበሩ የዶክመንተሪው «ትጉሐን ተራኪዎች»ም እንዲሁ ስለመማማር አንዳች ግንዛቤ ሳይኖራቸው ስለመርዶ ነጋሪነት ነበር ያነበነቡት::

አያድርገውና የበሽታ ወረርሽኝ አገራችን ቢገባ ሚዲያው ህብረተሰቡ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ብሎም የሚመለከተው አካል መፍትሔ እንዲያፈላልግ መረጃዎችን ይፋ ላያደርግ ነው? ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ከወራት በፊት ተከስቶ የነበረው «አተት» ነው:: በወቅቱ ይህ አጣዳፊ በሽታ በአገራችን ስለመኖሩ የግል ፕሬሶች ተቀባብለው ሲያስተጋቡ የመንግስት ሚዲያዎች ግን ዝምታን ነበር የመረጡት:: የኋላ ኋላ ግን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች መግለጫ ሲሰጡ የመንግስት ሚዲያዎች ስለንጽህና አጠባበቅ ሰበካ ጀመሩ:: ከልማት አብሳሪዎቹ ቀድመው አገራዊ ግዴታ የተወጡ ፕሬሶችን «መርዶ ነጋሪ» የሚል ክርስትና ስም መስጠት ጠንክረው እንዲሰሩ «ማባነኛ ደወል» ሊሆን አይችልም::

## 3. ከማይመለከታቸው ወገኖች ጋር መወያየት ለምን?

የመገናኛ ብዙሐንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ በሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም በፓርላማ መጽቁን ተከትሎ አዋጁን እንዲያስፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው የብሮድካስት ባለስልጣን ባወጣው የአፈጻጸም ማብራሪያ (ቅጽ) ላይ በሚዲያ ተቋሙ ውስጥ ከ2% በላይ ድርሻ ያለው ፤አዘጋጅ መሆን እንደማይችል ይደነግጋል::

በዚህ መነሻነት በዚሁ የቴሌቪዠን ውይይት ላይ ተሳታፊ የነበሩትና የብሮድካስት ባለስልጣን ም/ኃላፊ የሆኑት አቶ ደስታ ተስፋው የካቲት 20/2001 ዓ.ም በጽ/ቤታቸው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በአዋጁ አንቀጽ 6 መሰረት በፕሬስ ውጤቱ ሙሉ የኤዲቶሪያል ስልጣን ያለው ዋና አዘጋጅ መሆኑን ገልጸው «አሳታሚ ግን በድርጅቱ ውስጥ የጎላ ጥቅም ያለው የድርጅቱን የስራ አስተዳደር የሚመራ ማንኛውም ሰው ነው» ካሉ በኋላ ይህ እንዲሆን የተደረገበትን ምክንያት ሲያብራሩ «የሚዲያ ባለቤቶች የህትመት ይዘትን በመቆጣጠር ክቡር የሆነውን የጋዜጠኝነት የሙያ ነጻነት እንዳይጋፉ በህግ መደንገግ የሚዲያ ነጻነትን ለማረጋገጥ የተደረገ ህጋዊ ከለላ ነው» ብለው ነበር አቶ ደስታ:: እንግዲህ ይህ አዋጅና የአፈጻጸም መመሪያ ስራ ላይ ባለበት ሁኔታ ፤ኢቴቪ በሰሞንኛው የጋዜጠኝነት ስነምግባር ውይይቱ ሙሉ የኤዲቶሪያል ነጻነት ያላቸውን ዋና አዘጋጆች ትቶ አሳታሚዎችን ብቻ በመጥራት ስለ ልማታዊ ዜና አዘጋገብ፤ስለወገንተኝነትና ሚዛናዊነት ሲያከራክር የነበረው::

በበኩሌ ኢቴቪ ለምን አሳታሚዎችን ብቻ ጠርቶ አወያየ እያልኩ አይደለም:: (በዚህ አጋጣሚ እንደ አንድ አሳታሚ የምመራው ድርጅት ከዚህ የአፈጻጸም ማዕቀፍ ቢያፈነግጥ ዕጣ ፈንታው ምን እንደሚሆን ስለማውቅ የባለስልጣን መስሪያቤቱን የተጣመመ መመሪያ ስማክበር ተገደድኩ እንጂ ባለቤት ዋና አዘጋጅ መሆን አይችልም የሚለው ድንጋጌ ተገቢ ነው ብዬ

አላምንም።) ቢሆንም ግን እራሳቸው አቶ ሽመልስ ባወጡት ህግ አሳታሚ በኤዲቶሪያል ጉዳዮች ላይ ጣልቃ አይገባም ብለው ሲያበቁ ዛሬ አቶ ሽመልስ እራሳቸው በኤዲቶሪያል ጉዳዮች ዙሪያ ከአሳታሚዎቹ ጋር ውይይት የሚያካሂዱት በምን አግባብ ነው? ኢቴቪ በግንዛቤ ማነስ ነው አሳታሚዎችን የጋበዘው ቢባል እንኳን፤ ህገመንግስትንና ህግን በማክበር ቁርጠኛ አቋም አለኝ የሚሉት አቶ ሽመልስ «በምን አግባብ ከአሳታሚዎች ጋር እወያያለሁ» በማለት ውይይቱን ማቋረጥ ነበረባቸው። ምክንያቱም ፍቃደኛ ሆነው በውይይቱ ላይ የተሳተፉ አሳታሚዎቹ በኢቴቪ ስቱዲዮ የደረሱበትን ስምምነት ተግባር ላይ ለማዋል በአዘጋጆቻቸው ላይ ጫና እንዲፈጥሩ እያበረታታናቸው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መልኩ የምናደርገው ውይይቱ ፋይዳ ቢስ ነው።

# መሰሪ ፖለቲካ ቢበቃንስ

*በፍስሐ ያዜ*

በአገራችን ፖለቲካ ዙሪያ በተለይም ምርጫን በሚመለከት ጉዳይ ሁለት መሠሪ አስተሳሰቦች ወይም አካሄዶች አሉ።
እነዚህ ሁለት ነገሮች የሚከናወኑት ምርጫ ሊደርስ ከዓመት ያልበለጠ ጊዜ ሲቀረው ሲሆን፤ ተፈፃሚ የሚሆኑት ደግሞ፡- አንደኛው በገዥው ግንባር አማካኝነት፣ ሁለተኛው በተቃዋሚ ፓርቲዎች አማካኝነት ነው።

እነዚህን መሰሪ ፖለቲካዊ አካሄዶች በውል ከተረዳንም የእያንዳንዱ ፓርቲም ሆነ ፓርቲ ነኝ ባይ ድብቅ አጀንዳን በቀላሉ መገንዘብ ስለሚያስችለን አስቀድመን እንየው።

በመጀመሪያ ደረጃ ብዙ ቅን ተግባሮችን ለአገርና ለህዝብ የመፈፀም ሰፊ እድል ያለው፣ ነገር ግን ያልቻለበት ኢህአዴግ ምርጫ ሲደርስ ወደ ህዝቡ ለመቅረብ ይሞክራል። የተለመደውን በአጉል ተስፋ የተሞሉ ቃላቶችን እንደሞኝ ለቆጠረው ለዚህ ንቁ ህዝብ በየመድረኩ ይደሰኩራል። የመደስኮሪያ መድረኮች ካጠሩም ምርጫው ሲቃረብ ሌሎች አዳዲስና ያልተለመዱ መድረኮች በልዩ አበል እንዲቋቋሙ ያደርጋል። ለጊዜያዊ አበል ሲባልም ህዝቡ ጥሪውን አክብሮ ቢያንስ በዚህ አጋጣሚ በገንዘቡ ገዝቶ ሊጠጣ ያልቻለውን እሽግ ውሃ ለመጠጣት፣ አንዳንዱ ለመቅመስ ይታደማል።

ቲሸርት የሚታደልበት ከሆነማ እኔ ራሴ አልቀርም። ለማንኛውም ይህን መሰል የመደስኮሪያ መድረክ ሲዘጋጅ መሄጃ የሌለው ጊዜ ለማሳለፍ፣ በአገሪቱ ፖሊሲ ምክንያት መስራት እየቻለ ሥራ አጥቶ ቤት የሚውለው ቤት ላለመዋል አጋጣሚውን ተጠቅሞ ውሎ ለመምጣት፣ አንዳንድ የሚባለውን ለመስማት፤ ሌላው በዘመኑ አይቶት ስለማያውቀው የስብሰባን ምንነት ለማየት፣ የቀረው መግቢያ የሌለው ልዩ ዝግጅት እየመሰለው፣ የራሱ አባሎች ደግሞ ዝግጅቱን ለማዳመቅ፣ የኔ ቢጤው (ተመጽዋች ማለቴ አይደለም። ለነገሩ ሁሉም ወገን ከጥቂቶች በስተቀር ተመጽዋች ነው። መንግስት

ራሱ በምፅዋት ሃይል ነው ያለው) ወሬ ለመለቃቀም፣ ሌላውም ለሌላ ምክንያት መድረክ ላይ ይገኛል።

በዚህ ጊዜ ያለአንዳች ጥርጣሬ ኢህአዴግ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ተደርጎ ይቆጠራል። ስለዚህ «ብንሰራም ባንሰራም ህዝቡ እንደው ከኛ ጋር ነው» የሚል ድምዳሜ ላይ ይደረሳል። ቢያንስ ይኼ ሁሉ ህዝብ የተገኘው ለምን እንደሆነ የሚረዳ ሰብሳቢ ቀርቶ የሚጠረጥር እንኳ አለመኖሩ አስገራሚ ነው። ነገሩ እንደ ሱስ ሆኖ ቀጠለ።

በተለይ ገዥው ፓርቲ ከምርጫ 97 በኋላ የህዝብን ተንጋግቶ መምጣትና ደጋፊ መስሎ መታደም ሊያስተማምን እንደማይችል በደንብ መረዳት ሲገባው አልተረዳውም።

ሁኔታው በዚህ መልኩ ቀጠለና ለዓመታት መኖራቸው እንኳ እስኪረሳ ድረስ ታይተው የማያውቁ፣ ድምፃቸው ተሰምቶ የማያውቁ ባለስልጣናት ልክ ምርጫ ሲቃረብ እንደ ማንኛውም ተራ ሰው ከግዙፍ ግዙፍ መድረኮች ጀምሮ ወለላቸው ምንጣፍ አልባ በሆኑ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ድረስ ተገኝተው ንግግር ማድረግ ይጀምራሉ።

ይኼ አካሄድ በማንኛውም ጊዜ (በአዘቦት ቀንም ቢሆን) ኖሮ መንቀፍ ባላስፈለገ። ነገር ግን ምርጫ ሲደረስ ጠብቆ መወዳጀት ቂጣ ለመንጠቅ አቻ ህፃን ጓደኛውን እያባበለ እንደሚቀርብ ሆዳም ህፃን ዓይነት ስለሚሆን ሊተች ይገባዋል።

ከዚያም ቃል ይገባል፣ የተጀመሩ ግንባታዎችና ምንትሶች ከምርጫው በኋላ ተጠናቀው አገልግሎት እንደሚሰጡ ወዘተ... ይገለጽና ከስብሰባው አጀንዳ ውጭ እግረመንገድ ህዝቡ ከማንኛውም የአመጽ ኃይል ጋርም መተባበር እንደሌለበት፣ የተጀመሩትን ልማቶች ለማደናቀፍ የተሰለፉ ወገኖች አሉና መጠንቀቅ እንሚያሻ ተደጋግሞ ይሰበካል። አደናቃፊው ማን እንደሆነ ሁሌም ግራ እንደገባኝ ነው። ይመስለኛ ል ተቃዋሚዎቹን ነው።

ብቻ ምን አለፋችሁ ምርጫ ሲደርስ የሚገቡ ቃላቶችና የሚጣሉ መሠረቶች፣ የሚጀመሩ መልካም እንቅስቃሴዎች ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ቢደረጉ ይች አገር የት ትደርስ እንደነበር ለመግለጽ አይቻልም። ምናልባት ከG-8 አገሮች ጋር ተቀላቅላ G-9 መባል ይጀምሩ ነበር። የገዥው ግንባር ቋሚ አካሄድ (አሰላለፍ) ይኸው በመሆኑም ለውጤት መብቃት አለመቻሉ በራሱ ያስረዳናል። በእውነት የአሰላለፍ ለውጥ ካልተደረገ ሁሉ በዳኛ አድልኦ እየታገዙና «ኦፍ ሳይድ» የሆነውን ጎል ነው ብሎ ድርቅ እየተባለ ለድል መብቃት እንደማይቻል ተመልካች ያውቀዋል። የሆነ ሆኖ በገዥው ፓርቲ ዘንድ ሲንፀባረቅ የኖረውና አሁንም በድምቀት እየተንፀባረቀ ያለው እንዲያውም በጣም ከማንፀባረቁ የተነሳ ዓይን እያቃጠለና እያጠፋ ያለው መሰሪ የፖለቲካ አካሄድ ያየነውን ዓይነት በሽንገላ የተሞላ ሂደቱ ነው።

ሁለተኛውና በተቃዋሚ ፓርትዎች ዘንድ በእጅጉ የሚንፀባረቀው መሰሪ የፖለቲካ አካሄድ ደግሞ በተመሳሳይ ጊዜ የሚከናወን ሲሆን ይኸውም ልክ ምርጫ ሲደርስ እርስ በርስ ተጠላልፈው ለመውደቅ ያመቻቸው ዘንድ ወቅቱን ጠብቀው የሚገምዱት ገመድ ነው።

ምን ዓይነት እርግማን እንደሆነ ለብዙዎች ግልጽ ባይሆንም ከገዥው ፓርቲ እንሻላለንና ምረጡን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከገዥው ፓርቲ እኩል ምርጫ በደረሰ ሰሞን የራሳቸውን ህብረት፣ አንድነት፣ ውህደት፣ ትብብር፣ ጥምረት፣ ቅንጅት (የፓርቲ ስሞች አይደሉም) ትስስር፣ ጥልፍልፍ፣ ቁልፍልፍ፣ ምንትሴ ቅብጥርሴ የሚሉትን ነገር ደጋግመው ማነብነብ ይጀምራሉ። እርግጥ ነው መተባበርና መደጋገፍ ቢጠቅም እንጂ አይጎዳም። ነገር ግን ለመቀናጀትም ሆነ ለመዋሃድ፣ ህብረት ለመፍጠርም ሆነ ለመጣመር፣ ለትስስርም ሆነ ለአንድነት፣ ለመጠላለፍም ሆነ ለመቆላለፍ የግድ ምርጫ እስኪደርስ መጠበቅ አያስፈልግም። አስፈላጊነቱ ከታመነበት ቀደም ብሎ ተቀናጅቶ በሚኖረው ሰፊ ጊዜ ልዩነትን እያጠበቡ፤ ሃሳብ ለሃሳብ እየተግባቡ፤ ግለሰብ ለግለሰብ፣ ቡድን ለቡድን እየተፈታተሹ እየተገማገሙ፣ በደንብ ተነጣጥሮ ግልጽ ያለ አቋም ላይ መድረስና መዘጋጀት ከዚያም ህዝቡን ማዘጋጀት ሲጠበቅባቸው በዚህ ምትክ ልክ ኢህአዴግ ምርጫን ጠብቆ ከህዝብ ጋር ለመወዳጀትና ለመቀናጀት እንደሚፈልገው ሁሉ እነርሱም ምርጫው ሲቃረብ እርስ በርስ መቀናጀት ያምራቸዋል።

በዚህ ጉዳይም ኢህአዴግ በምርጫ 97 ወቅት ቢያንስ መማር አልቻለም ብዬ ከህዘብ ብዛት ጋር አያይዤ እንደገለጽኩት ሁሉ ተቀዋሚዎች በ97ቱ ምርጫ ባለቀ ሰዓት መቀናጀታቸው ጉድ እንዳደረጋቸው አጢነው ከስህተታቸው ሊማሩ አልቻሉም። አስደናቂውን አደጋ ሊማሩበት አልቻሉም።

ይህ መሰሉ ሰፊ ጊዜ ያልተሰጠውና በጊዜ ሂደት ማጥራት ያልተቻለ ቅንጅትና ጥምረት ወሳኙ ወቅት ላይ አደጋ ሊጋረጥ እንደሚችል እየታወቀ ቢያንስ ለዓመታት ሳይታሰብበት ተጎልቶ ኖሮ ምርጫው ወራት ሲቀረው እንደ መጨረሻ ፀሎት ተደርጎ መወሰዱ በእርግጥም መሰሪ ፖለቲካ ቢባል ያስኬዳል።

እነዚህ ወገኖች ለዓመታት ቃሉን አንስተውት ሳያውቁ ምርጫው ሲቃረብ ለምን እንደሚረባረቡበት ግራ ያጋባል። ችግሩ ለፓርቲው መፈረካከስ ብቻ ቢሆን በምን አገባን ይታለፍ ነበር። ነገር ግን የህዝብን ድምጽ በየአደባባዩ እንዲበተን ስለሚያደርጉት ያሳዝናል። እንግዲህ ምርጫው ጥቂት ወራት ነው የቀረው። ሆኖም እርስ በርስ የመጣመሩ ሽር ጉድ እንደቀጠለ ነው። እስከዛሬ ምን ሲሰሩ ነበር አትሉኝም?

እስከዛሬማ እርስ በርሳቸው በየጋዜጣው እየተዘላለፉ፣ በግለሰብ ደረጃ እየተሞላለጩ ነበር የከረሙት። ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ ጉዳዮች በሁለቱም ወገኖች መቀረፍ ያስፈልጋቸዋል። እያንዳንዱ ፓርቲም ሆነ ግለሰብ በህዝብ ድምጽ መቀለዱ ሊያበቃ ይገባል። ምድር ዘላለማዊ ናት ተብሎ  የታወጀ ይመስል የሁሉም ጉጉት ስልጣን መያዝና መበልፀግ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ማብቃት ያለበት ተግባር መሆኑንም ልናምንበት ይገባል።

እርስ በርስ እየተጠላለፉ መውደቅ ይብቃችሁ - ለተቃዋሚዎች፤ ህዝብ ያታለላችሁ እየመሰላችሁ ራሳችሁን ማታለል በቃችሁ - ለገዥው ግንባር፣ ብል ይሰሙኝ ይሆን?

ለማንኛውም እነዚህ በሁለቱም አካላት እየተፈፀሙ ያሉና ሲፈፀሙ የኖሩ መሰሪ ፖለቲካዎች ናቸውና አንባቢያንን ልዩ ትኩረትና ምርመራ አድርጉባቸው ለማለት በቂ ናቸው:: እያንዳንዱ ዜጋም በምርጫው በሚሳተፍበት ወቅት የእያንዳንዱን ፓርቲም ሆነ የአባላቱን ቀናዒነት ከልብ ማጤን የሚኖርበት ይህን መሰሉን መሰሪ አካሄድ እንዳይቀላቀል ነው::

በማስመሰልና በሸንገላ ለመመረጥ የጓጉ ፖለቲካኞች የሌሉበት፤ ግጭትና ደም መፋሰስ የማይታይበት፤ ኮሮጆ የማይሰረቅበት፤ ተጠላልፎ መውደቅ የሌለበትና ባጠቃላይ በሰላማዊና በሰላማዊ መንገድ ብቻ ተካሂዶ የሚጠናቀቅ ምርጫ ያድርግልን::

ከምርጫው ጋር ተያይዞም ቃሊቲ የሚለውን ስም በፍፁም መስማት የሚፈልግ የለም!

# ልዩ ቅኝት

# ዛሬም ነገም ስደት፣ ለምን?

**እየተበራከተ የመጣውን የኢትዮጵያዊያን ስደት አስመልክቶ *አቤል ዓለማየሁ* ዓለም አቀፍ ጥናቶችና ሪፖርቶች እንዲሁም የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሙያ ሀሳብን አካቶ ተከታዩን ፅሁፍ አሰናድቷል::**

በሆሳዕና እና በአጐራባቿ የሚገኙ በርካታ ወጣቶች የቋጠሯትን ጥሪት ሸክፈው፣ ብድር አሰባስበው፣ ያላቸውን ከብትና ቤት ሸጠው ወደ ደቡብ አፍሪካና አረብ ሀገራት እየተመሙ ነው:: በሀገሮቹ የተጓዙ ጥቂቶች በስልክ የተሻለ ገንዘብ እያገኙ ስለመሆናቸው ብቻ ስለሚያወሩና ከጉዞ መልስ በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ ከአልባሳት የሚጀምሩ መጠነኛ ለውጦች ስለሚያሳዩ በጓደኞቻቸው ላይ መንፈሳዊ ቅናት፣ ጉጉትና መነሳሳት ይፈጥራሉ::

በንድግ ሥራ ትተዳደር የነበረችው አልማዝ አድነው ከሆሳዕና ነዋሪዎች መካከል አንዷ ናት:: የሀገሯ ልጆች ተሰደው መጠነኛ ለውጥና ሞት እያገኙ መሆናቸውን በቅርብ የምትታዘበው ቢሆንም ከእጅ ወደ አፍ የሆነውንና ራሷን ለማሻሻል በቂ ያልሆነው የንግድ ሥራዋ ብዙም ስለማያስደስታት እንደ ጓደኞቿ ሁሉ እሷም ወደ አረብ ሀገር ተጉዛ እድሏን በመሞከር ኑሮዋን ለማሻሻል አቀደች:: የአረብ ሀገር ህይወትን በርካታ አስከፊ ገጽታዎች (ክስተቶች) የሰሙት ጆሮዎቿን በሁለት እጆቿ በመያዝ ልቧ ስኬት ላይ ብቻ በመተማመኑ ያጠረቃቀመቻትን መጠነኛ ገንዘብና ሻንጣዋን ይዛ የጉዞ ሂደት ለመጀመር አዲስ አበባ ወደሚገኙ ዘመጆቿ ጋር መጣች:: ሂደቱን ከፓስፖርት ማውጣት ጀምራ በቶሎ በአየር ታክሲ በመብረር ከአንዱ የመካከለኛው ምስራቅ አገር ማረፊያዋን ለማድረግ ብታቅድም ነገሮች እንደሀሳቧ መሆን አልቻሉም:: «መሰናዶውን ጨርሼ

እልክሻለሁ» ያላት አንድ ኤጀንሲ «ለጊዜው መላክ የሚያስችለኝን ፈቃድ ተከለከልኩ» በማለቱ የከፈለችው ወደ ሦስት ሺህ የሚጠጋ ገንዘብ ውሃ በላው፡፡ እሷና መሰሎቿ ገንዘባቸውን ለማስመለስ ቢመላለሱም ውጣ ውረዱ በዛባቸው፡፡ ወደ ክስ ለመሄድ ዝግጅት ላይ ባሉበት ወቅት የአልማዝ ሆሳዕና ያሉ ዘመድና ጓደኞቿ ቀድመዋት ተሳክቶላቸው በረራ ሲያደርጉ ስትመለከት ከሌላ ኤጀንሲ ጋር ግንኙነት ጀመረች፡፡ በገንዘቧ መብከን ውስጧ ቢያዝንም ክስ ውስጥ መግባትን ጊዜ እንደ ማጥፋት በመቁጠር በጀመረችው አዲስ መንገድ በመጠቀም ወደ ኳታር አቀናች፡፡

የቤት ውስጥ የፅዳት አገልግሎት ለመስጠት ከገባችበት ቤት አሰሪዎች ጋር የጠነከረ አለመስማማት ባይኖራትም ከሴት አሰሪዋ ዘንድ አልፎ አልፎ ጭቅጭቅ ይከፈትባታል፡፡ ሁሉንም ችላ ለመኖር ውስጧ ቢያምንም ከቤተሰቦቿ ጋር የስልክ ግንኘ ነት እንዳታደርግ በመከልከሏ ዱብ እዳ ሆነባት፡፡ ከወር በፊት ኢንዶኔዢያ ዜግነት ካለው ከምትሰራበት ቤት ሾፌር ጋር ለገበያ ትወጣለች፡፡ ሾፌሩንም እጅ ስልኩ ላይ እንዲያስደውላት ተማፅና ወደ ሀገር ቤት «ሃሎ» ትላለች፡፡ የሾፌሩን ስልክ የሚጠቀሙት አሰሪዎቿ ባልና ሚስት ብቻ ናቸው፡፡ አልማዝም ወደ ሀገር ቤት ደውላ ስልክ በምታናግርበት ጊዜ ወደ ሹፌሩ ስልክ ላይ የደወለው የቤቱ ባለቤት ስልኩ ይያዝበታል፡፡ በቶሎ የተጠራው ሹፌር ወደ ኢትዮጵያ የተደወለውን የስልክ ጥሪ ከስልኩ ላይ አጥፍቶ ነገሩን ለመሸፋፈን ቢሞክርም ባለቤትየው ሲም ካርዱ በስሙ የወጣ በመሆኑ የስልክ አገልግሎት ወደሚያገኝበት ድርጅት በመሄድ ነገሩን ይደርስበታል፡፡ «በቶሎ ሌላ ሹፌር ማግኘት ስለማይችሉ ሹፌሩን ቢቆጡትም የከፋ ውሳኔ አላሳለፉብትም» የምትለው አልማዝ አድነውን ግን እንደሰረቀች አስመስለው ለፖሊስ በማመልከት አሳሰሯት፡፡

ሰባት ቀንም ታስራ ከገደብ የእስር ቤት ቆይታዋ በኋላ ዳግመኛ ኳታር ውስጥ መግባት እንዳትችል ፓስፖርቷ ላይ ምልክት አስቀምጣ ኮንትራቷን ለማጠናቀቅ ስድስት ወር እየቀራት በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ ወደ ሀገሯ ተላከች፡፡

አልማዝ መሠረታዊ መብቷ ተነፍጎ፣ ለእስር ተዳርጋ ወደ ሀገር ብትላክም ብዙሃን ስደተኛ ኢትዮጵያዊያን በስደት በአሰሪዎቻቸው ከሚደርስባቸው የሰሩበትን ገንዘብ አለማግኘት፣ እንግልት፣ መደፈርና ስቀይ አንፃር የከፋ አደጋ አላጋጠማትም፡፡ ከቤት ውስጥ ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደሞዟ ተከፍሏታል፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት በበርካታ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የሚገኙ እህቶቻችን ራዕያቸው ጽልመት ወርሶት ውጥናቸው ከሃሳብነት ፈቀቅ ማለት ሳይችል በእስር ቤት ተወርውረው የጨለማ ኑሮ ውስጥ ናቸው፡፡ በባህር በሊቢያ በኩል ወደ ጣሊያን ሊገቡ የሚታገሉ ወጣቶችም ከሞት ተርፈው ጣሊያን ቢደርሱ እንኳን ማረፊያቸው እስር ቤት በመሆኑ ስቃይ ውስጥ መሆናቸው ይነገራል፡፡ በበርካታ ዓለም አቀፍ ሀገራት የተሰደዱ ኢትዮጵያዊያንም ጉዟቸው እንዳሰቡት ሳይሆን የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያቀርቡት ምክንያት ተቀባይነት እያጣ ተጠርዞ የመላክና የሰቀቀን ኑሮን ቀጥለዋል፡፡

## ንግድን የሚፎካከረው ፍልሰት

በአሁኑ ሰዓት በዓለማችን ላይ ከ200 ሚሊዮን በላይ ሰዎች የሚገኙት በትውልድ ቦታቸው አይደለም:: እነዚህ በተለያዩ ሀገራት የሰፈሩ ዲያስፖራ ስደተኞች ብዙ ህዝብ አለባቸው የሚባሉ የአራት ሀገራት ህዝቦችን ቁጥር ይልቃሉ:: እነዚህ ስደተኞች ለሚኖሩበት ሀገር በስራቸው ለትውልድ ሀገራቸው ገንዘብ ፈሰስ በማድረግ ሰፊ የኢኮኖሚ ጥቅም ይሰጣሉ::

82 በመቶ የሚሆኑ ስደተኞች የሚገኙት ባደጉ ሀገራት ነው:: በ2008 በተደረገ ጥናት ከሀገራቸው ወጥተው የሚኖሩት ዜጎች ወደ እናት ሀገራቸው የሚያፈሱት ገንዘብ በዶላር 305 ሚሊየን ብር ይጠጋል:: ጥናቱ አያይዞም በሀገራቸው የውጪ ምንዛሪንና ድህነትን የመዋጊያ መሣሪያ ምንጭ መሆናቸውን ጠቁሟል:: ምንም እንኳን ለሚኖሩበትም ሆነ ለሀገራቸው ኢኮኖሚ ጠቀሜታን ቢሰጡም ዓለም አቀፍ የገንዘብ ቀውስ በሚከሰት ጊዜ ከስደተኞች የበለጠ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ጉዳት የሚደርስበት እንደሌለ ባለሙያዎች ይናገራሉ:: የሚኖሩበት ሀገር ኢኮኖሚ ከሚኖሩበት ሀገር ተወላጅ ሠራተኞች ይበልጥ ከፍ፣ ዝቅ ያደርጋቸዋል:: ፖሊሲ አውጪዎች የሀገራቸውን ዜጋ በዋናነት ታሳቢ አድርገው የሚያወጧቸው ሕጎች ስደተኞች የተረጋጋ እንቅልፍ እንዲያገኙ የሚያደርጋቸው አይደለም:: ፖለቲካዊ ጫናና ግፊቶች ሲበረቱም ለስደተኞች ዝግ ሆነው የወጡ ሕጎች በይበልጥ ስለሚተረጎሙ ኢካኖሚያዊና የመኖር መብታቸው ይነካል::

ሉላዊነት በአስደናቂ ሁኔታ በተንሰራፋበት ባለፉት ሃያ ዓመታት ስደት ከንግድ ወይም ከውጪ ኢንቨስትመንት ቀጥሎ ተስፋፍቷል:: ሮበርት ሉካስ «International Labor Migration in a Globalization Economy» በሚል ጥናታቸው ላይ እንዳሰፈሩት ስደተኞች ወደ ትውልድ ሀገራቸው የሚልኩት ገንዘብ ያደጉ ክልሎችን በመፍጠርና ሠራተኞች ከፍተኛ ደሞዝ እንዲያገኙ በማድረግ በኩል ትልቅ እድገት ማስገኘቱን አስፍረዋል:: የሮበርት የጥናት ሪፖርት በተጨማሪም ስደት ለስደተኞችና ከፍተኛ ገቢ ላላቸው ሀገራት ከፍተኛ ጥቅም እንዳስገኘ በጥናት መረጋገጡን ያሳያል:: በተለይ ያደጉ ሀገራት የስደተኞችን የጭንቅላት ብቃት ጨምቀው እንደጠጡትና ሠራተኞቹም ቢሆኑ የጥቅም ጉስቁልና እንዳልደረሰባቸው አትቷል::

## ወደ የመን የጠነከረው ስደት

እንደ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR) ገለፃ በ2009 ብቻ ከ74 ሺህ በላይ አፍሪካውያን አካባቢያቸውን በመልቀቅ ወደ የመን ተሰደዋል:: ይህ አሃዝ ከ2008 ጋር ሲነፃፀር 50 በመቶ ብልጫ አሳይቷል:: ሮውተርስ የዜና ወኪል የ«UNHCR» አፈ-ቀላጤ የሆኑት አንድሬጅ ማሄኪች በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ግጭቶችና ኢካኖሚያዊ ጫናዎች የስደተኞችን ቁጥር እንዳሻቀበውና ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በባህር ተሻግረው ወደ የመን የሚላኩ አፍሪካውያን ቁጥር እንዳበዛው

ገልፀዋል:: አፍሪካዊያን ስደተኞች ወደ የመን ለመግባት በሚያደርጉት ትግል «በአውሬዎች የመበላት፣ የመደፈር፣ የመገደል፣ ሻርኮች ወደ በዙበት ባህር የመወርወር አደጋ ይጋለጣሉ::» ይላሉ አንድሬጅ ማሄኪች የስደትን አስከፊነት ሲያስረዱ:: «ከእንቅስቃሴና ከሚኞች ቁጥር አንፃር፣ በኤደን ባህረ ሰላጤ እና በቀይ ባህር ያሉት የባህር መተላለፊያዎች በዓለም እጅግ በርካታ መርከቦች የሚተላለፉባቸው ናቸው» በማለት የባህር መተላለፊያዎችን ይገልጿቸዋል::

እንደ «UNHCR» ስታትስቲክስ መረጃ ከሆነ ባለፉት ዓመታት በየመን በመፍለስ አብላጫ ቁጥር የነበራቸው ሶማሌያዊያን ባለፈው ዓመት በሞቃዲሾ ከነበረው ጦርነት አንፃር እንደሌላው ዓመት በርካታ ሶማሌያውያን ወደ የመን አልፈለሱም:: እንደ ሮውተርስ ገለፃ ከሆነ ወደ የመን የተሰደዱ ሶማሌያዊያን ቁጥር ሰላሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ (32,800) ነው:: የ«UNHCR» አፈ-ቀላጤ የሆኑት አንድሬጅ ማሄኪች ከ42 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ወደ የመን መሰደዳቸውን ሮውተርስ ነግረውናል ብሎ ጽፏል:: አሃዙ ከ2008 ጋር ሲነፃፀር በእጥፍ ብልጫ አሳይቷል:: የኢትዮጵያውያኑ ስደት ወደተለያዩ የአረብ ሀገራት የሥራ እድል «እናገኛለን» ከሚል እሳቤ ነው:: ኮሚሽኑ ከአፍሪካ ቀንድ ቢያንስ 309 ሰዎች በ2009 በጉዞ ወቅት በውሃ መወሰዳቸውን አስታውቋል:: ይህ አሃዝ ባለፈው ዓመት 590 ነበር::

የመን በአሁኑ ሰዓት በ150 ሺህ የሚጠጉ ሶማሌያዊ ስደተኞችን ታቅፋለች:: ኢትዮጵያዊያንን ጨምሮ ብዙዎች የመን የሚደርሱ ስደተኞች አስፈላጊውን ሁኔታ በማሟላት ጥገኝነት አይጠይቁም:: በ2009 ሕጋዊ ባልሆነ ሁኔታ የመን የደረሱ ኢትዮጵያዊያን «እንታሰራለን እና የተለያዩ የቅጣት ዓይነቶች ይደርስብናል በሚል ፍራቻ ጥገኝነት አልጠየቁም» ሲሉ ማሄኪች ተናግረዋል:: ስደተኞቹ የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽነር ባለስልጣናትንም ለማግኘት ፍቃደኛ አይደለም::

## እስር ቤት የታጨቁ

ሶሪያ በቤት ውስጥ ሠራተኝነት ሦስት ዓመት ያለፋት ሶፊያ መሐመድ (የምትጠራው ለጉዞ ሲባል በቀየረችው ስም ነው) ከሶሪያ ወደ ቱርክና ጣሊያን ለመጓዝ ሙከራ የሚያደርጉት ኢትዮጵያውያንን ፈለግ መከተል ብትፈልግም በምትኖርበት ሀገርና ልታቀናበት ባሰበችው ሀገራት የተያዙ ስደተኞች እጣ እስር ቤት መታጨቅ መሆኑን መረጃ በማግኘቷ ሙከራዋ ሊገታ ችሏል:: እንደሰማችው ከሆነ በጣሊያንና ቱርክ በርካታ ኢትዮጵያውያን በእስር ላይ ናቸው:: ለጉዞ በተዘጋው ሶሪያም በእስር የሚማቅቁ ኢትዮጵያውያን መኖራቸውን ትናገራለች:: «የኢትዮጵያዊያን ህይወት በእጅጉ ያሳዝናል» የምትለው ሶፊያ በእዚያ ዓመት ከኤጀንቶች ጋር ተነጋግራ ለመመለስ ችግር ገብቷታል:: «ኤጀንቴ [አረብ ነው] አንድ ኢትዮጵያዊት ደብድቦ ተሰውሯል:: ካገኘሁት ግን ወደ ሀገሬ ለመመለስ ወስኛለሁ» ትላለች::

በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥራ ስምሪት ባለሙያ የሆኑት አቶ ስዑድ መሐመድ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በዓመት ከሀገር የሚወጡ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ምን ያህል መሆኑ እንደማይታወቅ ይገልፃሉ:: «ሕጋዊ ባልሆነ ምክንያት ከሀገር ስለሚወጡ ሰዎች መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፤ ስለ ሕገ-ወጥ ጉዳይ ልገምት ብትልም ትሳሳታለህ::» ይላሉ:: ይህ አሃዝ ለማወቅ የሚያስችል ምንም ዓይነት መረጃ ኖሯቸውም እንደማያውቅ ለአውራምባ ታይምስ ተናግረዋል:: እንደ ባለሙያው ገለፃ ባለፉት ዓመታት ቤሩትና ሶሪያ ለመሄድ የሚያስችል ቪዛ ይሰጥ ስለነበር የሥራ ስምምነት ኮንትራት ተፈራርመው በሕጋዊ ሁኔታ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ከ20 ሺህ እስከ 25 ሺህ የሚሆኑ ዜጎች ይጓዙ ነበር:: በአሁን ሰዓት ሁለቱ ሀገሮች ቪዛ መስጠት ስላቆሙና ጉዞው ስለተዘጋ የተጓዦች ቁጥር ወደ 8 ሺህ አንሷል::

«መረጃ የምትመዘግቡት ወደ አረብ ሀገራት የሚሄዱትን ብቻ ነው?» ተብሎ ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ ስዑድ መሀመድ የሥራ ኮንትራት ተፈራርመው የትም ሀገር ቢሆን የሚሄዱትን እንደሚመዘግቡ ይገልፃሉ:: «ሚኒስቴሩ ወደ ውጪ የሚሄዱ ኢትጵያውያንን በሁለት መልኩ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ይሰጣል:: አንደኛው የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በውጪ ሀገር ሥራ መኖሩን ሲያረጋግጡ ሠራተኛ መርጠው ይልካሉ:: ሁለተኛው ግለሰቦች በራሳቸው ጥረት በዓለም ዙሪያ ሥራ አፈላልገው ካገኙ በኋላ በኤምባሲ በኩል አረጋግጠው እኛጋ ሲመጡ ፈቃድ እንሰጣቸዋለን:: አሃዙ አሜሪካንን ጨምሮ ወደ ተለያዩ ሀገራት የሚጓዙ ኢትዮጵያዊያንንም ያካትታል::

«ኤጀንሲዎቹ በአብዛኛው ፈቃድ ያላቸው ለአረብ ሀገራት ነው» ያሉት የሚኒስቴሩ ባልደረባ ሌላ ከአረብ ሀገራት ውጪ የሚሄዱ ተጓዦች ከ200 እንደማይበልጡ ተናግረዋል:: በየቀኑ በአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት በኩል ወደ ተለያዩ ሀገራት የሚተሙ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር በርካታ መሆኑን ስለሚመለከቱ እንዴት ይኼ ቁጥር በ8 ሺህ ብቻ ሚኒስቴሩ ይገድበዋል? ሊሉ ይችላሉ:: ይህ የአውራምባ ታይምስ ጥያቄም ነበር «ወደ ተለያዩ ሀገራት በቱሪስት ቪዛ፣ በትምህርት ቪዛ፣ በቢዝነስ ሺዛ፣ ወደ አሜሪካ በቤተሰብ በኩል የሚጓዙ መደበኛ ስደተኞች፣ በግላቸው ሥራ አግኝተው የሚጓዙ እና ሌሎችም ወደ እኛጋ ሳይመዘገቡ አሉ:: ቁጥሩም እነሱን አይጨምርም:: የምንመዘግበው ወደ እኛ መጥተው የሥራ ኮንትራት ፈርመው የሚሄዱትን ብቻ ነው» ሲሉ ገልፀዋል::

## የሚኒስቴሩ የጥናት እቅድ

እንደ ሥራ ስምሪት ባለሙያው ገለፃ ባለፈው ዓመት ከማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከኢምግሬሽን፣ ከፖሊስ የተውጣጣ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ነበር:: ዜጎች ወደ አረብ ሀገር ለምን እንደሚሄዱ፣ ወደ አረብ ሀገር ተጉዘው የሚደርስባቸው ችግር፣ ሕገ ወጥ ደላሎችን በተመለከተ እንዲሁም በተመሳሳይ ጉዳዮች

ዙሪያ ኮሚቴው አነስተኛ ጥናት አድርጓል፡፡ እዚህ ጥናት ላይ በመመርኮዝ ወደ ፊትም አማካሪ በመቅጠር ሰፊ ጥናት ለማድረግ አቅዷል፡፡ የሚኒስቴሩ ጥናት የሚያተኩርባቸው ሕገ-ወጥ ዝውውር፣ የስደተኛ ሠራተኞች ግለ-ታሪክ፣ የሕገ-ወጥ ደላሎች ሥራና ግለ-ታሪክ የስደት ምንጩና የሚያስከትለው በጎና መጥፎ ጎን ይካተትበታል፡፡ «በሕጋዊ ሁኔታ የሚሄዱትም ለምን እንደሚሄዱ ለማጥናት አስባችኋል?» ብለናቸው «ይህ አማካሪ ከተቀጠረ በኋላ የሚታሰብ ነው፡፡» ብለዋል፡፡

ሮውተርስና ሌሎች የዜና ማሰራጫዎች የዘገቡት ከ42 ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊያን ወደ የመን የሚያደርጉትን ስደት አስመልክቶ «ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዜና ማሰራጫዎች ከመስማት የዘለለ በተጨባጭ የሚያቀው ነገር የለም» ሲሉ አቶ ስዑድ መሐመድ ለአውራምባ ታይምስ ተናግረዋል፡፡ «ወደተለያዩ ሀገራት የሚጓዙ ስደተኞች መኖራቸው የማይካድ ነው» የሚሉት አቶ ስዑድ በየመን፣ ታንዛኒያና በሌሎች ሀገሮች በሕጋዊም ሆነ ሕጋዊ ባልሆነ ሁኔታ ተሰደው በችግርና በእስር ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን ለማስመለስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ተጨባጭ ሥራ እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ለዚህም በማረጋገጫነት የሚያስቀምጡት ታንዛኒያ በእስር ላይ የነበሩ ኢትዮጵያን ዜጎች መሀከል የተወሰኑትን በዚህ ዓመት ማስመለስ መቻሉን ነው፡፡

ከ23 ሚሊዮን በላይ የህዝብ ቁጥር እንዳላት የምትገመተው ሪፐብሊክ ኦፍ የመን በሰሜን ሳዑዲ አረቢያ፣ በምዕራብ ቀይ ባህር፣ በደቡብ የአረብ ባህር እና የኤደን ባህረ ሰላጤ፣ በምስራቅ ኦማን ያዋስኗታል፡፡ በደቡብ ምዕራብ ኤሽያ በምትገኘው በዚህች ሀገር እና በሌሎች ሀገራት በአሁን ሰዓት ለስደተኞች ቁጥር ማሻቀብ የዜጎች በሀገራቸው የሚከሰቱ ፖለቲካዊ ግጭቶች፣ የኢኮኖሚ ጥገኝነት፣ ከቤተሰብ እና ከቅርብ አካላት ጋር ስምምነት ማጣት እንዲሁም ሌሎች ችግሮችን ባለሙያዎች በምክንያትነት ይጠቅሳሉ፡፡ የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀደው ጥናትም ሆነ ሌሎች አማራጭ የመፍትሔ ሃሳቦች የዜጐቻችንን ስቃይ ለመታደግ መፍጠን እንዳለባቸው «አውራምባ ታይምስ» ታምናለች፡፡ ይህም እንባ ማቆም ባይችል እንኳን መቀነስ ያስችላል፡፡ ለኢትዮጵያዊያን ሰላም በያሉበት!!!

## ቃለምልልስ

# «የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ የመስጠት ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም»

*አቶ ስዬ አብርሃ*

ኅዳር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በግዮን ሆቴል በተደረገ የአቋም መግለጫ ማስተዋወቂያ ስነ ስርዓት ላይ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን እጣ ፈንታ «የመቀየር ኃይል» አላቸው የተባሉት የቀድሞው የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና የቀድሞው የመከላከያ ሚ/ር አቶ ስዬ አብርሃ ፓርቲውን መቀላቀላቸውን ይፋ ሲያደርጉ «በተቃውሞው ጎራ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ» በማለት በርካቶች ለድምዳሜ የተቃረበ ግምታቸውን ማሳደራቸው አልቀረም:: በተለይም የ1987ቱ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት ሲፀድቅ የወቅቱ ርዕሰ ብሔር የነበሩት ዶ/ር ነጋሶ አድርገውት የነበረውን ንግግር በመኮነን «ንግግሬ ራስን መዋሸትና ማታለል ነበር::» በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብንና የፖለቲካ ድርጅቶችን ይቅርታ ይደረግልኝ ብለው የተማፀኑበት መንገድ የአዲሱ ምዕራፍ አመላካች ተደርጎ ተወስዶ ነበር:: በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ጽ/ቤት በመገኘት የፓርቲው ም/ፕሬዚዳንትና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሆነው የ'ተመረጡት'ን አቶ ስዬ አብርሃን ያነጋገረው ባልደረባችን **ውብሸት ታዬ** ግን ከዶ/ር ነጋሶ የቀረቡት የይቅርታ ተማፅኖዎች በአቶ ስዬ አተያይ ከወቅቱ የፈጠኑና ራሱን የቻለ ምዕራፍ የሚያስፈልጋቸው ሆነው ተገልፀዋል ይለናል:: በእነዚህና ፓርቲውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ቆይታ አድርገዋል::

**ሰሞኑን ከአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ተከታትየው ነበር:: የቀድሞው የኢፌዴሪ ፕ/ት ዶ/ር ነጋሶ የስልጣን ዘመናቸውን አስመልክቶ ሰራሁት ላሉት ስህተት ይቅርታ ከጠየቁበት ሁኔታ በተለየ የመከላከያ ሚ/ር፣ የኤፈርት ዳይሬክተር፣ የብሔራዊ ባንክና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦርድ ሰብሳቢ ሆነው መስራትዎን አስመልክቶ በኩራት ድምጸት ሲናገሩ ተደምጠዋል:: በእነዚያ በከፍተኛ ስልጣን ላይ በነበሩበት ዘመናት እንደድርጅትና እንደግለሰብ ይቅርታ የሚያስጠይቅ ስራ አልሰራሁም ብለው ያምናሉ?**

በመጀመሪያ መታየት የሚኖርበት ስህተት ተሰርቷል ወይ? የሚለው ነው:: በተለያየ ጊዜ ስገልፀው የነበረው ነው:: ስህተት ተሰርቷል ብዬ አምናለሁ:: በድርጅት ውስጥ ለተሰሩ ስህተቶች እንደአመራር ኃላፊነት ለመውሰድ ምንጊዜም ዝግጁ ነኝ ብዬ ተናግሬያለሁ:: እኔ ወደፊት በትግሉ ውስጥ ለመቀጠል የወሰንኩ ሰው ነኝ:: ካለፈው ስህተቴ ተምሬ የተሻለ እሆናለሁ፣ የተሻለ አስተዋጽኦ አደርጋለሁ ብዬ አምናለሁ:: ፖለቲካ ደግሞ ሰፊ ሂደት ነው፤ በዚህም የሚሰራ ሰው ይሳሳታል:: ቁም ነገሩ ከስህተት መማርና በቀጣይ መልካም ተግባራትን ማከናወን ነው:: አሁንም ቢሆን ስህተት አልሰራም ብዬ አልናገርም:: በተቻለኝ መጠን ስህተት ላለመስራት ጥረት አደርጋለሁ እንጂ:: የኢትዮጵያ ፖለቲካ ደግሞ ብዙ ጉራንጉር የሞላበት ነው:: በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: እኔ ለማለት የምችለው ይህንን ነው::

**ስህተቶች አሉ ብለው ካመኑ በስህተቱ የተጎዱ ወገኖች አሉ ማለት ነውና «ለተሰራው ስህተት ይቅርታ እጠይቃሁ» ማለቱ ከፖለቲካዊ ስብዕና አንፃር ምን ጉዳት አለው?**

ይቅርታ ስለመጠየቅ... የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ ምንም የሚያሳፍር ነገር የለውም:: ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ የመስጠት ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም:: ወደዚያ ደረጃ ላይ ልናደርሰው ነው የምንታገለው ብዬ አምናለሁ:: መጀመሪያ ሕዝቡ የመረጠውንና የፈቀደውን የሚያደርግበት ደረጃ ላይ እናድርሰው::

**ይህ ማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን ባለበት ተጨባጭ ሁኔታ «በድለንሃል፤ ይቅርታ አድርግልን» ለሚሉ ወገኖች ይቅርታ የመስጠት መንፈሳዊ....**

ይኸው ነው:: መልሸዋለሁ::

**በዚሁ ዕለት ለራዲዮ ጣቢያው በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ በገዢው ፓርቲ በደል ቢደርስብዎትም «ችግር የሚፈታው በመነጋገርና በመወያየት እንጂ በምሬት አይደለም» ሲሉ ገልፀዋል:: በአንድነት አመራር መካከል ቀደም ሲል በተፈጠረው ያለመግባባት ለተወሰነው ድርጅታዊ የእገዳ ውሳኔ ይህንን የመነጋገርና የመወያየት መፍትሔ ለምን አትገለገሉበትም? የፓርቲው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ከመሆንዎ አንፃር እንዴት ይመለከቱታል?**

የኢትዮጵያ ፖለቲካ በመረጋገም፣ «የበደለ ይበደል፣ ያጠፋ ይጥፋ» በሚል መርሕ ከተኼደ መውጫ መፍትሔ አይኖረውም:: በፖለቲካ አቋምና በአስተሳሰብ መለያየት ያለ ነገር ነው:: በአመለካከት ልዩነት ሲፈጠር ልዩነቱን ወደጥላቻ ድብድብ፣ አሳሪና ታሳሪ፣ ገዳይና ተገዳይ መውሰድ አግባብ አይደለም:: ከቻልን የልዩነታችንን መሰረቶች መመርመር፣ መወያየትና ለማጥበብ መምከር ይኖርብናል:: ይህ ፈጽሞ የማይቻል ከሆነ እውነታውን ለሕዝብ መግለጽና የሕዝቡን ፍርድ መጠበቅ ከምንም ይሻላል::

**እርስዎና ዶ/ር ነጋሶ ኅዳር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በግዮን ሆቴል አንድነትን መቀላቀላችሁን ይፋ ካደረጋችሁ ከሶስት ቀን በኋላ ፓርቲው በኢምፔሪያል ሆቴል የጠራው ጠቅላላ ጉባኤ «መርህ ይከበር» ከሚሉት አባላት ጋር በተፈጠረው ውዝግብ ሳይካሄድ መቅረቱ ይታወሳል:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ የድምጽ መስጫ ፎርም ታድሎ በየጥጋጥጉ በአባላት በተሞላበት ሁኔታ ወደ አመራሩ መጥታችኋል:: የተመረጣችሁበት ሂደት ከነበረው ግልጽ ያለመሆን ሂደት አንፃር ስለያዛችሁት ከፍተኛ ስልጣን ምን ይሰማዎታል?**

የምናደርገው ትግል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚኖረው ፋይዳ አንፃር ባሉ ጉዳዮች ላይ ብንነጋገር እመርጣለሁ:: ከዚያ ባለፈ በፓርቲ ውስጥ የሚካሄዱ ጉዳዮች እንደዋንኛ አጀንዳ ባይወሰዱ እላለሁ::

***«ዳኝነትና ነፃነት በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ መጽሐፍ መፃፍዎና በቅርቡ እንደሚታተም ተነግሯል:: መጽሐፉ የሚያጠነጥንባቸው መሰረታዊ ሃሳቦች ምንድናቸው?***

እንደሚታወቀው ከ1993ቱ ክፍፍል በኋላ በእኔና በቤተሰቤ ላይ የደረሰ የፍትህ መጓደል ነበር:: ይህንን ሁነት እንደተራ ዘገባ ወይንም በአንድ ግለሰብ ላይ እንደደረሰ ክንዋኔ ተመልክቶ ከማለፍ ይልቅ ከአገራችን ነጻነትና የዳኝነት ስርአት ነፀብራቅ ጋር በማያያዝ ለማቅረብ በመፈለግ ነው:: ከዚያ በመነሳት ሊባል የሚችለውን ግምገማ ለማሳየትና ስለዜጎች ህገ መንግስታዊ መብት፣ ስለዳኝነት ስርአቱ ወዘተ የቀረበበት ነው::

***ስለ 1993ቱ ክፍፍል ካነሱ ... ከሁለታችሁም ወገን «አንጃ» እና «ተንበርካኪ» ከሚሉ የተሸፋፈኑ መከራከሪያዎች ውጭ «ስለሁነቱ በግልጽ የተነገረ ጉዳይ የለም» ይባላልና በዚህ መጽሐፍዎ የተሻሉ መረጃዎችን አካተው ይሆን?***

እንግዲህ ... (እየሳቁ) ዝርዝሩን ሲወጣ ብናነበው ይሻላል::

***በ1967 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ህወሓትን በመመስረት የትጥቅ ትግሉን ከተቀላቀሉ ጀምሮ በብሔር ፓለቲካ ውስጥ ቆይተዋል:: በ1993ቱ ክፍፍል ወቅትም በድርጅቱ አመራር መካከል የብሔርተኝነት ጠገግ የተስተዋለባቸው አቋሞች አሉ ይባላል:: ከዚህ በመነሳት ብዙዎች አቶ ስዬ ክልላዊ ፓርቲን [ቀደም ሲል የተመሰረተው ዓረና] ሊቀላቀሉ ይችላሉ ብለው ገምተው ነበር:: እንዴት የሕብረ ብሔር ፓርቲ ወደሆነው ወደ «አንድነት» መጡ?***

*መታወቅ ያለበት ነገር ከነበረው አስከፊ ጭቆና አንፃር በህወኃት ውስጥ ብንታገልም የትግራይ ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ ጋር በመሆን በዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ጥላ ስር ብቻ ተጠቃሚ እንደሚሆን ይታወቅ ነበር፤ ትግሉም ይህን መሰረት አድርጎ ነው የተካሄደው:: የኢህአዴግ አመሰራረትም ለዚሁ ነበር:: በብሔር ተደራጅቶ የመፋለሙ እንቅሰቀሴ ግብ ኢትዮጵያውያን በጋራ ለሚሿቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች የተካሄደ ትግል ነው:: ዛሬ ጭቆናን የሚቀበል ማንም ብሔር ብሔረሰብ የለም:: አድሎአዊ አሰራሮችን አሜን ብሎ የሚቀበል የለም:: ችግሩ እነዚህ መሰረታዊ የሆኑ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች እየተገፉ ነው:: ፍትህ እየጠፋ የሕግ የበላይነት እየተረገጠ ነው:: የብሔር መብት ከፋፍሎ ከመግዛት ባለፈ ተግባር አልዋለም:: ስለዚህ ሕብረ ብሔራዊነት የፖለቲካ ድርጅቶች የየራሳቸው ልዩነቶች ቢኖሯቸውም የጋራ*

እሴቶችን በማቀናጀት፣ የሁሉንም ፍላጎት አካቶ፣ የሚኖሩ ጭንቀቶችን ከግንዛቤ በማስገባት የሚመሰረት ስርአት በመሆኑ ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ የሆነውን «አንድነት»ን ተቀላቅያለሁ::

**ይህን አመለካከት በመያዝ የሕብረ-ብሔራዊ ፓርቲን ለመቀላቀል የወሰኑት መቼ ነው? በ1993ቱ ክፍፍል? ከእስር ሲፈቱ ወይስ ወደመድረክ መጥተው መሳተፍ ከጀመሩ በኋላ?**

ቆይቻለሁ:: /ፈገግ ብለው/ የመድረኩ አባል ፓርቲዎች ይህን የጋራ ተጠቃሚነት እሴት ለማሳካት እየጣሩ ነው:: በዚህም ተጨባጭ ለውጥና ገንቢ ክንውኖች በመከናወን ላይ ናቸው::

**በመድረኩ ውስጥ ካሉት ሕብረ ብሔራዊ ፓርቲዎች አንዱ እርስዎ የሚመሩት 'አንድነት' ነው:: ምንም እንኳ «ሕብረ ብሔራዊ» የሚያሰኘውን ለሕጋዊ ፓርቲነት የሚያበቃ  መስፈርት አሟልቶ ከምርጫ ቦርድ እውቅና ቢሰጠውም ያለው ሕዝባዊ ተቀባይነት  በአንፃራዊ ሁኔታ በተወሰኑ ክልሎች ላይ ብቻ ነው ይባላል:: ይህ የተቀባይነት እጦት በተለይ ኦሮሚያ ክልል ላይ ይታያል የሚል ግምገማ አለ:: የኦሮሞን ሕዝብ ስነ ልቦና፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶቹን በመረዳት ሁኔታውን ለመቀየር ያላችሁ ዝግጅት ምን ይመስላል?**

ዌል... ይህን ጥያቄና ሌሎች የወል ጥያቄዎችን አካቶ መጓዝ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ቀላል ነገር አይደለም:: ከባድ ነው:: በሂደት እየጠራ የሚሄድና ይህን በትክክል ሚዛኑን ጠብቆ የማስኬድ ጉዳይ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሚዛን የሚወስን ይሆናል:: እርግጥ በዚህ ነጥብ ላይ አንዳንድ ከመንገድ ወጣ ያሉ አመለካከቶች ሊታዩ ይችላሉ:: ወይ ገና ከጠዋቱ [ከጅምሩ] በጥርጣሬ አይን የመተያየት ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: መታመን ጊዜ የሚወስድ ነገር ነው:: በኦሮሞ ሕዝብ ልብ እና በእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ለመታመን ጊዜ፣ ሥራ፣ ግምገማና ማስተካከያዎችን እያደረጉ መጓዝን ይጠይቃል:: የብሔር ተኮር እና ሕብረ ብሔራዊ ፓርቲዎች አደረጃጀትና የሚያራምዱት መርህ ከአንዱ ወደ አንድ የሚያላጋ በመሆኑ እንዳልኩት ያንን ሚዛን ጠብቆ መሄድ ከባድና ጥንቃቄን የሚሻ ነው::

**ምርጫ ቦርድ ባወጣው የአፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄደው ምርጫ የቀሩት በጣት የማቀጠሩ ወራት ብቻ ናቸው:: ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ የፓርቲያችሁ አጠቃላይ ዝግጅት የጊዜ ሰሌዳውን ታሳቢ ያደረገ ነው?**

አንድነት የሚወዳደረው በመድረኩ አማካይነት ነው:: አሁን እየተሰራ ያለው ሥራ አባል ፓርቲዎቹ ብቁ ተወዳዳሪዎች ናቸው የሚሏቸውን ይዘው የሚመጡበት አሰራር ነው:: ከዚያ በኋላ ይኼ ወይም ያኛው በሚፈለገው የመወዳደሪያ ቦታ የሚኖረው ተቀባይነት

ተጠንቶ ሽንሽን ወይም ድልደላ ይካሄዳል፡፡ እርግጥ ዝግጅታችንን አልጨረስንም ይሁንና ግን በአዲስ አበባ ያለውን አጠናቀን ከስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን በቀጣይ ወደ ክልሎች በተመሳሳይ ሁኔታ እንንቀሳቀሳለን፡፡ ሥራው በጋራና በተናጠል ግን በተደራጀ መልኩ እየተካሄደ ነው፡፡

**በምታደርጓቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በአባሎቻችሁ ላይ ጫናዎች እየደረሱ እንዳሉ በተለያዩ ጊዜያት ገልፃችኋል፡፡ ችግሩን ለመቀነስ ያለው አማራጭ ምንድን ነው?**

ነገሩ የጀመረው በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ ነው፡፡ በወቅቱ ጠንካራ ተቃዋሚ ማን እንደነበርና ለምን እንደነበር ታይቷል፡፡ ወደመድረክ ስንመጣ እያጋጠመን ያለው ፈተና አንድ ባህሪ የሚያንፀባረቅበት ነው፡፡ ተሰባስበንና በጠንካራ አደረጃጀት ተዋቅረን ስንመጣ እነዚህን እንቅስቃሴዎች የማሰናከል ርብርብ አለ፡፡ የወ/ሪት ብርቱካን 1ኛ ዓመት እስር መታሰቢያ በመስቀል አደባባይ እንዲከበር አዲስ አበባ መስተዳድርን ጠይቀን የተሰጠን «በቢ.ፒ.አር» ምክንያት ሥራው ከእጃችን ስለወጣ የመፍቀድ መብቱ ለማን እንደተሰጠ አናውቅም የሚል አገር የሰማው አስገራሚ መልስ ነው፡፡ ሌሎች የተለያዩ የማሰናከል ጥረቶች ያጋጥሙናል፡፡ ፓርቲዬን ወክዬ ማለት የምፈልገው ሁለት ነገር አለ፡፡ አንደኛ ችግር መጣ ብለን አንቆምም፣ ሁለተኛ ችግር መጣ ብለን ከመንገዳችን አንወጣም፡፡ ለውጥ እናመጣለን፤ ሕዝቡጋ እንደርሳለን፡፡

**ክብረ መንግስት ከተማ ውስጥ በሚገኝ እስር ቤት ያለ አንድ አባላችሁ «መኢአድን ከተቀላቀልክ ትፈታለህ» መባሉን ዋቢ በማድረግ እየደረሰብን ነው ያሉትን ጫና አስመልክቶ ለአንድ ጋዜጣ የሰጡትን መግለጫ አንብቤ ነበር፡፡ ከሁኔታው ለመረዳት እንደሚቻለው «መኢአድ» ጠንካራ ከሚባሉት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ ነው፡፡ ገዥው ፓርቲ የአንድነት አባላትን ወደመኢአድ አስፈራርቶ በማስገባት ተጠቃሚ የሚሆንበት ስነ አመክንዮ ምንድነው?**

ይህንን ያለው ወይም ያደረገው መኢአድ አይደለም፡፡ አሳሪዎቹ ናቸው፡፡ ለምንና እንዴት ሊያደርጉ ፈለጉ? የሚለው እንደጫና የሚጠቀሙበት ስልት ሊሆን ይችላል፡፡ አንድነትን ልቀቁ ብቻ አይደለም ጫናው፡፡ ወይም መኢአድን ተቀላቀሉ የሚል አማራጭ ማቅረብ ጭምር ነው፡፡ እንደመድረክ እንደራደር ስንል የነበረውም ለእንደነዚህ አይነት ችግሮች ማቃለያ ነበር፡፡ የመደራደር መሰረታዊ ፍላጎት የዜጎችን ነፃነት የማስጠበቅና ምርጫውም ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን መንገድ ለመጥረግ ነበር፡፡

**ባለፈ የህይወት ልምድዎ የትጥቅ ትግሉን ከትግል አጋሮችዎ ጋር በአሸናፊነት ተወጥታችኋል፡፡ ሰላማዊ ትግል የሚካሄድበት ስልት ከትጥቅ ትግል ስልት የራቀ፣**

**ውስብስብና ከባድ ነው የሚል መከራከሪያ ይቀርባል:: ለተቃውሞው ጐራ ካለዎት የቅርብ ጊዜ ተሞክሮ አንፃር ስለአሸናፊነት በልበሙሉነት ለመናገር ይችላሉ?**

**የትጥቅ ትግሉንም ስንጀምረው የነበረው ተመሳሳይ ጥያቄ ነበር:: ከጥቂት ጓደኞቼ ጋር ትግሉን ስንጀምር ሰዎች «ምን ሆናችሁ? ምን ልታደርጉ ነው?» ሲሉንና «ደርግን ለመጣል ነው» ስንላቸው ብዙዎች «አይቻልም!» ነበር የሚሉን:: ጉራ አይሁንብኝና ብዙዎች «አይቻልም!» ያሉት ተችሏል:: በአገር ፍቅር፣ በቅንነትና በበጎ አስተዋይነት ተነስቶ «አይቻልም!» የሚባለው ሁሉ የሚቻል ይሆናል::** አገራችን ውስጥ በርካታ ችግሮች አሉ:: አንዳንዶቹ «ሊፈቱ፣ ሊታረቁ አይችሉም!» የሚባሉ ዓይነት ናቸው:: ግን ደግሞ መሪዎች የሚፈለጉት «አይሆንም፣ ሊሆን አይችልም» የሚባለውን እንዲቻል እንዲያደርጉ ነው::

## ህዝቡ ምን ይላል

# እልህ ምላጭ ያስውጣል

**በንጋቱ ዘገየ**

የአፍሪካ ዋንጫ ነገ ይጀምራል:: ጨዋታው ለዓይናችን ማረፊያ ለሥራ ፈቶች የጊዜ ማሳለፊያ መሆን ቢችልም ሁለት የአእምሮ ፈተና እየሰጠን ነው:: ብሶት የሚያስብስ:: የሚያሳፍርም:: የአፍሪካ ዋንጫን ከጀመሩት ሀገሮች አንዷ የነበረችውና ወደፊት መጓዝ ቢያቅት ያለውን ጠብቆ: መቆየት የማትችለው ኢትዮጵያን በውድድሩ ሜዳ ላይ አናያትም:: ዋንጫውም ደረጃውም ይቅር እንዴት ተከፋይ መሆን ያቅተናል:: ሩጫ ብቻ:: ለወል ስራ ያልተፈጠረን:: ለመጠላለፍ እንጂ ለመደጋገፍ ያልታደልን:: ጨዋታውን በቴሌቭዥን መመልከት እንችል ዘንድ የሚነገረውን ማስታወቂያ የሰሙ አንዲት አረጋዊት ኢትዮጵያ አለችበት በማለት ይጠይቃሉ:: የአውሮፓ ተጨዋቶችን አንድም ሳይቀሩት ልቅም አድርጎ የሚያውቀው የ13 ዓመት የልጃቸው ልጅ ነበር እማዬ የለችበትም:: በማጣሪያው ወድቃለች በማለት የመለሰላቸው:: አዬ ኢትዮጵያ ሩጫ ብቻ ነው የሚሆንላት ማለት ነው:: እናን ተም ሌት ተቀን ማንቼ ቼልሲ: ስትሉ የማታውቁዋቸው የማያውቋችሁን ተጨዋቾች ስትጠሩ ጨዋታ እያላችሁ ለሌቱን አፍጣችሁ ስታድሩ ሰፈሩን በጩኸት ስትረብሹ እንጂ ስለ ኢትዮጵያ መች ስታወሩ ትሰማላችሁ አሉ:: የትናንት ወኔያቸውን በሚያስታውስ የቁጭት ስሜት:: አይ እማ የሌለውን ምኑን እናውራ የቱን እንየው አለ ታዳጊው ወጣት::

የአፍሪከ ዋንጫን ስትመለከቱ ኢትዮጵን ከሜዳው ስታጡ፡ አረጋዊቷ የተናገሩትን ዓይነት ነገር ስትሰሙ አንድ ነገር ፈጥናችሁ እንደምታስታውሱ እገምታለሁ:: ይድነቃቸው ተሰማን:: ጥረው ግረው ያቋቋሙት የአፍሪከ ዋንጫ ሲጀመር ስማቸው ያለመታወሱ፡ ሀገራቸው በሜዳው ያለመታየቷ፡ ቁጭት ይፈጥራል:: አረጋዊቷ እንደዚህ ምርር ብለው የተናገሩ አይሰሙም እንጂ ይድነቃቸው ቢሰሙ እኔ ለዓለም ዋንጫ የጣርኩላት ሀገር፡ ለአፍሪከም አቃታት አይ የጊዜ ነገር፡ቀዳሚ ጀማሪ ፈጥኖ ኋላ ቀሪ፡ በማለት ቁጭታቸውን በተናገሩ ነበር:: እንዴት ይገርማቸው እንዴት ይድነቃቸው፡ ጀማሪዋ ሀገር ስትጠፋ ከሜዳው:: ይብላኝ እንጂ ለእኛ እያለን ለሌለነው፡ አዲስ መስራት ቢያቅተን ጅምር የማንቀጥለው:: እሳቸውስ አሉ ሞተው ይኖራሉ:: የእኛ ግን የክፋታችን ክፋቱ፡ በቁማቸው አናሰራ ታሪከቸውን አንዘክር ሲሞቱ:: አልቅሶ መቅበሩን ግን እናውቅበታለን፡ ተክነንበታል መሆን ሳይሆን ማስመሰልን:: ሞሮኮ አስታውሳ ለስማቸው መጠሪያ ኩዋስ ሜዳ ስትሰራ፡ ስንት የደከሙላት ትውልድ ሀገራቸው፡ ምን ሰራችላቸው::

የአፍሪከ ዋንጫን ጅማሮ አስታውሶን የኢትዮጵያ በሜዳው ያለመታየት እንደ ዜጋ ሆድ አስብሶን የይድነቃቸው አለመታወስ ደንቆን እንደ አቅማችን ከአሰብናቸው ስለሳቸው ከሚባሉ ከብዙ ነገሮች ስብስብ መሀል አንዱን መዘን ፡ተምሳሌትነቱን ተጠቅመን እሳቸውን ማስታወስ እናድርገው የዛሬው ቆይታችንን::

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን ቋሚ ተሰላፊው ይድነቃቸው አሰልጣኝም ነበሩ:: የቡድን አሰላላፍ ከሰሩ በኋላ አስተያየት የሚሰጧቸው እንደ አማከሪ የሚጠቅሙዋቸው ሰው ነበሩዋቸው::ስማቸው ተዘነ ጋኙ:: ከእለታት በአንዱ ቀን ከይድነቃቸው የደረሳቸውን የቡድን አሰላለፍ ተመልክተው የይድነቃቸውን ስም ያወጡና በሌላ ተክተው ይመልሱላቸዋል:: ይድነቃቸው ሲያዩ እንዴት ተደፈርኩ ብለው ያዙኝ ልቀቁኝ አላሉም:: እሱ ማን ሆኖ ነው እኔን የሚያስወጣው ብለውም አልተከፋም፡ ቂም አልያዙም:: ማንም ሊነግረኝ ያልደፈረውን እኔም ማየት ያልቻልኩትን ማርጀተን ነው የነገረኝ ብለው አስተያየቱን ተቀብለው የዛኑ ዕለት ጫማቸውን ሰቀሉ:: ድንቅ ተግባር::

እውነቱን በድፍረት፡ አልያም እንደ አቶ ይድነቃቸው አማካሪ በስልት፡ የሚናገር ጠፍቶ ስንት ጫማ መስቀል የሚገባቸው ሰዎች ጭዋታ ሲያበላሹ እያየን ነው::ፖለቲካ ጡረታ የለውም የተባለ ይመስል ወንበር እስከ መቃብር ብለው የዘመኑን ጨዋታ ያልቻሉ ግን ከሜዳው የማይለዩ እያየን ነው::

አንድ ሰው ጨዋታ የሚያቆመው በእድሜ መግፋት ብቻ አይደልም:: የትናንት ችሎታ ለዛሬው ዘመን ጨዋታ አልመጥን ከአለ፡ ሜዳ ገብቶ ከሌሎቹ ተጨዋቶች ጋር ተግባብቶ መጫወት ከአቃተ ነጋሪ ሳያስፈልግ ድክመቱ ከሜዳ ውጪ ሳይወራ ጫማ መስቀል አዋቂነት ነው:: አሰልጣኙ ባይደፍር ቡድኑ በይሉኝታ ቢታሰር ተመልካች አልየው ይላል:: አይኑን በጨው አጥቦ ከሜዳ ከገባም ኳስ ሲይዝ ይጮህበታል ፡በድክመቱ ላይ መደናገር ይፈጥርበታል::ታዲያ የሚበጀው ሳይቃለሉ ጫማ መስቀሉ ነበር::

ደፍሮ ድክመትን የሚናገር አልያም ከላይ እንደጠቀስናቸው ሰው ጊዜ ጠብቆ መላ ፈጥሮ የሚጠቁም ከተገኘ እንደ ይድነቃቸው ተቀብሎ፡ ስራ ላይ የሚያውል በቶሎ፡ አይገኝም ተፈልጎ፡፡

ከመስማት ማማት ይቀድማል፡ ከመቀበል መወንጀል ይቀናል፡ አስተያየቱ የተነገራቸው የተናቁ መስሎ ነው የሚሰማቸው፡፡እናም የተነገራቸውን የራስ ድክመት ከማየት፡ ነጋሪውን ለማጥፋት ይዶልታሉ ቀን ከሌት፡፡ ለእንደዚህ አይነቶቹ የልብ ልብ የሚሰጡዋቸው እያጨበጨቡም ወደ ገደል የሚገፋፉዋቸው፡ በዙሪያቸው የሚሰባሰቡ ሆድ አደሮች ናቸው፡፡ አሉባልታ የሚያስፋፉ ምስጢረኛ ሆኖ ለመታየት ደፋ ቀና የሚሉ ጥቅም ያስገኝልኛል ለስልጣን ያበቃኛል ብለው ከአሰቡ እናታቸውንም ቢሆን አሳልፈው ከመስጠት የማይመለሱ እነዚህ ከዋናዎቹ በባሰ ጉዳት አላቸው፡፡አሳብቀው ያጣላሉ፡ በሀሰት መስክረው ከስራ ያስወጣሉ፡ አሉባልታ ነዝተው የርስ በርስ መተማመን ያጠፋሉ፡፡ በዚህ ድርጊታቸውም በድፍረት አልያም በብልሀት፡ የሚጠቁሙ ድክመት ፡ የሚናገሩ ስህተት፡ ተስፋ ቆርጠው ማለት ይጀምራሉ ልኑርበት፡፡ ሌላውም እንሱን አይቶ ተነሳሽነቱ ጠፍቶ፡ ጎመን በጤናን ማዜም ይጀምራል፡፡ ይህም ጫማ ሰቅለው ከጨዋታ ውጪ መሆን የሚገባ ቸውን እያበረታታ ችሎታ አላነሰንም ለምቀኛ ወሬ ቦታ አንሰጥም እንዲሉ ይዳርጋቸዋል፡ ቀስ በቀስም ልባቸው እያበጠ ከእብሪት ወደለየለት አንባገነንነት ያደርሳቸዋል፡፡

ዙሪያቸውን ከበው የሚያጨበጭቡ፡ ሲለዩ የሚያሙ፡ ድክመታቸውን እንዲያርሙ እገዛ ማድረግ ያልቻሉ፡ ጌቶቻቸው ሲወድቁ ግን ቆመው ሲስቁ ይታያሉ፡፡ መፈክር የማርክሲዝም ሌኒዝም ነው ባይባልብን «የአንባገነንነት ነጭና ጥቁር የለውም» ብለን መፈክር እናሰማ ነበር ፡፡ ዴሞክራቶች ነን የሚሉትስ መፈክር እያሰሙ አይደለም ወይ የምትሉ ከአላችሁ እንደ ሎቶ ሎተሪ ፋቅ ፋቅ አድርጋ ችሁ እዩዋቸው ነው መልሴ፡፡

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ፡ ባለፈው ሰሞን መቀመጫቸው ቤተ መንግስት የሆነ አንድ ባላሥልጣን ኢህአዴግ ውስጥ ማርኪሲዝም የሚባል ነገር የለም ሲሉ የሰማው ጸጉር ሰንጣቂ ወዳጄ አይፈረድባቸውም እሳቸው አባል የሆኑት ኢህአዴግ መንግስት ከሆነ በኋላ ነው፡፡ ማሌሊትን የት ያውቁትና፡፡ አቶ መለስ የካድሬው ማሰልጠኛ ኃላፊ እንደነበሩ መች አዩና፡፡ ግን እኮ የማያውቁትን ነገር በልበ ሙሉነት ከመናገር ይለፈኝ ማለት ይቻል ነበር፡፡ ባለሥልጣን መሆን ማለት ሁሉን ማወቅ አይደል አለኝ፡፡

ሳምንት ቅዳሜ እለት አስበን ሳይሆን በድንገት፡ ሶስት ጉዋደኛሞች ተገናኘን አውራ አምባን ለማየት፡፡ ከመከከላችን ፈጣኑ የፊት ገጹን ቃኝቶ ውስጡን ሳያይ የጀርባውን ገጽ አዞረና ዋው እልህ ምላጭ ያስውጣል በማለት ሳይታውቀው ጮሆ ተናገረ፡፡ ሁለታችን እንደየፍጥነታችን የውጥ ገጾችን እያገላበጥን ነበርና ሁኔታው አደናግጦን ቀና ስንል የወ/ት ብርቱከን ፎቶ የጋዜጣውን የመጨረሻ ገጽ ሞልቶ ይዞታል፡፡ እልህ ምላጭ ያስውጣል ያለበት ምክንያት ግን በቶሎ አልገባንም፡፡ በየእጃችን የያዝነውን ጋዜጣ ገልብጠን ፎቶውን እያየን ምክንያቱን ጠየቅነው፡፡ አይታችሁም የማይገባችሁ ሆናችሁዋል የባሰባችሁ አለና እኛ ያራዳ ልጆች በፍልጥ ሳይሆን በፊሊጥ

ነው የሚገባን በማለት የለመድነውን ጉራውን ከጎረረብን በኃላ ፓርቲው ገንዘብ ከፍሎ ያወጣው ማስታወቂያ እኮ ነው:: ጋዜጣው መቼም ይህን ሁሉ ገጽ በነጻ አይሰጥ አለ:: እኛ ግን አሁንም የነገሩ ምክንያት ስልልገባን ለጉራው ተመቻቸንለት:: እናንተ ከሀ እስከ ፐ ከአልነገሩዋችሁ መች ይገባችኋል አለንና:: የአንድነት አመራር ስለብርቱካን ያለውን አቋም ላለፈው አንድ ዓመት አንብበናል:: ይህ ማስታወቂያ ከአመራሩ አቋሙ አንጻር ሲመዘን የሚገኘው ውጤት አመራሩን የገጠመው ተቃውሞ እልህ ውስጥ ከቶት እንጂ የአቋም ለውጥ አድርጎ ይህንንም አምኖበት የፈጸመው እንዳልሆነ ነው አለ:: ይህ ከሆነ እልህ ምላጭ ያስውጣል ብቻ ሳይሆን የጠሉትንም ያስወድዳል ማለት ያስችላል:: አዎ ገባህ ማለት ነው:: ዘገየህ እንጂ በማለት የመጀመሪያው አሁንም ጎረረ::

እኔ ግን ከፎቶ ግራፉ ግርጌ የተጻፈው መልእክት ላይ ነበርኩ:: በተለይ ከማርቲን ሉተር ኪንግ አባባል ተወስዶ የተጻፈው ቀልቤን ስቦታል:: «በመጨረሻው ሰዓት አሳሪዎቻችን ምን እንዳሉ ሳይሆን የወዳጆቻችንን አረምሞ/ዝምታ/እናስታውሳለን ይላል:: ብርቱካን ገና ሳትታሰር በፖሊስ በተጠራችበት ወቅት የራስሽ ጉዳይ ብሏል ተብሎ የሚወቀሰው የአንድነት አመራር ነው የጻፈው ማለት ይቸግራል:: ከሆነ ደግሞ በራስ ላይ የተሰጠ ምስክርነት ነው:: ማነው የጻፈው ብሎ የሚያጠያይቅም ነው:: በእርግጥ ታምኖበት ሁሉም የአመራር አባል አውቆት:ከሆነ የተጻፈው አመራሩ በሰራው በተናገረው: ሁሉ ተጸጽቷል ማለት ነውና እሰየው የሚያሰኝ ነው:: የሚያረጋገጠው ግን በተግባር ሲተረጎም ነው አልኩኝ:: የእኔን ንግግር ሰምተው አይኔንም ተከትለው ከፎቶው ወደ መልእክቱ አመሩ:: ፈጠነ (ስሙ አይደለም ግብሩ እንጂ) ጓደኞችን ጠብታ ውኃ መርከብ ታሰምጣለች የሚለውን አባባል በተግባር ያሳየ ድርጊት በማለት ሌላ እቆቅልሽ ፈጠረብንና ቀድሞ መረዳት በመቻል ስሜት እየተኩራራ ያስረዳን ጀመረ ::

ይህን ማስታወቂያ ያወጣው ብሎም ይህን በራሱ ላይ ምስክርነት የጻፈው የአንድነት አመራር ይህን ተናገርክ ይህን ሰራህ የሚለው የሚጠይቀው ባይኖር ወደዚህ ደረጃ አይመጣም ነበር:: አምነውበትም ይፈጽሙት ወይንም በሁኔታዎች ተገደው እልህ ምላጭ ያስውጣል አንተ እንዳልከው ደግሞ የጠሉትንም ያስወድዳል ሆኖባቸው ይፈጽሙት ሰሩት ግን ቢያንስ ለዛሬ መልከም ነው:: ሰዎቹ ክስ ተመስርቶባቸዋል እየተባለ ነውና ተስፋ ቆርጠው ጎመን በጤናን መዝፈን ከአልጀመሩ ደግሞ ለአመራሩ መታረምም ይጠቅሙታል:: ያኑ ደግሞ ከዚህም የተሸለ ነገር እንሰማለን::

ሲሆን በድፍረት ያም ከአልተቻለ በዘዴ በብልሀት ችግርን የሚጠቁም ድክመትን የሚተች ህገ ወጥነትን የሚሞግት መጥፋቱ እንጂ ቢኖር አጥፊዎች ከፈቀዱ ወደው ከአልሆነም ተገደው ይታረማሉ:: አልያም በጊዜ ጫማቸውን ሰቅለው ጨዋታ ከማበላሸትና ዘወትር ቡድኑን ለሽንፈት ከመዳረግ ገለል ይላሉ ወይንም ይደረጋሉ::

ዝምታ ወርቅ ነው አጉል ባህል ተሰብሮ: ዝም አንልም የሚል ትግል ተጀምሮ ጨኸት ለውጥ ማምጣቱን በዓይናችን ከአየነው ለኋሱ አባት ለአቶ ይድነቃቸው፤ ባለፉበት ሀገር ታሪክ በሰሩበት ለስም መጠሪያቸው ኋሰ ሜዳ እንዲሰራ: ዝም አንልም ብለን እንጩህ በጋራ::

ውድ አንባቢዎች ሳምንት እንደ ዛሬው፡ ወቅታዊ ጉዳይ ትኩረተን ቢስበው የሳምንቱን ለዛሬ በቀጠሮ ነበር ያቆየነው፡፡ ተሻግሬ ጎጃም፤ ወደ መርጦለ ማርያም፤በሀገርኛ ዘዬ ብሶት ሲገለጽ ሰምቼ ላወጋችሁ አልነበር ቀጠሮአችን፡ ግና ዛሬም አልተሳከልን፡፡ አያረጅምና አወጋችኋለሁ እስከዛው ድረስ ግን ምነው ዛሬስ ሰው በጎጃም አዘነ የሚለውን የዳምጠው አየለን ዘፈን ተጋበዙልኝ፡፡ ሰላሙን ይስጠን ደግ ደጉን ያሰማን፡፡ ከመሪዎች እብሪትን ከተቃዋሚዎቹ ክህደትን ከእኛ ዝምታን ያጥፋልን፡፡ የራሳችንን እያኮሰስን የውጪዎችን አድናቂ ከመሆን ያውጣን፡፡ በህይወት ያሉትን እናበረታታ የሞቱትንም እናከብር ዘንድ ልባችን ላይ የተተከለውን የጥላጫ ቋጥኝ ያንሳልን፡፡

የአፍሪካ ዋንጫ ተወዳዳሪ ለመሆን ማጣሪውን ማለፍ አቃተን፡፡ ይድነቃቸውን ለማስታወስ ምን አገደን?

# ቅዳሜ መዝናኛ

## ዳሰሳ

## በገና ጨዋታ ማን ይሆን የተቆጣ?

**በናፍቆት ዮሴፍ**

ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ የልብ ጓደኛሞች የሆኑ ሦስት ትላልቅ ዛፎች የወደፊት ምኞታቸው ይጨዋወታሉ፡፡ አንደኛውም አለ፣ «በዓለም የከበሩ ማዕድናት የሚቀመጡበት እቃ ሁኜ ብሰራ፡፡» ሁለተኛውም አለ፣ «የዓለም ነገስታት የሚመላለሱበት ትልቅ መርከብ ከአካሌ ቢሰራ፡፡» ሦስተኛውም አለ፣ «የዓለም ሕዝብ ደግሞ ደጋግሞ እንዲያስታውሰኝ፣ እንዳይረሳኝ አንድ ከፍታ ቦታ ላይ ቆሜ ብታይ፡፡»

... ዘመናት ተቆጠሩ፡፡ የመጀመሪያው ዛፍ ተቆርጦ ከአካሉ የከብቶች መመገቢያ፣ ግርግም ተሰራ፤ ከብቶቹም ይመገቡበት ገቡ፡፡ ሁለተኛው ተቆርጦ አንዲት ትንሽዬ የአሣ ማጥመጃ ጀልባ ከአካሉ ተሰራች፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ጎረድ ጎረድ ተደርጎ ስርቻ ስር ተቀመጠ፡፡ ሦስቱም ዛፎች ቅስማቸው ተሰበረ፣ «የምኞታችን አልሆነም» አሉ፡፡ ይህን በማለታቸው መሳሳታቸውን ያወቁት ብዙ ዘግይተው ነበር፡፡

ክርስቶስ እየሱስ ከ2002 ዓመታት በፊት ለሰው ልጆች ቤዛ ሊሆን ከድንግል ማርያም ስጋ ነስቶ በግርግም ተወለደ:: /የመጀመሪያው ዛፍ ከከበሩ ማዕድናት ሁሉ የከበረውን ሕፃን ታቀፈ::/ በተለይም ወገኖቹ አይሁዶች በሮማውያን ሲረገጡና ሲገዙ በነበረበት ወቅት የሕፃኑን መወለድ በጉጉት ይጠብቁ ነበር:: እነሆ ያ ቃል ተፈፀመ፤ ክርስቶስ በከብቶች በረት ውስጥ በመወለድ ትህትናን አሳዬ፣ ለዓለም ሁሉ መዳን ሆነ:: ይሁን እንጂ ክርስቶስ ርካሽ በሆነ በከብቶች በረት ውስጥ ተወልዶ ይህንን ሁሉ ተዓምር ይሰራል ብለው ግን ጠብቀው አያውቁም ነበር:: ብዙ ተዓምራትን አደረገ፤ ዓይን አበራ፣ ደዌ ፈወሰ፣ የሞተን አስነሳ:: በትንሽዬ ጀልባ ላይ ከአሣ አጥማጆች ጋር በመሆንም አያሌ አሣዎችን ያጠምዱ ዘንድ አስቻላቸው:: /ሁለተኛው ዛፍ የነገስታት ሁሉ ንጉሥ የሆነውን፣ እርሱን ጫነ::/ በመጨረሻም ተልዕኮው ሊጠናቀቅ ግድ ሆነና ሊሰቅሉት ዘንድ ወሰኑ:: እርሱን የሚሰቅሉበት እንጨት ሲፈልጉም ከስርቻ ስር አገኙና በ«ተ» ቅርፅ አሰናዱት፤ ተጠቀሙበትም:: «የዓለም ቤዛ ሊሆን ወደምድር የመጣው ሕፃን ኖረ ኖረና ዓላማውን ሁሉ ሊፈጥም በመስቀል ላይ ዋለ» እየተባለ ይኸው እስከዛሬ ይነገራል፣ ይታወሳል:: /ሦስተኛውም ዛፍ «መስቀል» ሆኗልና የዓለም ሕዝብ እስካሁን አልዘነጋውም::/

## እንኳን ለ2002 ዓ.ም የክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ!

በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩት በዓላት አንዱ የዓለም ቤዛ፣ የእየሱስ ክርስቶስ ልደት ነው:: በዚህ ታላቅ የልደት በዓል አከባበር ላይ ሽር ጉዱ ድግሱ፣ ድፎ ዳቦው የገና ጨዎታውና የአሲና ገናዬ ጭፈራው እጅግ በጣም ማራኪና በዓሉን ተናፋቂ እሚያደርገው ነው:: ይህ ሁሉ ለበዓሉ የሚደረገው ሽር ጉድና ድግስ እንዳለ ሆኖ ከድግሱ ጐን ለጐን ግን ሊታሰብባቸው የሚገቡና ጥሩ ያልሆኑ ነገሮች እንዳሉም ልብ ሊባል ይገባል::

በገና በዓል አከባበር ዙሪያ የሚደረገው መሰናዶና ድግስ በእርግጥም ዘመድ ከዘመድ፣ ጐረቤት ከጐረቤት ያለውን ተካፍሎ በልቶና ጠጥቶ፣ እንዲሁም ከአዘቦት ቀናት በተለየ መልኩ የሚዋልበት በመሆኑ፣ እንዲሁም ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ሀጢያት በራሱ ቤዛነት ሊያስተሰርይ ወደዓለም በውልደት የመጣበት ቀን በመሆኑ በዓሉን አስደሳችና ደማቅ ያደርገዋል::

ሆኖም የበዓል አከባበራችን አቅምን ያላገናዘበና ለኑሮ ቀወስ የሚዳርግ መሆኑ ጥሩ ያልሆነው ጐኑ ነው:: (ይህ ሁሉንም የበዓላት ወቅት ይመለከታል::) በዓሉን ለማክበር «ከማን አንሼ» በሚል ኪስን ማሚጠጡ ሳያንስ እስከ መበደር ድረስ የሚያስኬድ ከሆነ ከበዓልነቱ ይልቅ ጭንቀቱና መጪው የእዳ መክፈያ ጊዜ የሚያስከትለው ፈተና ስለሚያመዝን ደስታውን ጉደሎ ያደርገዋል:: «ገንዘብ ካለ ሁሌም ፋሲካ ነው» የሚለውን ብሂል በመዘንጋት ከአቅም በላይ መደገስና ለአላስፈላጊ ወጪ

መዳረግ አሁን ካለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ከወደፊት ጭንቀት አርቆ ማሰብ ብልህነት ነው፡፡ ምክንያቱም ሆድ ዛሬ የቱንም ያህል ቢሞላ ነገ መጉደሉና የተለመደው ሂደቱን መቀጠሉ አይቀርም፡፡

በሌላ በኩል አሁን አሁን በተለይ ታላቅ ሀይማኖታዊ በዓሎች አከባበር ላይ እሴቶቻችንና የበዓላት ግርማ ሞገሶች እየተገፈፉና ጥላቢስ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ በባህል፣ በሃይማኖትና በተለያዩ ዘርፎች ከሌላው ዓለማት የምትለይባቸው ብዙ ቅርሶች አሏት፡፡ ሆኖም እነዚህ ባህላዊ እሴቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸራረፉና ይዘታቸውን እያጡ መጥተዋል፡፡

ለምሳሌ ያህል በገና በዓል ላይ የ«አሲና ገናዬ» የዱሮውና የአሁኑ አጨዋወት በፍፁም አይገናኝም፡፡ አሁን አሁን በዘመነኞች እየተበላሹና በብዛት «አርቴፊሻል» እየሆኑ ነው፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስ መዝሙረ ዳዊት ላይ እንደተጠቀሰው «ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ ገና የተጫወትኩባት ቀኝ እጄ ትርሳኝ፡፡» ተብሏል፡፡ በዛን ዘመን የገና በዓል ሲከበር በተለይም ከምሳ ሰዓት በኋላ በበዓሉ ሥነ-ሥርዓት መሠረት በገጠር በየትኛውም ሜዳ፣ በአዲስ አበባና በተለያዩ ከተሞች እንደስታዲየምና «ጃን ሜዳ» ባሉ ሜዳዎች የገና ጨዋታ ይካሄዳል፡፡

የመጫወቻ ዱላው (ቂሌ) ጫፉ የተቆለመመ ሲሆን «ሩር» ተብላ የምትጠራው ኳስ የምትሰራበት ቁስ እንደ አካባቢው ይለያያል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ከቀለጠ ኮንጐ ጫማ (ላስቲክ) የሚሰር ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ከእንጨት ትሰራለች፡፡ በሌላ አካባቢ ገና የሚጫወቱባትን ኳስ ከኮባ ወፍቾ እንደሚሰሯት ይነገራል፡፡ የሆነ ሆኖ የገና ጨዋታው በሁለት ተቀራኒ ወገኖች የሜደው መሀል ላይ ሩሯን (ኳሷን) በአፈር በመሸፈንና በመቆራቆስ ይጀመርና አንዱ ወገን ወደለላው ጐል በማስቆጠር አንዱ ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ሆኖ ይጠናቀቃል፡፡

ይህ ጨዋታ እድሜ ሳይለይ የሚከናወን ሲሆን ከጨዋታው መጠናቀቅ በኋላ ገና የተጫወቱበትን ዱላ ወደ ላይ ይዘው ከተጫወቱበት ሜዳ በመነሳት «አሲና ገናዬ»ን እየጨፈሩ ወደ ሰፈራቸው ሲመለሱ ማየት ልብን በሀሴት ይሞላ እንደነበር ይነገራል፡፡ አሁን ያ ሁሉ የለም፡፡ ቢኖርም ያን ያህል ለዓይን የሚሞላ አይደለም፡፡ ስለዚህ ወደ ማንነታችን መመለስ ሳይኖርብን አይቀርም፡፡

ቀጨኔ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገኘናቸውአባት እንዳጫወቱን በአሁኑ ሰዓት የገና በዓል ብቻ ሳይሆን ሁሉም ታላላቅ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች እየተበረዙና እየተከለሱ ከመሆናቸም በላይ አንዳንድ ሥርዓቶች አንደገንዘብ ማስገኛ እየተወሰዱ እንደሆነ ገልፀው በጊዜ አንድ እልባት ካልተበጀለት የታሪኩና የሥርዓቱ ዳና እስከመጥፋት ሊደርስ እንደሚችል ያላቸውን ሥጋት አጫውተውል፡፡

በዚያው ቤተክርስቲያን ውስጥ ያገኘናቸው አንዲት አዛውንት መነኩሲት «በቀደመው ዘመን የገና በዓል አከባበር እንዲህ የዋዛ አልነበረም» ይላሉ፡፡ መነኩሲቷ «በዚያን ጊዜ ዘመኑም ጥሩ ነበር፡፡» በማለት ከንፈራቸውን በሀዘን ይመጣሉ፡፡

ይሁንና አሁንም የክርስቶስ የልደት በዓል አከባበር ሙሉ በሙሉ የደበዘዘ እንዳልሆነ የገለፁት መነኩሲቷ የአከባበሩ ሁኔታ ግን ትንሽ ፈር የለቀቀ እንደሆነ፣ ይህም ሊስተካከል እንደሚገባው ያስጠነቅቃሉ፡፡ አዛውንቷ ፖስት ካርድና የገና ዛፍ በገና በዓል ተፈላጊነታቸው ለኢትዮጵያውያን ባዕድ እንደሆነና በዚሁ ሳቢያ በየዓመቱ የሚቆረጡት ዛፎችም ያንኑ ያህል ጉዳት እያደረሱ መሆናቸውን አሳስበው «ከዚህ ይልቅ ኢትዮጵያውያን የገናን በዓል የምናከብርበት ግርማ ሞገስ ያለው ሥርዓታችን ይሻለናል» ብለዋል፡፡

ሰሞኑን የገናን በዓል አስመልክተው ለህዝበ ክርስቲያኑ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የሃይማኖት አባቶችም በበኩላቸው በዓሉን ሥናከብር ማሰብ ያለብንን እና ስለ ሃይማኖት ሥርዓት አጠባበቃችን እንድንጠነቀቅ፣ ፈጣሪ የሰጠንን ተፈጥሮ በአግባቡ ባለመጠበቃችን ለተፈጥሮ የአየር ሚዛን መዛባት እንደተዳረግንና ለዚህም ተፈጥሮን በአግባቡ በመጠቀም የተራቡትንና የታመሙትን በመጠየቅና ከክርስቲያን የሚጠበቁትን በጐ አድራጐቶች በማከናወን በዓሉን እንድናሳልፍ አሳስበዋል፡፡

አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ለህዝበ ክርስቲያኑ በጽ/ቤታቸው ባስተላለህፈት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እንደተናገሩት «ይህ ሃይማኖታዊ በዓል አዲስ ህይወት የተጀመረበትና በእግዚአብሔርና በሰው የነበረው ግንኙነት ከተቋረጠ በኋላ እንደገና እንዲቀጥል የተደረገበት፣ እርቅና ሰላም የተመሠረተበት፣ የትሁቱ የሰው ልጅ ልዕልና የተገለጠበትና ለሰው ልጅ የተሰጠው ተስፋ የተፈፀመበት በመሆኑ እለቱን ስናከብር የታመሙትን በመርዳት፣ የሕግ ታራሚዎችን በመጐብኘት፣ ፈጣሪ የሰጠንን ተፈጥሮ በአግባቡ በመጠቀም ቂምን ይቅር በማለት መሆን አለበት» ብለዋል፡፡ አቡነ ጳወሎስ አክለውም ይህን ታላቅ መንፈሳዊ በዓል በምናከብርበት ጊዜ እለቱ «ሰላም በምድር ይሁን» ተብሎ የታወጀውን የሰላም አዋጅ እያስታወስን ሰላም በዓለም ላይ እንዲሰፍንና በህዝቦች መካከል ሰላማዊ ህይወት እንዲኖር መጸለይ እንዳለብን አሳስበው ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ፕሬዝደንት የሆኑት ቄስ ዶ/ር ዋቅስዩም ኢዶሣ በበኩላቸው «እለቱ ከነብዩ ኢሳያስ እርሱ «የሰላም አለቃ» ይሆናል ተብሎ የተነገረለት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመወለዱ ሰላም ወደ ዓለም መምጣቱን ያመላክታል» ካሉ በኋላ «ይህ በክርስቶስ የተገኘ ሰላም በሰዎች ሁሉ መካከል ሊሰፍን ይገባል» ብለዋል፡፡ ሲያክሉም በዓሉን በሰላም በፍቅረና በመረዳዳት ራስ ወዳድ ሳንሆን ማሳለፍ እንደሚገባን አስታውሰው ለመላው የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መልካም በዓል እንዲሆን ተመኝተው ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት ዋና ፀሀፊ የሆኑት ቄስ አለሙ ሼጣም በክርስቶስ የታወጀው ሰላም በሰው ልጆችም መካከል መስፈን እንዳለበትና በመቻቻልና በወንድማማችነት በዓሉን እንድናከብርና ድሆችን በመርዳት የታሰሩትን

በመጠየቅ ህሙማንን በመጎብኘትና በመሳሰሉት በጐ ተግባራት እንድናሳልፍ አሳስበው ነበር።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ቂስ ብጹዕ አቡ ኢየሱስ በበኩላቸው በዓሉን አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክታቸው ማንኛውም ሰው መልካም በማድረግ ከትራፊክ አደጋ፣ ከኤችአይቪ/ኤድስ ራስንና ሌሎችንም በመጠበቅ፣ ተፈጥሮን በመንከባከብ፣ ሰላምን በማስፈን የሰው ልጆች አንዲተጉ ጠይቀው ቤተክርስቲያናቸው በተለያዩ መንገዶች በጐ ተግባራትን እንደምታከናውን ገልፀዋል።

የገና በዓል አከባበርን አስመልክቶ ስለ ፖስት ካርድ፣ የገና ዛፍ፣ በበየዓመቱ ስለሚጨፈጨፉ የጽድ ዛፎችና ስለመሳሰሉት ነገሮች በርካታ ነገሮች ተብለዋል። መልካም ምኞትን ካርድን ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች መግለጽ መልካምነት ሳይኖረው ቀርቶ አይደለም። ቤታችንን በደማመቀ የገና ዛፍ ማሽቆጥቆጥም የተለየ ስሜት ሊፈጥርብን ይችላል። ነገር ግን ስለ ሩር፣ ስለ ቂሌ፣ ስለ አሲና ገናዬ ስናወራ «ያኄ» እያልን እንዳይሆን፣ እንዲሁም ከነጭራሹ በፈረንጆቹ ውስጥ ሰጥመን ስለባህላችን የምንተርከው እንኳን እንዳይዘነጋን መጠንቀቁ ይበልጥ መልካም ነው። የዘንድሮ የገና በዓል በሰላም እና በደስታ እንደተከበረ፣ የሰላምና የፍቅር ሆኖም እንዳለፈ ተስፋችን ነው።

## አንዳፍታ

# «የምቀበርበትን የሬሳ ሳጥን መስራት የምፈልገው ራሴ ነኝ»

**ኮሜዲያን ማርቆስ ፍቅሬ ወልደማርያም**

«እጅጋየሁ» እና «እያንጓለለ» የሚል ርዕስ ያላቸው ሁለት ነጠላ የኮሜዲ ክሊፖችን ሰርቷል። በተለያዩ መድረኮች የኮሜዲ ሥራዎቹን ሲያቀርብ ልብሱን በማወላለቅ በቅጥነቱና ባፈጠጡት የጐድን አጥንቶቹ ይቀልዳል። ኤግዚቢሽን ማዕከል መድረክ ለማግኘት ደጅ ሲጠና እንዳልነበር በአሁን ሰዓት በሚዘጋጁ የተለያዩ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች ላይ በጥያቄ ሥራውን ያቀርባል። የእንጨት ሥራ ባለሙያም ነው። «መቀለድ ሙያዬ ሳይሆን ሆቢዬ ነው» የሚለው ማርቆስ አንድ አፍታ ከአቤል ዓለማየሁ ጋር ቆይታ አድርጓል።

### ከተሰጥዎና ከድፍረት በይበልጥ ያለህ የትኛው ይመስልኻል?

ድፍረቴ ይበልጣል። ለማንም ባለሙያ ተሰጥዎ ያስፈልጋል። ድፍረት ከሌለህ ግን ተሰጥዎህን ይዘህ ብትቀመጥ ዋጋ የለውም።

**ተሰጥዎን የምትገልፀው እንዴት ነው?**

ተሰጥዎ ከአምላክ የሚሰጥ ፀጋ ነው። እሱ ካልሰጠህ የምትፈጥረው ነገር አይደለም።

**መንገድ ላይ፣ ታክሲ ውስጥ፣ ካገኘህ ሰውጋ ትቀልዳለህ። ኮሜዲ ላንተ ሙያህ ነው «ሆቢ»?**

እንዳልከው ሁሉም ቦታ እቀልዳለሁ። ኮሜዲን የያዝኩት እንደ «ሆቢ» ነው። በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በፊልም ያየኸውን ነገር መድረክ ላይ እንድታደርገው ይፈልጋል። ክሊፕ ላይ ሦስቴ ስትገለባበጥ ካየህና መድረክ ላይ ይህን ማሳየት ካልቻልክ ማንም አያምንህም። እዚህ ሀገር ውስጥ ማስመሰል እንጂ መሆን በፍፁም አይታይም። ዘፋኞቻችንማ ከኮምፒዩተር ጋር ጥሩ አድርገው ይዘፍኑና መድረክ ላይ ግን ይንተፋተፋሉ። ኤግዚቢሽን ማዕከል ጥሩ የሥነ-ጥበብ ት/ቤት ነው። ጥሩ ከሰራህ ይጨበጨብልኻል። ጥሩ ካልሰራህ ግን ጠጅ ታሸጐ የሚሸጥበት ዕቃ ተወርውሮብህ ትወርዳለህ። ጁስም የያዘ ቢሆን ያወርድኻል።

**ጥሩ ኮሜዲያን ነኝ ብለህ ታስባለህ?**

አሳስብም በጣም ብዙ ነገሮች ይቀሩኛል። ጥሩ ኮሜዲያን ብዬ እንደማከብራቸው እንደነ ታማኝ በየነ ለመሆን ህሊናን አፅድቶ ብዙ መስራት ይጠበቅብኛል።

**ቁም ነገር ማውራት ትችላለህ?**

በጣም እችላለሁ። ቁም ነገረኛም ነኝ። በሀገር፣ በሥነ-ተዋልዶ፣ በችግር፣ በበሽታ ዙሪያ ወደ ቀልድ የምመልሳቸው ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥቼ ከተከታተልኳቸው በኋላ ነው።

**በመድረክ ሥራ የተከፈለህ ትልቁ ክፍያ ስንት ነው?**

ኧ... ብር [ተደናገጠ] ኧረ የሚወራ አይደለም። እኛ ሀገር የሚከፈልህ ሌላ ሀገር ጉርሻ (ቲፕ) የሚሰጥ ነው። ትልቁ ክፍያ ቴዲ አፍሮ በእስር ከተፈታ በኋላ በስታዲየም ባቀረበው ኮንሰርት ላይ ሥራዎቼን አቅርቤ ህዝብ ያጨበጨበልኝ ነው። በቪሲዲ የሰራሁት ሥራማ ጭራሽ እዳ አለበት።

**መቼም ባልለየው የምትለው ነገር?**

እንጨት ሥራን። ስሞት የምቀበርበትን የሬሳ ሳጥን መስራት የምፈልገው ራሴ ነኝ። (ሣቅ)

**ስለ ሞት ካነሳህ... ሐኪም በአንድ ሳምንት ውስጥ ትሞታለህ ቢልህ ከመሞትህ በፊት ምን ታደርጋለህ?**

በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የሚማሩ ወጣቶችና የተለያዩ አካላት የሚፈጥሩትን የብሔርና የሃይማኖት ልዩነቶች አንድ ቦታ ላይ ሰብስቤ አንድነትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን አስተምሬ ብሞት ደስ ይለኛል፡፡ ከዚያ በኋላ የራሴን የሬሳ ሳጥን ሰርቼ እሞታለሁ፡፡

## ማረሚያ ቤት የሚገኘው ታምራት ገለታ «እያንጓለለ» የሚለውን ክሊፕህን ቢያየው ምን ዓይነት አስተያየት የሚሰጥህ ይመስልኻል?

እኔ የሰራሁት በጥንቁልና ላይ ነው፡፡ ለእከሌ፣ ለእቶ እንትና አላልኩም፡፡ መነሻ የሆኑኝ ጋሼ ግን ቢያዩት የሚጨፍሩበትና የሚዝናኑበት ይመስለኛል፡፡

## ልታገኘው የምትፈልገው ታዋቂ ሰው ማን ነው?

ብችል አፄ ምኒልክን ነበር፡፡ ዛሬ ድረስ በጥሩ እንድናነሳ የሚያደርጋቸውን ትልቅ ሥራ የሰሩ ታላቅ ሰው ናቸው፡፡ «በዚያ ዘመን ምን ዓይነት ትምህርትና ዲግሪ ይሆን የነበርዎት!» እላቸው ነበር፡፡

## ምግብ መስራት ትችላለህ?

ምንም ነገር አልችልም፡፡ ኧ... አንድ የትም ሀገር የማይችሉት አሪፍ ምግብ መስራት ግን እችላለሁ፡፡ ዳቦ ቆርሶ አቮካዶ ውስጡ ከትቶ መብላት፡፡ እንዲህ እያደረኩ ከቁርስ እስከ ራት በልቼ አውቃለሁ፡፡

## መድረክ ላይ እንቅስቃሴ (ሩጫ) ታበዛለህ የሞከርከው የስፖርት ዓይነት ነበር?

ምንም የለም፡፡ ቤቴ ዮሴፍ ቤተ-ክርስቲያን አካባቢ ነው፡፡ ዮሴፍ ከሰው ቁጥር ይልቅ የሬሳ ቁጥር ስለሚበልጥ ወደ ት/ቤት ስንሄድ የመቃብር ቦታውን ለማለፍ በሩጫ ነበር፡፡ ትንሽ «ኮሽ» ካለ መጣብኝ ብለህ ስለምትሮጥ ያ ከሯጮች ይበልጥ ግንዛቤ ሰጥቶኛል፡፡ የቀበሌያችን በረኛ ነበርኩ፡፡ ኳስ ቢያመልጠኝ ልጁን አፈርጠዋለሁ፡፡ ብዙ የፈጠፈጥኳቸው ልጆች አሉ፤ እስከዛሬ ድረስም ያስታውሱኛል፡፡ (ሳቅ በሳቅ)... ኤግዚቢሽን ማዕከል ስገለበጥ ሦስቴ እግሬ ተሰብሮ በቃሬዛ በመውጣት ሪከርድ ይዣለሁ፡፡ እግሬን ታምሜ የነበረ ሲሆን ሰውዬው [አባባ ታምራት] ሽባ አደረጉት ተብሎ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎችም እንዲህ ብለው ጠይቀውኛል፡፡ እኔ እንደውም እያማረብኝ ሄዶ 49 የነበርኩት አሁን 60 ኪሎ ግራም ሆኛለሁ፡፡

# ጥቅሰ-ገና

## የገና የስጦታ መልዕክት

ለጠላትህ ይቅርታን
ለባላጋራህ ትዕግስትን
ለጓደኛህ ልብህን
ለደንበኛህ አገልግሎትን
ለህፃናት ጥሩ ምሳሌነትን
ለሁሉም ሰው እርዳታ ሰጪነትን
ለራስህ ክብርን [በገና ስጦታነት አበርክት/ቺ።]

**አሬን ኦርኖርድ**

## የፍቅር ግንኙነትን መስመር ማስያዝ

ጥሩ ፍቅረኛ ካገኛችሁና ሁለታችሁም አንዳችሁ ላንዳችሁ ጽኑ ከሆናችሁ ሂደቱ የተጠናቀቀ ሊመስላችሁ ይችላል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሂደቱ ገና መጀመሩ ነው። ምንም እንኳን «እኛ» የሚለውን የስሜት አንድነት መስርታችሁ ሊሆን ቢችልም፣ መሠረታዊውን የ«እኛ»ነት ባህሪ የመመስረት ተግባር ይጠበቅባችኋል። በሌላ አባባል ግንኙነታችሁን በአግባቡ መስመር የምታስይዙበት ጊዜ አሁን ነው።

ለፍቅር ግንኙነታችሁ ጠንካራ የስሜት መሠረት ከገነባችሁ አሁን የሚቀረው አብዛኛውን ጊዜያችሁን የምታጠፉበት የዕለት ተዕለት ግንኙነት ነው። አዎን፣ በመካከላችሁ የውህደታችሁን ዘላቂነት የሚያረጋግጥ መግባባት መመስረት ያስፈልጋችኋል። የልቦቻችሁና የነፍሶቻችሁ ግንኙነት አብራችሁ እንድትዘልቁ ሊያደርጋችሁ ይችላል። ነገር ግን የጋራ ተሞክሯችሁን ጥረት እንደምታገኙ ማወቁ ላይ ነው።

ከጋብቻዎች ውስጥ ሃምሳ በመቶው በፍቺ የሚቋጭበት አንደኛው ምክንያት፣ መጽሐፍ ቅዱስ (የሃይማኖት መጽሐፍት) ይዘው ሲማማሉ ከደገሙት ቃል ውጪ በመካከላቸው መግባባትንና ስምምነትን ባለመፍጠራቸው ነው። ሰዎች ይገናኛሉ፣

በፍቅር ይያዛሉ፣ ህልሞቻቸውንና ግቦቻቸውን ይነጋገራሉ፣ በጥቂት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ፣ ከዚያም ይጋባሉ:: ቆይቶ ከዚያ በፊት ያልተረዱት ነገር ይገለጥላቸዋል - ለምን አብረው እንደሚኖሩና አንዱ ከሌላው ምን እንደሚጠብቅ:: ሰዎች ግንኙነታቸውን በምን መልኩ እንደሚመሩት፣ ስለሚኖርባቸው ኃላፊነትና ሚና የሚጨነቁበት ጊዜ እምብዛም ነው:: ጊዜ ሲያልፍ አንድ ቀን አንዳቸው ወይም ሁለቱም ከእንቅልፋቸው ይባንኑና ጋብቻቸው መልህቅ የሌለው መሆኑን ይረዳሉ::

… ሁለታችሁም በምትፈልጉት መንገድ ግንኙነታችሁን መስመር ለማስያዝ ስትፈልጉ እንዴት እንደምትገናኙና እንደምትግባቡ ሊያስማማችሁ የሚችል ስምምነት መስርቱ:: እነዚህ ስምምነቶች በሁለታችሁ መካከል አንዳች ችግር ተከስቶ የመለያየት አደጋ ሲያንዣብብባችሁ አንድ ላይ የሚያስተሳስሯችሁ ማጣሪያዎች ይሆናሉ::

… መፈራረም በጣም ቀላል ተግባር ነው:: ስለዚህ ለውህደታችሁ ያላችሁን የጋራ ዓላማ ቁጭ ብላችሁ በመወያየትና ጥቂት ዋነኛ ጥያቄዎችን በማንሳት ጀምሩ::

… በመካከላችሁ አለመግባባት ሲፈጠር በምን መልኩ መነጋገር እንደሚገባችሁ ደንብ ልታበጁ ትችላላችሁ:: ለምሣሌ አንዱ ሲናገር አለማቋረጥ፣ በተናደዱ ሰዓት ጥሎ አለመውጣት፣ ስሜት የሚጐዳ ነገር አለመወርወር፣ አለመሳደብ፣ አለማንባረቅ፣ አለመማታት:: ይህም ለወደፊቱ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች እንዳይወሳሰቡና በቀላሉ እንዲፈቱ ይረዳል::

በመጨረሻም ህይወት የሚያመጣውን ውጣ ውረድ እንዴት እንደምትቋቋሙት ተወያዩ:: የሚያሳዝን ነገር ሲገጥማችሁ እንዴት ነው የምትቋቋሙት? መከራን እንዴት ልትጋፈጡት ነው የምታስቡት? ስኬትንና አስደሳች ሁኔታዎችንስ እንዴት ነው የምታከብሯቸው? ህይወት ባቡር ቢሆን እነዚህ ስምምነቶች ደግሞ የደህንነት ቀስቶች ናቸው::

**/ዘላለማዊ ፍቅር:- ድርሰት:- ቻርሲ ካርተር-ስኮት ትርጉም:- ማህሌት ጥላሁን - 1996/**

## ቋጠሮ

### ርዕሱ አይታይም

ስቆም-እየሔድኩ ነው
ስተኛ-እነቃለሁ
ስሞት-እኖራለሁ
ዝም ስል ድምጽ አለኝ
ሳለቅስ እስቃለሁ
ስስቅ አለቅሳለሁ

እዚህ-ሆኜ እዛም- አለሁ
በጣም ውብነኝ- እስጠላለሁ
ደስ አይበልሽ- ደስ እላለሁ
ስሞትልሽ- እኖራለሁ
ስስቅብሽ- አለቅሳለሁ
እና! ታዲያ አንች
ስንለያይ- አትዘኝ
የተለያየነው- ስንገናኝ
የተገናኘነው- ስንለያይ ነው።

**/ጨለማን ሰበራ - በአገኘሁ አዳነ ድልነሳሁ - 1997/**

# "Loving"

ቦርሳ ተሸክመው፣
        ከትምህርት ቤት መልስ
ትንሽ ሲቀራቸው
        እሰፈር ለመድረስ
እጅ ለጅ ተያይዘው
        ማሞና ማሚቱ
እሷም ወደ ቤቷ እሱም ወደ ቤቱ
መንታ መንገድ ደርሰው ሊለያዩ ሲሉ
ማሞ «I love you» አላት
እሷም «I love you too!»
ከመክሰስ በኋላ ጓሮ ተገናኝተው
እየተጫወቱ «Loving»ን አንስተው
እቅፍ አረገና ማሞ ድንገት ሳማት
ምን እንደሆን እንጃ?
        ማሚቱን ደስ አላት
ማሞ በረታና አንገቷን አቀፈ
በማያውቀው ስሜት እየተንሳፈፈ
ከንፈሯን ፈልጐ አፉ ውስጥ ወተፈ።

ትናንት እንዳዩት ፊልም እየተናነቁ
ማሞና ማሚቱ ሳሩ ላይ ወደቁ::
አስር ቢደፍን ነው
አልዘለለም ከዚያ፣
ብቻ በደመነፍስ
የማሙሽ ችሎታ
እያደገ መጥቶ ሱሪውን ፈታታ::
እጁን ሰደደና ቀሚሷን ገለበው
የማያውቀው ረሀብ ስላንገበገበው
ክብደት ጨመረና ማሚቱን ተጫናት
ዋይ አለች ልጅቱ
ጠንከር ያለ ነገር አካሏን ሲወጋት::
ማሚት በመጮህዋ ማሞ ደነገጠ
ትናንሽ ዓይኖቹን እያጉረጠረጠ
«አይዞሽ "Loving " ነው» አለ እየተኩራራ
ፍፁም አልተረዳም ስህተት እንደሰራ
"Loving"

**/«ባትጋራኝ» የግጥም መድብል- ከዓለሚቱ ዳመና ሸዋዬ-1995/**

# እኛነት

# ወሎ

- በወሎ በተደጋጋሚ በደረሰው ድርቅና እልቂት በመላው ዓለም የሚገኘው ህዝብ እንባ በእንባ እየተራጨ፣ ያለውን ንብረት እየሸጠ ወይም እያራገፈ ለወሎ ያበረከተውን ያህል በወሎ በሚገኙት ድንቅ ታሪካዊ ቦታዎችና ቅርሶች አድናቆቱን ገልጿል:: በሀገር ጉብኝትም መልክ እየተጓጓዘ ለወሎ ያለውን ፍቅርና አድናቆት አሳይቷል::
- አምስት ዓይነት አበይት ቋንቋዎች የሚናገሩት ብሔረሰቦች በወሎዬነት ስሜትና እምነት ተፈቃቅደውና ተፈቃቅረው ያላንዳች ኮሽታ በወሎ በሰላም ይኖራሉ:: እነሱም አማራ፣ አገው፣ ኦሮሞ፣ ትግራይ እና አፋር ናቸው:: አነስተኛ ቁጥር ያላቸው አርጐባዎችም በወሎ ይገኛሉ::
- በወሎ በምራቃቸው፣ በቱፍታቸውና በስማቸው «አንቱ» የተሰኙ ያለፈውንና መጪውን ጊዜ እንደ ጉድ የሚተረትሩ፣ በጭንቅ የተያዘውንና በጣር ላይ የሚገኝ

ውን ሳይቀር የሚፈውሱና ሙት እስከማስነሳት የደረሱ ታዋቂ ሼኮች፣ ቃልቾች በጠቅላላው አዋቂዎች ነበሩ፣ አሁንም አሉ፡፡

- በወሎ ከጥንት ጀምሮ ህብረተሰቡን በተለያዩ አካባቢዎችና አጋጣሚዎች የሚያዝናኑ አዝማሪዎች የመኖራቸው ሁኔታ ይታወቃል፡፡ አዝማሪዎቹም «ወረሲሞ» (በዘሩ አዝማሪ ሳይሆን ሙያውን የቀሰመ) እና «ደለቅሬ» (በዘሩ አዝማሪ የሆነ) በመባል ይታወቃሉ፡፡

**/ምንጭ፡- ወሎ- የአገር ድባብ - 1984/**

# አለም አቀፍ

# የኢራን የኑክለርና የፖለቲካ ቀውስ

አህመዲኒነጃድ፣ ለሁለተኛ ጊዜ የእስላማዊት ሪፑብሊክ ኢራን ፕሬዝዳንት ሆነው ከተመረጡበት ጊዜ አንስቶ በተለይ ከምዕራብያውያን፣ ከተቃዋሚዎችና ከተቃዋሚዎቹ ደጋፊዎችና ከእስራኤል ጋር የተካረረ የፖለቲካና የወታደራዊ እሰጥ-አገባ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እንደድንበር የለሽ የጋዜጠኞች ተሟጋች ድርጅትና «አምንስቲ ኢንተርናሽናል» ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ቡድኖች፣ የአህመዲኒነጃድ መንግስትን የሚወቅሱ ጠንካራ ትችቶቻቸውን በተደጋጋሚ አስደምጠዋል፡፡ ሆኖም ኢራን እነዚህ ትችቶች ምንጫቸው «የኢራንን እድገት ከማይመኙ ኃይሎች» ነው በሚል ከቁብ የተቆጠሩ አይመስሉም፡፡ ይህም፣ መፍትሔ የታጣላቸው የሚመስሉ የውስጥ የፖለቲካ ቀውሷንና «የኑክለር ጦር መሣሪያ እያመረተች ነው» የሚለውን የምዕራብያውያንንና የአገር እስራኤልን ስጋቶች «ለማደብዘዝ»፣ አገሪቱን «የሚያቅቧት» ከዚህ በፊት ከተጣሉባት ማዕቀቦች በተጨማሪ ሌሎች ማዕቀቦች እዲጣሉባት በተለይ አሜሪካ እና እስራኤል ዓለምን በመጎትጎት ላይ ይገኛሉ፡፡

የእስራኤል መከላከያ ሚኒስትር የሆኑት ኢሁድ ኦልመርት፣ ኢራን የኑክለር ጦር መሣሪያ ባለቤት እንዳትሆን «ማስደረግ ከማይቻልበት ነጥብ» ላይ በፍጥነት እየተንደረደረች እንደሆነ የተናገሩት በፈረንጆቹ አዲስ ዓመት መግቢያ ዋዜማ ላይ ሳለን ነበር፡፡ በዝግ ስብሰባ ለአገራቸው ፓርላማ *የውጭ ጉዳዮችና መከላከያ ኮሚቴ* አብራርተዋል እንደተባለው፣ ኢራን በ2010 (እ.አ.አ.) መጀመሪያ አካባቢ የኑክለር ቦምብ ለመገንባት የሚያስችላት ቴክኖሎጂ ባለቤት እደምትሆንና በ2011 (እ.አ.አ.)፣ አንድ የኑክለር ቦምብ ልትሰራ ትችላለች የሚል ግምታቸውን ተናግረዋል፡፡ የኮሚቴው የቀድሞ ሊቀ-መንበርና የካቢኔ ሚኒስትር የሆኑት ዩቫል ስቴይንትዝ፣ «ኢራን የኑክለር ጦር መሣሪያዎች ለማግኘት እየሞከረች ሲሆን በምዕራብያውያን ምንም ጠንካራ፣ ምንም ፈጣን እርምጃ ካልተወሰደ፣ በአንድ ወይም በሁለት ዓመታት ውስጥ ይሳካለታል» በማለት አጽንዖት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

ኢራን፣ የኑክለር ፕሮግራሟ «ለሰላማዊ ዓላማ የሚውል ነው» የሚል አቋም ብታራምድም፣ ሚኒስትሩ እስራኤል እስላማዊት ሪፑብሊክ ኢራን ኑክለር ቦምብ እያመረተች ስለመሆኗ የማያከራክር መረጃ እንዳላት ይሞግታሉ፤ «እጅግ በጣም ጠንካራ ማለት የሚያስችሉኝ፣ ጠንካራ ማስረጃ እና የስለላ መረጃዎች እውነታው እንደዛ እንደሆነ የሚያሳዩ ሲሆን ይህም ለሁሉም የምዕራብያውያን የስለላ ተቋማት እጅግ ግልጽ የሆነ ነው።» ይላሉ።

የእስራኤል ባለሥልጣናት በኢራን ላይ ጠንካራ ማዕቀቦች እንዲጣሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥሪያቸውን አከታትለው እንዲያቀርቡ ምክንያት ከሆኗቸው አጋጣሚዎች መካከል በቅርቡ ኢራን አስቀድማ በይፋ ሳታስታውቅ ያስወነጨፈችው ረዥም ርቀት ተምዘግዛጊ የሚሳየል ሙከራ የሚጠቀስ ነው። በኢራን ላይ ጠንካራ የሚባል አቋም ከወሰዱ አገራት ውስጥ እስራኤል ቀዳሚዋ ነች፤ አስደንጋጭ ነው የሚያስብል ማስጠንቀቂያም ለኢራን ሰጥታለች፡- የኢራንን የኑክለር ፕሮግራም በተመለከተ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ከከሸፉ፣ ራሷን ለመከላከል አስቀድማ የኢራንን የኑክለር ማብላያ ተቋማትን በወታደራዊ እርምጃ እንደምታወድማቸው  አስጠንቅቃለች።

ምዕራብያውያን፣ ኢራን የኑክለር ጦር መሣሪያዎችን እያመረተች ነው የሚለው ጥርጣሬያቸው የፈጠረባቸውን ስጋት ለማቃለል በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) አማካኝነት የቀረበላትን ጥያቄ ቴህራን ችላ በማለቷ የአሜሪካ ስቴት ዲፓርመንት ሴክሬታሪ ሂለሪ ክሊንተን የተሰማቸውን ብስጭት ገልፀዋል። በተ.መ.ድ. በተደገፈው እቅድ መሰረት፣ ኢራን አብዛኞቹን በዝቅተኛ ደረጃ የበለፀጉ የዩራኒየም ምርቶቿን ደረጃቸው ከፍ እንዲል እንዲጣሩና ከዚያም ከፍተኛ ጥራት ያለው የኃይል ምንጭ እንዲሰጡ ወደ ውጭ ማጓጓዝ የሚጠይቃት ነው። ግና የኢራን ፍራቻ የሚባለው አንዴ ያመረተቻቸውን ከላከች በሁዋላላ ከእንደገና ሁሉንም መልሳ ማግኘት የመቻልና ያለመቻሏ ጉዳይ ነው።

ሴክሬታሪዋ፣ ሰኞ ጥር 4/2010 (እ.አ.አ.) እንዳሉት፣ የኢራንን አጨቃጫቂ የኑክለር ፕሮግራምን በተመለከተ አዳዲስ ማዕቀቦች በቴህራን ላይ እንዲጣል ለማስደረግ አስተዳደራቸው ከአጋሮቹ ጋር መነጋገር መጀመሩን ተናግረዋል። አሜሪካን በመጐብኘት ላይ ከነበሩት የኳታር ጠ/ሚኒስትር ጋር በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ሂላሪ እንዳሉት፣ የማዕቀቦቹ ዓላማ በተራው ሕዝብ «ስቃይ» ላይ ተጨማሪ ስቀይ እንዳያደርስ ተደርጎ ከኢራን መንግስት አመራሮችና ከአገሪቱ እጅግ ጠንካራ ወታደራዊ ቡድን ከሆነው አብዮት ጠባቂ ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ባላቸው ሰዎችና ተቋማት ላይ ጫና ማሳደር ነው።

ኢራን ለጥያቄው ምላሽ እንድትሰጥ አሜሪካ እስካለፈው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ ድረስ የጊዜ ገደብ አስቀምጣላት ነበር። ሆኖም የራሷን አፀፋዊ ምላሽ በመስጠት ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጋዋለች። ያቀረበችውንም ሃሳብ እንዲያሰላስሉትና ምልሻቸውንም እንዲሰጧት እንደነርሱ የጊዜ ገደብ - አንድ ወር - ሰጥታ የነበረ ሲሆን ካልተቀበሏትም በጣም የበለጸገ የዩራኒየም ምርት ማምረቷን በይበልጥ እንድትገፋበት እንደሚያደርጋት አስጠንቅቃ ነበር። ሴክሬታሪ ክሊንተን ሃሳቡን «ተቀባይነት የሌለው»

በማለት አጣጥለውታል:: «ለወታደራዊ ጥቅም ሊውል የሚችል» የዩራኒየም ማበልጸግ እቅስቃሴ ውስጥ እንዳለች ኢራን እየተናገረች በምትገኝበት ወቅት አሜሪካ እንዲሁ ተመልካች አትሆንም ብለዋል ሂላሪ:: አያይዘውም፣ መንግስታቸው ለድርድር በሩ ክፍት መሆኑን ከመጥቀስ አልቦዘኑም::

የኢራን አንዱ የዩራኒየም ማበልረጸጊያ ተቋም በቅድሷ ከተማ - ኩም - አቅራቢያ ባለ ተራራማ ስፍራ ከመሬት በታች በተሰራ ዋሻ ውስጥ እንዳለ የታወቀው በ2009 መስከረም ውስጥ ነበር:: ከዚህም በኋላ ነበር ኢራን በመላ አገሪቱ በርካታ የዩራኒየም ማበልፀጊያ ተቋማትን ከምድር በታች ውስጥ ለውስጥ ገንብታለች የሚሉ ዘገባዎች ተበራክተው መደመጥ የጀመሩት:: እንደ ሪፖርቶች ከሆነ፣ በዚህ የስውር እንቅስቃሴዋ ኢራን ሁለት ግቦችን አሳክታለች:- ተቋማቱ በጠንካራ የተፈጥሮ አለታማ ስፍራዎች ውስጥ በመገንባታቸው ወታደራዊ ጥቃት ቢሰነዘርባቸው እንኳን ሊያወድማቸው የሚችል ጉዳት አይርስባቸውም እንዲሁም የትኛውም ዓይነት የኑክለር ኃይል ባለቤት ለመሆን የምታከናውናቸውን ጥረቶቿን መጠንና ስፋት ለመሸሸግ ችላለች::

የኦባማ አስተዳዳር በኢራን እንዲጣሉ የሚፈልጋቸው ማዕቀቦች እውን እንዲሆኑ፣ በአገሪቱ ያለውን የፖለቲካ አለመረጋጋትና የትብብር መታጣት ለመጠቀም ተስፋ አድርጓል እየተባለ ነው:: ምንም እንኳን ወታደራዊ እርምጃ በኢራን ላይ ለመውሰድ እስራኤል ብታስጠነቅቅም፣ እንዲሁም አሜሪካ አማራጩን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ባታደርገውም ይህ ዓይነት እርምጃ የመወሰዱ እድል ያን ያህል ሰፊ አይመስልም:: ከዚህም በላይ ከወታደራዊ አማራጭ ይልቅ ዲፕሎማሲያዊ ግፊት እንዲደረግ ከፍተኛ ጫና እያሳደሩ ነው የሚባሉት የኢራን ሰው ሰራሽ ዋሻዎች ናቸው - ቴህራን «ሰላማዊ የመከላከል» ስትራቴጂ ብላ የምትጠራቸው ዋሻዎች::

ዢንዋ የዜና ወኪል፣ የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ በኢራን ላይ ተጨማሪ ማዕቀቦች መጣል ውጤት እንደማያመጣ በአንድ ጋዜጣዊ መግለጫ መናገራቸውን ዘግባቧል:: ራሚን መህማን-ፓራስት፣ «ማዕቀቦችን በተመለከተ የእኛን ምልከታ በርካታ ጊዜ ገልፀናል::... ማዕቀቦች፣ ዛቻዎችና መሰል የተሳሳቱ እርምጃዎች ጠቃሚ ይሆናሉ ብለን አንወስዳቸውም፤... የዓለም አቀፉን አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንስ ሕጐችና ድንጋጌዎች ኢራን ሳታወላውል አክብራለች፤» በማለት ተጨማሪ ማዕቀቦችን በቴህራን ላይ መጣል አገራቸው ራሷን ወደ መቻል እንዳትጓዝ እንደሚያደርጋት አስጠንቅቀዋል::

# ኦባማን «ቃላት ያላስመረጠ» ክስተትና በየመን ላይ ያነጣጠረው ትኩረት

የመን፣ በሽብር ተግባሮች ላይ በታወጀው ዓለም አቀፍ ጦርነት «አዲሲቷ የጸረ-ሽብርተኝነት ጦርነት አውድማ» እንደሆነች ታውጇል - ከአፍጋኒስታን፣ ከኢራቅና ከፓኪስታን ቀጥሎ:: ለዚህም የቅርብ ምክንያት የሆነው፣ በፈረንጆቹ የገና በዓል ዕለት መድረሻውን አሜሪካ ያደረገን አውሮፕላን በአየር ላይ ለማጋየት በናይጄሪያዊው ኡመር ፋሩቅ አብዱልሙታላብ ያልተሳካው ሙከራ ነው:: ከተጨናገፈው የአጥፍቶ መጥፋት ሙከራ በኋላ በመላው ዓለም በሚገኙ አየር ማረፊያዎችና፣ በተለይ መዳረሻቸውን አሜሪካ ባደረጉ በረራዎች ላይ መጠነ-ሰፊና ጥብቅ የደህንነት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ምክንያት ሆኗል:: እንደ ሪፖርቶች፣ ኡመር ፋሩቅ አብዱልሙታለብ ሥልጠና እና የፈንጂ ቁሶችን ለማግኘት የቻለው የመን በነበረበት ወቅት እዛው ከሚገኙ የአል-ቃዒዳ አካላት ነበር::

ከክስተቱም በኋላ፣ የምዕራቡ መንግስታትና የስለላ ኤጀንሲዎቻቸው ድህነት ባጎሳቆላት በዚህች አረብ አገር ውስጥ ለአል-ቃዒዳ መፈልፈልና ለተዋጊዎቹ ወታደራዊ ሥልጠና ለመስጠት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አመቺ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው በሚል በየመን ላይ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊና ወታደራዊ ትኩረታቸውን አድርገዋል::

በ«NorthWest Airlines Flight 253» ላይ በተካሄደው ያልተሳካ ጥቃት፣ በጥቅም ላይ ሊውሉ የታሰቡት ፈንጂዎችና መሰናዶው ምንጫቸው የመን ስለመሆኑ በርካታ መረጃዎች ይፋ ተደርገዋል:: አብዱልሙታላብ እስከ ታህሳስ 2009 መጨረሻ፣ ለአራት ወራት ያህል፣ በየመን ቆይታ አድርጎ ነበር:: ለመርማሪዎችም ሰጥቷል በተባለው ቃል መሰረትም ፈንጂዎቹን ያገኘውና ትዕዛዝ የተቀበለው ከዚያው ከየመን ነበር:: ለጥቃቱም በየመን በሚገኘው «አረቢያን ፔኒንዙላ» የሰፈረው የአል-ቃዒዳ አሸባሪ ቡድን ኃላፊነቱን ወስዷል::

ያልተሳካው ውጥን የተፀነሰበት አገር በእርግጥም የመን ከሆነች፣ መሰል ውጥን ከአገሪቱ መነሻውን ሲያደርግ ይህ የመጀመያው አይደለም:: ቀይ ባህርን ከ«ኤደን ገልፍ» እና ከ«አረቢያን ሲ» ጋር በሚያገናኘው ወሳኝ የባህር የንግድ መስመር ላይ ነው የመን የምትገኘው:: በ1980ዎቹ አፍጋኒስታንን የወረረው የሶቪየት ኃይልን ለመፋለም ወደዚያው ለጐረፉት ለአብዛኞቹ የሳዑዲ እና የየመን ሙጃሂዲኖች (ሽምቅ ተዋጊዎች) አመቺ መተላለፊያ ነበረች - የመን:: የአል-ቃዒዳ ታጣቂዎች እንደ አሜሪካ የሚጠሏቸውን፣ በነዳጅ ዘይት የናጠጡ የሳዑዲ አረቢያ ገዥዎች ላይ ጥቃት ለመሰንዘርና ለመደራጀት የመን የተለየች ምርጫቸው እንደሆነች ተዘግቧል:: ከአል-ቃዒዳ ጋር የተያያዙ ናቸው ከሚባሉ ጥቃቶች መካከል:- በነሐሴ 2009 የሳዑዲ አረቢያ የአገር ውስጥ ሚኒስትር ልጅ - ልዑል ናይፍ - ላይ የተደረገው የግድያ ሙከራ አንዱ ነው:: ልዑሉ፣ አጥፍቶ ጠፊ አብደላህ ሀሰን ታሊ አል-አሲር ከሰነዘረባቸው የመግደል ሙከራ በጣም መለስተኛ ቁስለት ብቻ ነበር የደረሰባቸውና በሕይወት የተረፉት:: የሚገርመው ልዑሉ ራሳቸው የሳዑዲ አረቢያ የጸረ-ሽብርተኝነት ተቋም ዋና ኃላፊ መሆናቸው ነው:: ሌላው የሚጠቀሰው ምሳሌ፣ በመስከረም 17/2008 በሰንዓ በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰው ጥቃት ነው:: በወቅቱ እንደፖሊስ የለበሱ ስደስት

ታጣቂዎች ለሌሎች ዋና ጥቃት አድራሾች ከለላ ለመስጠት ከነበሩበት መኪና ውስጥ በመሆን የቶክስ እሩምታ ቢከፍቱም ዓላማቸውን በቦታው የደረሰው የየመን የፖሊስ ኃይል ለማኮላሸት ችሎ ነበር:: በክስተቱ ስድስት ፖሊሶች፣ ስድስት ጥቃት አድራሾችና ቢያንስ አራት በመንገድ ላይ የነበሩ ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል::

ያም ሆነ ይህ፣ የየመን ባለሥልጣናት አንድ ነገር በግልጽ እዲታወቅላቸው መፈለጋቸው አልቀረም:- አገራቸው በሺህዎች የሚቆጠሩ የአሜሪካና ሌሎች የውጭ ወታደሮች የሰፈሩባት ሌላዋ ኢራቅ ወይም አፍጋኒስታን እንድትሆን አይፈልጉም:: የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቡ ባክር አል-ቂርቢ በአንድ ቃለ-መጠይቅ ላይ እንዳሉት፣ አገራቸው አል-ቃዒዳን ለመዋጋት ከአሜሪካ ጋር ለመታገል የተጀመረውን አዲስ ጥምረት አንደምትቀበለውና የሁለቱ አገራት ግንኙነትም «ሥልጠናን፣ የስለላ መረጃዎች ልውውጥንና በወታደራዊ ሎጂስቲኮች መደጋገፍ ዙሪያ ብቻ ይሆናል» በማለት አበክረው ተናግረዋል:: ከእነዚህ ውጭ በምንም ዓይነት መልኩ ከአሜሪካም ጋር ሆነ ከሌሎች ኃይሎች ጋር የመን እንደማትጣመር አስገንዝበዋል::

የምዕራብያውያንና የየመን ባለሥልጣናት በደቡባዊ የመን ያለው ማዕካላዊውን የየመን መንግስት ጥላቻ፣ አሜሪካ በአካባቢው አል-ቃዒዳ ያለውን ፍላጐት ለማክሸፍ የምታደርገውን ጥረቶች ይበልጥ ያወሳስበዋል በማለት ላይ ይገኛሉ:: ባለፈው አርብ ኦባማ ባደረጉት ንግግር፣ በአል-ቃኢዳ ላይ «ከፍተኛ ጉዳት ለማድረስ» አሜሪካ የመንን ጨምሮ ከአጋሮቿ ጋር በቅርበት እየሰራች እንደምትገኝ ተናግረዋል:: ሆኖም አል-ቃዒዳን በይበልጥ የሚያውቁ የመን የሚገኙ ኤክስፐርቶች «ኦባማ እንደዛ ያሉት በደቡባዊ የመን የሚገኙ የማዕከላዊው መንግስት ተቃዋሚ የሆኑ ጠንካራ ጎሳዎችን ድጋፍ ለማግኘት በሚል ነው» የሚል ምልከታ አላቸው:: ደቡብ የመንያውያን፣ መንግስት ከነዳጅ ዘይት ከሚገኘው ገቢ የድርሻቸውን እንደከለከላቸውና አብዛኞቻቸውንም ተወላጆች ከወታደራዊና ከመንግስታዊ ሥራቸው እንዳፈናቀላቸው ይናገራሉ::

የከሸፈው የ«Christmas Day» የጥቃት እርምጃ በማለት የዜና አውታሮች የሰየሙት የአብዱልሙታላብ ጥቃት፣ በመላ አሜሪካ የፈጠረው መረበሽ ቀላል የሚባል አይደለም:: በተለይ በፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማና በደህንነት ሹሞቻቸው መካከል ያስነሳውም አቧራ በአጭር ጊዜ በንኖ የሚጠፋ አይመስልም::

ባለፈው አርብ ፕሬዝዳንቱ አንድ ከፍተኛ ስብሰባ ከደህንነት ባለሥልጣኖቻው ጋር አድርገው ነበር:: በስብሰባውም የአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች የደህንነት አጠባበቅና የስለላ መረጃዎች አሰባሰብና አጠነቃቀር ሥርዓት በይበልጥ የሚያጠናክሩ እርምጃዎች እንደሚወስዱ አስታውቀዋል:: በተለይ የመንን እና ኩባ የሚገኘውን «ጂትሞ» እስር ቤትን የሚመለከቱ አዳዲስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎችንም አስተዳደራቸው ተግባራዊ እንደሚያደርግ ገልጸዋል::

ኦባማ እንዳሉት ሁለት መሰረታዊ የፖሊሲ ክለሳዎች በመጪዎቹ ቀናት ተሰርተው ይጠናቀቃሉ:- የመጀመሪያው በአየር ማረፊያዎች የተሻሉ የምርመራ ዘዴዎች ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ

ስጋቶችን አስቀድሞ አውቆ ወዲያው እርምጃ መውሰድ እንዲቻል የስለላ መረጃዎችን በይበልጥ ብቃት ባለው መልኩ ማሰባጠርና መተንተን የሚያስችል መንገድን መተግበርን ይመለከታል።

ራሳቸው ፕሬዝዳንት ኦባማ እንደሉት፣ አሜሪካ መረጃ የማሰባሰብ ችግር የለበትም። አብዱልሙታላብ አደጋ መረጋገጡን የአገሪቱ መንግስት አስቀድሞ መረጃው እንደነበረው ተናግሯል። ሆኖም በአውሮፕላኑ ላይ ተጠርጣሪው ከመሳፈሩ አስቀድሞ በቂ ሰዎች አላጤኑትም፣ አጢነውም ነገሩ ሊገባቸው አልቻለም ተብሏ። አብዱልሙታላብም በአውሮፕላኑ ላይ ሊፈነዱ የሚችሉ ቁሶችን በውስጥ ሱሪው ይዞ ለመሳፈር ችሏል።

ያን ስህተት ፕሬዝዳንት ኦባማን በእጅጉ ያስቆጣቸውና የአገራቸው የስለላ ተቋማት ባለሥልጣናትን «ቃላት ሳይመርጡ» እንዲወቅሷቸውና እንዲተቿቸው አድርጓቸዋል። «ደግመን ደጋግመን፣ በፍጥነት መረጃዎችን አያይዘን ፈጣን እርምጃ መውሰድ ከጠላቶቻችን አንድ እርምጃ ቀድመን እንድንራመድ እንደሚያደርገን ተምረናል። ... እናም የተሻለ መስራት አለብን ... እናም የተሻለ እናደርጋን።» ብለዋል - ኦባማ። ፕሬዝዳንቱ ከደህንነት አማካሪዎቻቸው ጋር ካደረጉት ስብሰባ በኋላ በጣም ጠንካራ ትችት ሰንዝረዋል። ለዚህም ምክንያቱ አብዱልሙታላብ በአወሮፕላኑ ላይ እንዳይሳፈር ለማድረግ የሚየስችላቸው በቂ መረጃ የስለላ ተቋማቱ የነበራቸው መሆኑና በዚህም ወዲያው የተለያዩ መረጃዎችን አያይዘው የቅድመ-መከላከል እርምጃ ለመውሰድ አለመቻላቸው ነው። ይህንንም አስመልክተው፣ «ይህ ተቀባይነት የለውም፣ እናም በዝምታ አላልፈውም» እስከማለት ያደረሳቸውን ብስጭት በቃላት ገልጸዋል።

ሁለተኛው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለውጥ፣ ጓታናሞን የሚመለከተው ነው። እስር ቤቱን ለመዝጋት የኦባማ አስተዳደር እርምጃዎችን እየወሰደ በሚገኝበት በአሁኑ ሰዓት፣ በእስር ቤቱ የሚገኙ እስርኞችን ከእንግዲህ ወደ የመን መላክ እንደሚቆም ተነግሯል። ኦባማ እንዳሉት፣ ጓንታናሞ እስር ቤት «ለአል-ቃዒዳ በአረቢያን ፔኒንዙላ ለመመስረቱ ግልፅ ዓላማው ያ ነበር፤» በማለት ወደ የመን እስረኞችን መመለስ ለጊዜውም ቢሆን ከእንግዲህ እንደማይታሰብ ተናግረዋል።

ፕሬዝዳንት ኦባማ በአሜሪካ ላይ ሊሰነዘሩ የሚችሉ ጥቃቶችን ለማጨናገፍ፣ የአሜሪካን የስለላ ኤጀንሲዎች ዋና ዋና ኃላፊዎች የሽብር አደጋ ሊጋርጡ የሚችሉ ሁኔታዎች ክትትልን በተመለከተ ግዴታዎቻቸውን በግልጽ እንዲያስቀምጡና ሥርዓቱም የተጠርጣሪዎችን ዝርዝር በማካተት የተሻለ ክትትል እንዲደረግ የሚያስችል ጥንካሬ እንዲኖረው አሳስበዋቸዋል። አስፈላጊ እርምጃዎችን ኤጀንሲዎቹና ኃላፊዎቻቸው ካልወሰዱ ተጠያቂ እንደሚሆኑም ጨምረው ተናግረዋል።

ፕሬዝዳንቱ፣ «እንደፕሬዝዳንትነቴ፣ አገራችንን እና ሕዝባችንን የመከላከል ከባድ ኃላፊነት አለብኝ፣ እናም ሲስተሙ [የፀጥታው] ሲሰናከል፣ የእኔ ሽክም ነው።» በማለት የተናገሩት ከአምስተርዳም በመነሳት መድረሻውን አሜሪካ ዲትሮይት ባደረገው አውሮፕላን ላይ ከጽንፈኞች ጋር ቁርኝት አለው የተባለው ናይጄሪያዊው

አብዱልሙታላብ እንዴት በአውሮፕላኑ ላይ ሊሳፈር እንደተፈቀደለት የሚገልጽ ሪፖርት በአስተዳደሩ በ«ኋይት ኃውስ» ይፋ በተደረገበት ወቅት።

በፕሬዝዳንቱና በአማካሪዎቻቸው የተቀመጡት አዳዲሶቹ ፖሊሲዎች እና ሥነ-ሥርዓቶች፣ ኦባማ የአሸባሪዎችን አደጋ በበለጠ ፍጥነት ለመለየት የሚያስችል የመረጃ አጠቃቀም ላይ የስለላ ሥርዓቱ አቅቶታል ያሉትን ለማስተካከል የታለሙ ናቸው። እንደሪፖርቱ፣ የአሜሪካ የጸረ-ሽብርተኝነት ሥርዓትና አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ የሚባሉ ተጠርጣሪዎች ዝርዝር አቀማመጥ ማሻሻያ እንጂ ጥገና የሚያስፈልጋቸው አይደሉም። «በጦርነት ላይ ነን፣ ከአል-ቃዒዳ ጋር ጦርነት ላይ ነን፤» ያሉት ኦባማ፣ «እነርሱን ለማሸነፍ የሚጠይቀውን ሁሉ እናደርጋለን።» በማለት አስፈሪ ማስጠንቀቂያ አስተላልፈዋል።

# ስፖርት

## አብርሃም ጨርቆሴ በጣሊያን ድል አደረገ

- **ኃይሌ፣ ፈጣና ቀነኒሳ በውድድሩ አሸንፈው ያውቃሉ**

ኢትዮጵያዊው የዓለም ወጣቶች የ5 ሺህ ሜትር አሸናፊ አብርሃም ጨርቆሴ በ53ኛው የጣሊያን «ካምፓቺዮ» ዓለም አቀፍ አገር አቋራጭ ውድደር አሸናፊ ሆነ።

ባለፈው ረቡዕ ጣሊያን «ሳንጂኦርጂዮ ሱ ሌግናኖ» ላይ በተካሄደው የ10 ኪሎ ሜትር ፍልሚያ ከኬንያዊው ኢሉድ ኪፕቾጌ ጋር እልህ አስጨራሽ ፍትጊያ አድርጎ መጨረሻ ላይ በአንድ ሰከንድ ቀድሞ በመግባት ማሸነፉን ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል። አብርሃም ርቀቱን ሮጦ ለማጠናቀቅ 28 ደቂቃ ከ52 ሰከንድ ፈጅቶበታል። በ28:53 ኪናቾጌ፣ 28:56 ሞሰስ ማሳይ ሁለተኛና ሦስትኛ የወጡ ኬንያዊያን ናቸው።

በሴቶች በተደረገ የ6 ኪሎ ሜትር ውድድር ሃንጋራዊቷ አኒኮ ካሎቪክስ 20:17 በመግባት በሩጫ ታሪኳ በዚህ ውድድር ላይ ለሦስተኛ ጊዜ አሸናፊ ሆናለች። ከዚህ በፊት በ2004 እና በ2009 አሸናፊ ነበረች። ከጉዳት የተመለሰችው አትሌቷ ከጉልበት ጅማት ጋር በተያያዘ ህመም በህዳር ወር መጨረሻ በፍሎረንስ የተካሄደው የማራቶን ውድድር አምልጧታል። ኤሌና ሮማግኖሎ (20:25) ከጣሊያን፣ ፌደሪካ (20:27) ከኬኒያ ሁለተኛና ሦስተኛ ሆነዋል።

ሦስት ኬንያዊ አትሌቶችን እንዲሁም የስምንት ጊዜ የአውሮፓ አገር አቋራጭ አሸናፊና የ2003 የዚህ ውድድር አሸናፊ የነበረው ዩክሬናዊው ሰርጂይ ሌቢድን አስከትሎ በመግባት ያሸነፈው አብርሃም ታላላቅ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ካሸነፉበት ውድድር ላይ ስሙን አስፍሯል። ባለፉት ዓመታት በ«ካምፓቺዮ» በተደረጉ ውድድሮች ኃይሌ ገ/ስላሴ (1994)፣ ፈጣ ባይሳ (1995)፣ ቀነኒሳ በቀለ (2002) [ሁሉም እ.ኤ.አ.] አሸናፊ ነበሩ። «ኃይሌና ቀነኒሳ ባሸነፉበት ውድድር ላይ ማሸነፍ ትልቅ ክብር ነው። ለእዚህ

ውድድር በጣም ተዘጋጅቻለሁ:: ውድድሩን እወደዋለሁ:: ይህ ሁለተኛ የ«ካምፓቺዮ» ውድድሬ ነው:: በ2008 ከኤድዊን ሶይ እና ሰርጂይ ሌቢግ ኋላ በመግባት ሦስተኛ ወጥቻለሁ:: በቀጣዩ ሳምንት በስፔን ለመሮጥ እቅድ ነበረኝ ነገር ግን ዶሃ (ኳታር) ላይ ለሚካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮና እየተዘጋጀሁ ነው» ሲል በ2008 በዓለም የቤት ውስጥ ሩጫ 3ኛ ወጥቶ የነበረው አትሌቱ በስፔን መወዳደርና አለመወዳደሩ ላይ ድፍን ያለ ምላሽ ሰጥቷል::

# ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ዛሬ በኤደንበርግ ለድል ይጠበቃሉ

ዛሬ ኤደንበርግ ሆሊሩድ ፓርክ አካባቢ ታላቁ የ«BUPA» ዓለም አቀፍ የአገር አቋራጭ ውድድር ይካሄዳል:: ለአሸናፊነት በወንዶች ኢትዮጵያዊያኑ ቀነኒሳ በቀለና ገ/እግዚአብሔር ገ/ማርያም በሴቶች ጥሩነሽ ዲባባና እንግሊዛዊቷ ሃይሌይ ዬሊንግ ለአሸናፊነት ግምት ተሰጥቷቸዋል:: በአሁን ሰዓት በዩናይትድ ኪንግደም ስር የሚገኙ ሀገራት ውስጥ ያለው የአየር ፀባይ ቀዝቃዛ፣ ጤዛማና በረዷማ ሲሆን ሀሙስ ከዜሮ በታች 10 ሴንቲ ግሬድ የአየር ፀባይ ተመዝግቦ ነበር:: በዓመታዊው በዚህ ውድድር ላይ አስፋልት፣ ሳር እና ጭቃ ያለበት መሆኑ የውድድሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ የተቀመጠው መረጃ ያስረዳል:: ይህም የውድድሩን ከባድነት ያሳያል::

ይህ የ5 ኪ.ሜ. ውድድር ከ14 ዓመት በላይ ለሆኑ ሯጮች ክፍት ነው:: ከ7-13 ዓመት ያላቸው ህፃናት በ2.5 ኪ.ሜ. የወጣቶች ውድድር ላይ መካፈል ይችላሉ::

በስኮትላንድ ዋና ከተማ በሚደረገው በዚህ ውድደር ላይ ለሦስት ጊዜያት ያህል አሸንፎ የሚያውቀው ኢትዮጵያዊው ታላቅ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ከታናሽ ወንድሙ ታሪኩ በቀለ ጋር በመሆን ለዚህ ውድድር ልምምድ ሰርቷል::

ሌላው የዓለም አገር አቋራጭ ውድድር አሸናፊው ገ/እግዚአብሔር ገ/ማርያም በህዳር ወር በተመሳሳይ ውድድሮች ተደጋጋሚ ድሎች ማስመዝገቡ በውድድሩ ለድል እንዲጠበቅ አድርጐታል:: የስምንት ጊዜ የአውሮፓውያን የአገር አቋራጭ አሸናፊው ዩክሬናዊው ሰርጂይ ሌቢድ የውድድሩ ጠንካራ ተፎካካሪ ይሆናል ተብሏል:: ሌቢድ ረቡዕ በጣሊያን በአብርሃም ጨርቆሴ አሸናፊነት በተጠናቀቀው የ10 ኪ.ሜ. ውድድር አምስተኛ የወጣ አትሌት ነው::

በሴቶች የዲባባ ቤተሰብ አባል የሆነችው ገንዘቤ ዲባባ፣ የቀድሞ የዓለም ወጣቶች አገር አቋራጭ አሸናፊዋ ኬኒያዊቷ ቪቪያን ቼሩዮት፣ የ4 ጊዜ የዓለም አገር አቋራጭ ሩጫ አሸናፊዋና የኦሎምፒክ ድርብ ድል ባለቤቷ ጥሩነሽ ዲባባ እንዲሁም ዩሌንግ ጠንካራ ፉክክር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ አየለ አብሽሮ፣ አሊ አብዶሽ፣ ቃልኪዳን ገዛኸኝ በውድድሩ ላይ የሚካፈሉ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ናቸው፡፡

# ከመብራት ኃይል ጋር የተለያየው አስራት ኃይሌ ዝምታን መርጧል

በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ በአራት የአዲስ አበባ ቡድኖች ተከታታይ ሽንፈት ያጋጠመው መብራት ኃይል አሰልጣኝ የነበረው አስራት ኃይሌ ከክለቡ ጋር ተለያይቷል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ አሰልጣኞች በውጤታማነት በግንባር ቀደምነት የሚነሳው አስራት በመብራት ኃይል ባለፈው ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ያነሳ ቢሆንም በሊጉ ላይ ግን ውጤታማ መሆን አልቻለም፡፡ መብራት ባለፈው ዓመት ከሊጉ ከመውረድ ስጋት ያመለጠው በመጨረሻዎቹ ሁለት ጨዋታዎች ላይ ነበር፡፡ በዚህ ሲዝን ሜታ አቦ ቢራን፣ ሲዳማ ቡናን፣ ሰበታ ከነማን በማሸነፍ ከሙገር ሲሚንቶ፣ ከድሬዳዋ ከነማ፣ ከሐረር ቢራ እና ከደቡብ ፖሊስ ጋር ደግሞ ነጥብ የተጋራው መብራት ኃይል በአዋሳ ከነማ ሽንፈት ደርሶበታል፡፡ በተከታታይም በአዲስ አበባዎቹ ኢትዮጵያ ባንኮች፣ ኢትዮጵያ መድን፣ ደደቢትና ቅ/ጊዮርጊስ ተሸንፏል፡፡ አስራት ኃይሌ በቅ/ጊዮርጊስ በፍፁም ቅጣት ምት ጐል 1-0 ከተሸነፈ በኋላ ተጨዋቾቹን ተሰናብቶ ክለቡን መልቀቁን ማሳወቁን ውስጥ አዋቂዎች የገለፁልን ሲሆን መብራት ኃይል እሁድ ከትራንስ ጋር በአዲስ አበባ ስታዲየም ላለበት ጨዋታ እስካሁን ድረስ ልምምድ እየሰራ የሚገኘው በምክትል አሰልጣኙ አበበ አማካኝነት ነው፡፡ አስተያየት ሰጪዎች ተስፋዬ ፈጠነ አሊያም ተስፋዬ (ቱታ) ክለቡን ሊይዙት እንደሚችሉ አስራት በክለቡ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ይናገራሉ ነበር፡፡ ጉዳዩን አስመልክተን ለማጣራት ወደ መብራት ኃይል ስፖርት ክለብ ስራ አስኪያጅ አቶ በላይነህ ተሾመ የእጅ ስልክ ላይ ብንደውልም ስልካቸው አይነሳም፡፡

«በአሁኑ ሰዓት ከስፖርት ርቂ ማረፍና ሰላማዊ ኑሮ መምራት እፈልጋለሁ» ያለን አሰልጣኝ አስራት ኃይሌ ለጊዜው ምንም አይነት አስተያየት መስጠት እንደማይፈልግ ገልጿል፡፡ ደደቢት በ32 ነጥብ በሚመራው የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ 13 ነጥብ ያለው መብራት ኃይል 16ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡፡